# ምስለ ዐባይ በአማርኛ ሥነ ጽሑፍ፣ 1957-2008 ዓ/ም

**ታዬ አሰፋ**

**አጠቃሎ**

*ዐባይ ለእልፍ ዓመታት ለጥንታዊዋ ግብፅ ሥልጣኔ ምሰሶዋ የነበረውን ያህል ዛሬም ለብዙ ሚሊዮን ግብፃውያን የሕልውናቸው ዋልታ ነው። ጥቁር ዐባይ ከነጭ ዐባይ ጋራ ካርቱም ላይ ከተቀላቀለ በኋላ የሱዳንን በረሓ አቋርጦ በግብፅ ውስጥ ለመጠጥ፣ ለመስኖ እርሻ፣ ለኤሌክትሪክ ኃይል ማመንጫ፣ ለኢንዱስትሪ ፍጆታ፣ ለጀልባ ትራንስፖርትና ለቱሪዝም መስሕብ ያገለግላል። ከግብፅ ጋራ ባይመጣጠንም፣ ለሱዳንም ዘርፈ ብዙ ጥቅም ይሰጣል። ዐባይ በየዓመቱ ብዙ ቢልዮን ኩብ ጫማ ለም ዐፈር ከኢትዮጵያ እየጠራረገ ለሁለቱ የጎረቤት አገሮች እርሻ ቢያቀርብም ለመነጨበት አገር የነሱን ቅንጣት ያህል ጥቅም ሳይሰጥ ኖሯል። ኢትዮጵያ ለናይል ወንዝ 86% የሚኾነውን ውሃ ብታበረክትም እስካሁን የምትጠቀምበት የዐባይ ውሃ መጠን ከ1% እንደማይበልጥ ይገመታል። አገሪቱ ከዐባይ ወንዝ ፍትሓዊ ተጠቃሚ እንዳትኾን ሲከላከሉ የኖሩት የታችኛው ተፋሰስ ጎረቤቶቿ የሕዳሴው ግድብ ግንባታ መጀመሩ ሲታወቅ ምላሻቸው ከምንጊዜውም የከረረ ባላንጣነት መኾኑ ወንዙ ሦስቱን አገሮች በበጎም ኾነ በክፉ ምን ያህል እንዳስተሳሰረ አንዱ ማሳያ ነው። ዐባይ በዘርፈ ብዙ ጥቅሙ በሦስቱ አገሮች ፖለቲካዊ፣ ዲፕሎማሲያዊና ሃይማኖታዊ ግንኙነት ላይ የታሪክ አሻራውን ትቷል፤ በሕዝቦቹ ሥነ ልቦናና ባህል ላይም ተጽዕኖ አሳድሯል። በኢትዮጵያ የዚህ ተጽዕኖ አንዱ መገለጫ ከሌሎች የአገሪቱ ወንዞች የበለጠ ለዐባይ በሥነ ጽሑፏ ውስጥ የተሰጠው ሰፊ ሽፋን ነው። ስለኾነም የዚህ ጥናት ቀዳሚ ዓላማ ከቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ እስከ ኢሕአዴግ ዘመነ መንግሥት ለንባብ በበቁት የአማርኛ የፈጠራ ድርሰቶች ለዐባይ የተሰጠውን ምስል እና ድርሰቶቹ በዐባይ ዙርያ የሚያጠነጥኑትን ዋና ዋና ጭብጦች መቃኘት ነው። ኹለተኛው ዓላማ ከዚሁ ጋራ በተያያዘ ዐባይ በድርሰቶቹ ውስጥ የተሰጠውን ማኅበረ-ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ሚና፣ እንዲሁም በጊዜ ኺደት ከነዚህ አንጻር የተከሠተን የለውጥ አዝማሚያ ለይቶ ማሳየት ነው። እግረ መንገዱንም ከዐባይ ጋር በተዛመደ በዚሁ ሥነ ጽሑፍ ውስጥ ሱዳንና ግብፅ የተሣሉበትን ዕይታ ይዳስሳል። ጥናቱ የተከተለው ዘዴ ምንባባዊ የይዘት ትንተና ነው። በየዘመኑ ድርሰቶች ዋና ዋና የዐባይ ምስሎችንና ጭብጦችን መዳሰስ ሰፊ የጥናት አድማስን ግድ ስለሚል ለዚህ ዋቢ የኾኑትን የፈጠራ ድርሰቶች ማግኘት የተቻለውን በጥናቱ ለማካተት ተሞክሯል። ለጭብጦቹ ዳራ የኾኑ ሌሎች ዐባይ-ነክ ምርምራዊ ሥራዎችንም እንደ አስፈላጊነቱ በማጣቀሻነት ጥናቱ ተጠቅሟል።*

**ቁልፍ ቃላት፡-** *[ዐባይ፣ ምስለ ዐባይ፣ ዐባይና ጥንታዊ ሥልጣኔ፣ ዐባይና ባህል፣ ድኅነትና ኋላቀርነት፣ዐባይና ልማት፣ ሕዳሴ ግድብ፣ ግብፅ፣ ሱዳን፣ ኢትዮጵያ፣ የውሃ ፖለቲካ]*

### *መግቢያ*

የዐባይ ወንዝ በተረት፣ በዘፈን እና በሃይማኖታዊ ሥነ ጽሑፍ ስሙ ሲነሣ ዘመናት ተቆጥረዋል። ከቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ዘመነ መንግሥት ጀምሮም በተለይ በአማርኛ ሥነ ግጥም የተሰጠው ትኩረት ከጊዜ ወደ ጊዜ እያደገ ኼዷል። ከኢሕአዴግ መንግሥት ምሥረታ በኋላ በከፊልም ኾነ በሙሉ ትኩረታቸውን በዐባይ ወንዝ ላይ ያደረጉ ልቦለዶች ተደርሰው ለንባብ በቅተዋል። ይኹን እንጂ እነዚህ የምናብ ውጤቶች የኢትዮጵያውያን ተመራማሪዎችን ትኩረት መሳብ የጀመሩት (የባይሩ ታፍላን እንደ ጎርጎሮሳውያን አቆጣጠር/እጎአ/ በ2000 ዓ/ም የታተመ ጽሑፍ እና የባይለየኝ ጣሰውን እጎአ በ2002 ዓ/ም ለጉባኤ የቀረበ ጽሑፍ ሳይጨምር) የታላቁ የኢትዮጵያ የሚሌንየም (በኋላ "ሕዳሴ" የተባለ) ግድብ የማእዘን ድንጋይ ከተቀመጠበት ከመጋቢት 24 ቀን 2003 ዓ/ም በኋላ ነው። ለዚህ ምናልባት አንዱ ምክንያት ይህ ግድብ በተለይ በኢትዮጵያ እና ከዚያም አልፎ በዓለም ዙሪያ ከፍተኛ የዜና ርእስ መኾኑ ይሆናል። የግብፅና የሱዳን መንግሥታት ዜናውን በጸጋ አለመቀበልም ለቀጣናዊ የፖለቲካ ውጥረት በር በመክፈት ብሔራዊ ስሜትን መቀስቀሱም ሌላ ምክንያት ሊኾን ይችላል። በመገናኛ ብዙኃን እና በየመሥሪያ ቤቱ ለግድቡ ግንባታ ከሕዝብ ድጋፍ ለማሰባሰብ ሳያቋርጥ የሚኺንደጎደው ቅስቀሳ በዐባይ ላይ በርካታ አዳዲስ ዘፈኖችና ግጥሞች እንዲጎርፉ በመጋበዝ የአጥኚዎችን ትኩረት ስቧል። ይህን ተከትሎም በዐባይ ነክ የፈጠራ ሥራዎች ላይ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ብቻ አምስት የድኅረ ምረቃ ዲግሪ ማሟያ ጥናቶች እጎአ ከ2012 እስከ 2018 ባለው ጊዜ ውስጥ ተሠርተዋል። የውልሰው ሽቴ (2012 እጎአ) ለማስተርስ፣ አሰፋ ዓለሙ (2017 እጎአ) ለዶክትሬት ዲግሪ ማሟያ በየፊናቸው በዐባይ ላይ ያተኮሩ የኢትዮጵያና እና የግብፅ (ዐረብኛ) ግጥሞችን በማነጻጸር አጥንተዋል። ንጉሤ ይልማ (2018 እጎአ) እና አስናቀች ደምሴ (2015 እጎአ) ለዶክትሬት ዲግሪያ ማሟያ ጥናታቸውን በአማርኛ ዘፈኖች ላይ ሠርተዋል። ግርማ ገላዬ (2016 እጎአ) ደግሞ በሃይማኖታዊ ሥነ ጽሑፎች ላይ የማስተርስ ዲግሪ ማሟያ ጥናቱን ሠርቷል። የአምስቱም አጥኚዎች ትኩረት በነዚህ ሥራዎች ውስጥ ዐባይ የተሣለበት ኹኔታ ነው። በተመሳሳይም መርሻ አለኸኝ (2021 እጎአ) በተለያዩ ሃይማኖታዊ የግእዝ ድርሳናትና ጥቂት ዓለማዊ የግእዝና የአማርኛ ቅኔዎች ውስጥ ዐባይ እንዴት እንደተሣለ የሚዳስስ መጽሐፍ አሳትሟል።

የዚህ ጽሑፍ ቀዳሚ ዓላማ ከአፄ ኃይለ ሥላሴ እስከ ኢሕአዴግ ዘመነ መንግሥት የተደረሱ የአማርኛ የፈጠራ ጽሑፎች ውስጥ ለዐባይ የተሰጠውን ምስል፣ የተቀነቀነውን ጭብጥና፣ በዘመን ኺደት ከነዚህ አንጻር የተከሠቱ የለውጥ አዝማሚያዎችን ማሳየት ነው። ሌላው ዓላማው ዐባይ በድርሰቶቹ ውስጥ የያዘውን ባህላዊ፣ ማኅበራዊ፣ ኢኮኖሚዊና ፖለቲካዊ ሚናም ለይቶ ማሳየት ነው። በሦስት ዘመነ መግሥታት ውስጥ ዐባይን በመሰለ ማኅበረ-ኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊና ዓለማቀፋዊ ፋይዳ ባለው የተፈጥሮ ጸጋና ለዘመናት የሕዝባዊ ምናብ ትኩረት የኾነን ወንዝ የሦስት ዘመናት[1] ሥነ ጽሑፋዊ አሣሣል የሚዳስስ ጥናት አድማሱ ሰፊ ስለኾነ ለጥናቱ መሠረት የኾኑ በርካታ የፈጠራ ድርሰቶችን፣ እንዲሁም በሌሎች መስኮች ስለ ዐባይ የተደረጉ ጥናቶችን በማስረጃነት ለመጠቀም

---

[1] ጥናቱ ያካለለው የጊዜ አድማስ ከ1957 ዓ/ም እስከ 2008 ዓ/ም የኾነበት ምክንያት በዐባይ ላይ ተጽፎ ያገኘሁት ቀዳሚው የፈጠራ ድርሰት የታደለ አለነ "የዓባይ ጉዞ" (1957 ዓ/ም የታተመ) ሲኾን የመጨረሻው ያገኘሁት ድርሰት ደግሞ የኤፍሬም ሥዩም "ኑ ግድግዳ እናፍርስ" (2008 ዓ/ም የታተመ) ስለኾነ ነው።

ተሞክሯል። የጥናቱ ዘዴ ምንባባዊ የይዘት ትንተና ሲኾን የፈጠራ ድርሰቶቹ የተመረጡት ለርእሰ ጉዳዩ ባላቸው ፋይዳና አጥኚውም ሊያገኛቸው መቻሉን መሠረት በማድረግ ነው።
ምንም እንኳን በአንዳንድ የዐባይ ጭብጦችና ምስሎች ረገድ መመሳሰሉ ባይቀርም፣ ይኼ ጽሑፍ ከላይ ከተጠቀሱት ቀደም ያሉ ጥናቶች በተወሰነ መልኩ ይለያል። አንደኛ የሚዳስሰው በአማርኛ የተጻፉትን ዓለማዊ የፈጠራ ድርሰቶች ብቻ ስለኾነ ቃላዊና ሃይማኖታዊ ድርሰቶችን አያካትትም። ኹለተኛ እንደ አብዛኞቹ ሌሎች ጥናቶች ትኩረቱ በግጥሞች ላይ የተወሰነ አይደለም፤ አንድ አጭር ልቦለድ፣ አንድ ተውኔትና፣ አምስት ስለ ዐባይ የሚያወሱ ረጅም ልቦለዶችንም ይቃኛል። የስድ ንባብ ሥራዎቹ ቁጥር ያነሰው አጥኚው ሌሎች ተመሳሳይ ሥራዎችን ማግኘት ስላልቻለ ነው። ዐባይን ርእሰ ጉዳይ በማድረግ በብዛት የተደረሱት ግጥሞች ስለኾኑ በጭብጥና በምስል ወካይነታቸው 66 የሚኾኑት ግጥሞች በተለያየ ደረጃ በዚህ ጥናት ተዳስሰዋል። ከእነዚህ ግጥሞች አብዛኞቹ በሦስቱ ዘመነ መንግሥታት በግጥም መድበሎች ታትመው ለንባብ የበቁ ናቸው። (ጥናቱ በድረ ገጽ የወጡ ግጥሞችን አያካትትም።) ስለኾነም ይኼ ጥናት ከዲግሪ ሟሟያዎቹ ጥናቶች አድማሱም ይዘቱም ይሰፋል። በጥናቱ የተካተቱት ግጥሞች መብዛት በየዘመኑ ጎልቶ የወጣውን ምስል፣ ሚናና ጭብጥ ምንነት፣ እንዲሁም በጊዜ ኺደት የታየውን አዝማሚያ በሰፊ የመረጃ መሠረት አስደግፎ ለማሳየት እንዲረዳ ነው። ከላይ የተጠቀሱት ቀዳሚ ጥናቶች ከየዘመኑ አንጻር በድርሰቶቹ ውስጥ ጎልተው የተንጸባረቁ ጭብጦችን፣ ምስሎችንና የለውጥ አዝማሚያዎችን ለመዳሰስ አይሞክሩም። የልቦለድና የተውኔት ሥራዎችን ስለማያካትቱም፤ በነዚህና በግጥሞች መካከል ያሉ የምስልና የጭብጥ መመሳሰልና መለያየትንም አይዳስሱም። ስለኾነም ጥናቶቹ ዐባይ በአማርኛ ሥነ ጽሑፍ ውስጥ ስላለው ምስልና ጭብጥ አጠቃላይ ሥዕል ለመስጠት የአድማስና የምንጭ ውሱንነት አለባቸው። ከዚህ አንጻርም ይኼ ጥናት እነዚህን ክፍተቶች ለመሙላት ይሞክራል። ከአለፍ አገደም ስለ ግጥሞቹ ኪናዊ ባሕርይ ጠቅለል ያለ አስተያየት በዚህ ጥናት ቢቀርብም ይኼ ጉዳይ ራሱን ችሎ ቢመረመር ስለሚሻልና ቦታም ስለሚፈጅ በዚህ ጽሑፍ ትኩረት አልተሰጠውም።

ይህ ጽሑፍ የተደራጀው በዘመናዊ የአማርኛ ሥነ ጽሑፍ ለዐባይ የተሰጡትን ዐቢይ ምስሎችና ሚናዎች ከተያያዥ ጭብጦች ጋራ በሰባት ንኡስ ርእሶች በመመደብና በመተንተን ነው። እነዚህ ርእሶች ለትንተና እንዲመች ጎልቶ በተንጸባረቀው ምስል ወይም ጭብጥ ላይ አተኮሩ እንጂ ሌሎች ንኡሳን ጭብጦችና ምስሎችም ከፊሎቹ ድርሰቶች አሏቸው። አንዳንድ ርእሰ ጉዳዮችም ከሌላው ጋራ ይወራረሳሉ።[2]

1. **ገናኑ ዐባይ፦ የውበት አምባ፣ የሕይወት መድኅን፣ የሥልጣኔ ምንጭ፣ የታሪክ አሻራ**

በአፄ ኃይለ ሥላሴ ዘመነ መንግሥት ስለ ዐባይ ከተደረሱት ግጥሞች አጥኚው ማግኘት የቻለው ከአራት አይበልጡም። እነሱም በዋናነት የዐባይን ታላቅ ወንዝነት፣ የሥልጣኔ ምንጭነት፣ የታሪክ ባለቤትነት፣ የሕይወት መድኅንነት፣ የመንፈሳዊ ኃይልና እና የተፈጥሮ ውበት የሚያደንቁ ናቸው። ይህ አድናቆት በኢትዮጵያ በሚታየው ብቻ የተወሰነ ሳይኾን ድንበር ተሻግሮ ዐባይ በሱዳን እና

[2] በዚህ ጽሑፍ ውስጥ ለማስረጃ ከየድርሰቶቹ የተወሰዱት ጥቅሶች የተጻፉባቸው ፊደላት እንደ ደራስያኑ ምርጫ ቀርበዋል። ለምሳሌ አንዳንዱ ደራሲ *ዐባይ* ብሎ ሲጽፍ ሌላው *ዓባይ* ብሎ ቢጽፍ ፊደላቱን አንድ ወጥ ለማድረግ አልተሞከረም።

በግብፅ ያለውን ሚናና ፋይዳም ታሳቢ ያደረገ ነው። ከነዚህ ግጥሞች ውስጥ የመጀመሪያው የኾነው የታደለ አለነ "የዓባይ ጉዞ" (1957 ዓ/ም) የዐባይን መድኀንነት እንዲህ ሲል ያደንቃል፦

ዐባይ ለክብራሆን የግብጾች ሕይወት
ዕፁብ ግሩማዊ አዳኝ ታምራት (ገጽ 47)

ዐባይን በክረምቱ ወቅት መጋቢዎቹ ወንዞች ከያሉበት መጥተው የመቀላቀላቸውን እውነታ ገባሮቹን እጅ ከሚያስነሳ ባላባት ወይም ገዢ ጋራ በማመሳሰል እንዲህ ያወድሳል፦

በወርኃ ሰኔ በምንጮች ወራት
የወንዞች ጌታ ነህ ግዮን መኳንንት
ተሰብስበው መጡ እጅ ለመንሳት
የቆላውን ሸንተር ደጋውን አቀበት
ጠቅል ጅረቶቹን ሣትተው በአንድነት (ገጽ 47-48)

የዐባይ ዝና ከአገሩ አልፎ በአውሮፓም የናኘ በመኾኑ አሳሾች ሊያዩት እንደመጡና ታሪኩን በመጻሕፍት እንደጻፉለትም ያወሳል፦

ለአገሩም አኩሪ ነው ለኢትዮጵያ ጅረት
ከአውሮጳ ተነሡ አንተን ለማየት
አፍ ከልብ አድርገው ጻፉ መጻሕፍት (ገጽ 48)

የታደለ አለነ ግጥም ዐባይ ለሌላ አገር ሲሳይ በመኾኑ ቁጭት አይታይበትም። የዐባይ ዝና በሌላው ዓለም መናኘት ለአገሩ ኩራት መኾኑን ይመሰክራል። ኾኖም ዐባይ ለኢትዮጵያ ሊሰጥ የሚችለውን ጥቅም ከግብርና ምርት ጋራ ያመሳስልና ምርቱን የፈለገ ያቅናው (ያልማው) በሚል ጠቆም ያደርጋል፦

ወይ ዐባይ ወይ ግዮን የኢትዮጵያ ምርት
አቅኝ ከፈለገ ገበሬው ያምርት (ገጽ 49)

ዐባይን የዓለም የሥልጣኔ ምንጭ አድርጎ ከሁሉም በላይ የሚያንቆላጳላጥሰው ደግሞ በ1964 ዓ/ም በግብጿ የቴብስ ከተማ የተገጠመውና በ1966 ዓ/ም የታተመው የጸጋዬ ገብረ መድኅን "አባይ" ነው። ጸጋዬ በግጥሙ የሚያዜምላት ዐባይ እንስት ናት፤ እናትም ናት[3] — የጥቁር ዘርን፣ የዓለም ሥልጣኔን፣ ታላላቅ አማልክትን፣ ድንቀኛ ጠቢባንን እና ታሪክ ሠሪዎችን ያፈለቀች፤ ከሰዋዊም በላይ

[3] ዐባይን እንደ እንስት እና እንደ እናት የሚያየው ሌላው አድናቂ ግጥም አሰፋ ገ/ማርያም በእንግሊዝኛ የገጠመው "The Nile" ነው። ግጥሙ ዐባይን የድንበር፣ የአገር፣ የጊዜና የቦታ ወሰን የማያውቅ፤ ዕድሜው ዘላለማዊ፣ የሰላም ዘማሪ፣ የሰላም አጋፋሪ፣ ልጆቿ ሁሌም ደስተኛ፤ የሕይወት ሕልማቸው የሰላም፣ የፍቅር፣ የሥራ የኾነ አድርጎ ይሥላል። የአሰፋ ዐባይ እንደ ጸጋዬው ዐባይ ከእውነታው የራቀና እጅግ የጓነ ምስል ተሰጥቶታል።

*መለኮታዊ ቁመና ያላት። ጥንታዊቷን ግብፅ፣ ኑቢያንና ኢትዮጵያን በኩሽ ዘር አጋምዳ፣ ዐፈርና ውሃ ግታ፣ የሥልጣኔያቸውን ዱካ ከደምቢያ እስከ ዴር-ሱልጣን የምታስስ የታሪክ ከታብ ናት፡-*

> አባይ የምድረ-ኩሽ መኩሪያ
> በቅድመ-ታሪክሽ ጥርጊያ
> ከደም-ቢያ እስከ ኑ-ቢያ[4]
> ከሜምፊስ እስከሜሮኤ
> በሥልጣኔሽ ትንሣኤ
> ከዴልታሽ እስከ ዴር-ሱልጣን
> ከኡመ-ራህ እስከ ኡመ-ዱርማን፤
> አባይ የአቴስ የጡቶች ግት
> ለዓለም የሥልጣኔ እምብርት፤
> ጥቁር አባይ የጥቁር ምንጭ
> የካም የሥልጣኔ ፍንጭ (ገጽ 153)

ከሰሜን ምሥራቅ አፍሪካ ታላላቆቹ ነገሥታት የግብፅን መኔስ እና (ዳግማዊ) ራምሴስ፣ የኑቢያን (ዳግማዊ) ፒያንኪ (ገጣሚው "ቢያ-ሃንኬ" የሚለው) እና (ዳግማዊ) ሻባካ ("ሶባቃ" የሚለው)፣ እንዲሁም የአክሱምን ኢዛና ግጥሙ በመጥቀስ የሦስቱን አገሮች ታሪክ ትስስር[5] የምትዘክረውን ዐባይ የሰሃራን በረሓ በወዟ ደም ("በኢትዮጵያ ደም") የምታለመልም "የምድር ዓለም ሲሳይ" ያደርጋታል። የጸጋዬ ዐባይ ተራ የወንዝ ውሃ አይደለችም። የጠቢባንን ብቻ ሳይኾን የአማልክትንም

---

[4] ጸጋዬ "ኢልመ መዳ አባ ገዳ" (1964 ዓ/ም) የተባለ የአማርኛና ኦሮሚፋ ድብልቅ ግጥሙን በንባብ በሚያቀርብበት ጊዜ በመግቢያው ላይ ስለ "የወል ቤት" እና ስለ "የጸጋዬ ቤት" ግጥም ልዩነት ሲያብራራ *ወል* የሚለው ቃል "እጅግ ጥንታዊ የኩሽ ጥቁር ግብፅ ሂሮግሎፊክስ ቃል" ሲኾን የኅብር፣ የአንድነት፣ የጋርዮሽ አመልካች መኾኑን፣ ለምሳሌም የተለያዩ የወል ቤት በጋራ ተጠቃሚዎችን (ሥርገኛ፣ ሙሾ አውራጅ፣ ጦረኛ፣ እረኛ፣ ገጣሚ፣ ወዘተ) እና የተለያዩ የኩሽ ቋንቋ ተናጋሪ ማኅበረሰቦችን/አካባቢዎችን ስሞች (ወልመራ፣ ወለጋ፣ ወሎ፣ ወላይታ፣ ወልቂጤ፣ ወልወል፣ ወዘተ) በመጥቀስ ይህንኑ አንድነትና የጋራ ማንነት በመነሻ ድምፆች መመሳሰል ለማሳየት ይሞክራል። "ገዳ"ንም ግጥሙ እንዲሁ ከግብፅ ጋራ ያዛምዳል። እሳቤው ግብፅ፣ ኑቢያ፣ ኦሮሞ፣ ሶማሌ ያው የኩሽ የዘር ግንድ አካል ነው ለማለት ነው። ("Ilma Madhaa Abbaa Gadaa" በhttps://www.youtube.com/watch?v=8b0VWiEyN7I እይ። ስለ ግብፅ በተለይ እና ስለ አፍሪካ በአጠቃላይ ኩሽ መኾን የጸጋዬን ገለጻ በhttps://www.youtube.com/watch?v=Ny2TMcn9msY እይ።) በ"አባይ" ግጥሙም ውስጥ "ደም-ቢያ"፣ "ኑ-ቢያ"፣ "ኡመ-ራህ"፣ "ኡመ-ዱርማን"፣ "ቢያ-ሃንኬ" የሚሉትን ቃላት በሰረዝ የሚነጣጥለው፣ ሻባካን "ሶባቃ" የሚለው (የኦሮምኛውን "ሶቦቃ" የሚመስል ስም) የጥንታዊ ኑቢያን፣ ግብፅንና ኦሮሞን የኩሽ ዘርነት ሥነ ልሳናዊ ፍንጭ ለመስጠት ይመስላል። በኦሮምኛ "ኑ" ማለት እኛ፣ "ቢያ" ማለት አገር፣ "ኡመ" (ኡመተ) ሕዝብ ወይም "ኡመ" አምላክ ማለት ነው። ስለኾነም ኑቢያም ኢትዮጵያ ነበረች ለሚለው መላ ምቱ (hypothesis) "መረጃ" መስጠቱ ይመስላል።

[5] መኔስ ከክርስቶስ ልደት በፊት ወደ 3,100 ዓመት ገደማ ደቡቡንና ሰሜኑን ግብፅ በአንድ መንግሥት ሥር የገዛው ንጉሥ ሲኾን ዳግማዊ ራምሴስ ከክ/ል በፊት በ13ኛው ምዕተ ዓለም ኑቢያን እና ሊቢያን በግብፅ ሥር ጠቅልሎ የገዛ፣ እስከ ጥንቷ ፍልስጤም እና ሶርያ ወርሮ ያስገበረ የግብፅ ገናና ንጉሥ ነበረ። ፒያንኪና የልጅ ልጁ ሻባካ The Kindgdom of Kush (የኩሽ ግዛተ ነገሥት) በሚል የምትታወቀው ኑቢያን ከክ/ል በፊት በ8ኛው ምዕተ ዓለም አካባቢ የገዙ ሲኾን እነሱም የግብፅን አገዛዝ በመገርሰስ በተራዋ በኑቢያ ሥር እንድትተዳደር ያደረጉ ኃያላን ነገሥታት ነበሩ (ተክለ ጻድቅ መኩሪያ፣ 1950 ዓ/ም)። ኢዛና ከክርስቶስ ልደት በኋላ በ4ኛው ምዕተ ዓለም አክሱምን የገዛ ንጉሥ ሲኾን እሱም *ካሱ* (ኩሽ) እና *ኖባ* (ኑቢያ) የተባሉትን ወርሮ የሜሮዌን ግዛት ያንኮታኮተ ዝነኛ ንጉሥ ነበረ (Phillipson 2012 እኀአ፣ ገጽ 61 እና 76)። *ካሱ* እና *ኖባ* የቦታ ብቻ ሳይኾን የአካባቢው ሕዝብ መጠሪያም ሳይኾኑ አይቀርም።

ክብርና ሞገስ የምትጋራ፣ በተአምራዊ ትሩፋቶቿ የምትወደስ፣ የምትቀደስና የምትመለክ ናት። ዐባይን ለዚህ ያበቃት በዋናነት ካመት ዓመት በውሃዋና በደለሏ በምታፈራው ምርቷ ከትውልድ ትውልድ ቀልባ ማኖሯ ነው። ለዚህም ነው ገጣሚው "በአዝርእት አበቅቴሽ ሲታጠን" የሚላት፡-

የእጅ ማስነሳሽ በረከት
ግብርሽ ከአድማሳት ሲከተት
መንጣለያሽ ከዕለት ዕለት
መሻገሪያሽ ካመት - ዓመት
በመስዋዕት ሲወድቅልሽ
በዝማሜ ሲፈስልሽ
በመመለክ በመመስገን
ጽላትሽ ከዘመን ዘመን
በአዝርእት አበቅቴሽ ሲታጠን
አቤት አባይ ላንቺ መገን (ገጽ 154)

ምጡቋና ጥበበኛዋ ዐባይ በረቂቅነቷ ምንነቷ በቀላሉ የማይታወቅ አድርጎም ይሥላታል፡-

አባይ ታላቅ-ቅድመ-ተስፋ
የኪነት ጉባኤ አልፋ
ረቂቅ አባይ ያንቺ መገን
ምጥቀትሽ አይተነተን (ገጽ 154)

ኾኖም ገናና ታሪኳን መርምሮ የሚያሳውቅ ጠፍቶ ዘመን እንዳጠላባት ተራኪው በቁጭት ያወሳል፡-

የመጽሐፈ-ሙታን ዜና አድርጎሽ ቅድመ-ገናና
ዛሬ ወራቱ ራቀና
ምድረ-ዓለም ያንቺን አድናቆት
ፈለጉን መሻት አቅቶት
ታሪክ ወሮታሽ ጠፍቶበት
ትላንት በባዕድ ጩኸት
ዛሬም ባላዋቂ ሁከት
ቋንቋ ለቋንቋ ቢራራቅ
የቅድሚያሽ ንድፍ ላይፋቅ ... (ገጽ 155)

ይህቺ ግሪክ፣ ፋርስና ባቢሎን ከጥበቧ ሳሎን ጥቂት ጨልፈው ቀዱላት የተባለላት ዐባይ ዛሬ ታሪኳ ስለ ደበዘዘ እና የጥንት ገናናነቷ ስለ ተዘነጋ አዲሱ ትውልድ "የጥንቷ ዐባይ እንዴት ትሆን" ብሎ መጠየቅ እንዳለበት ግጥሙ ያሳስባል። ኾኖም "የቅድመ ታሪክሽ ጥርጊያ/ ከደም-ቢያ እስከ ኑ-ቢያ" በማለት የሥልጣኔውን ሥርወ ግንድ ከኢትዮጵያ ጋራ ለማስተሳሰር ቢጥርም የዐባይ ሥልጣኔ ከጣና ወጥቶ ካርናክ እስኪደርስ ዛሬ በምናውቃት ኢትዮጵያ ውስጥ የተወውን አሻራ በቆረቆረው ከተማ፣

ባቋቋመው ቤተ መቅደስ፣ ወይም ባፈለቀው ጥበብ ግጥሙ አያሳየንም። የሚዘረዝራቸው አማልክት (ራህ፣ ጣህ፣ አሞን፣ አቴስ፣ ኦሩስ) ምንጫቸው ግብፅ፣ የሚዘክራቸው የሥልጣኔው መዲናዎችና መገለጫዎች አንድም የግብፅ (ቴብስ/ልቅጾር፣ ሜምፊስ፣ ካርናክ፣ አቡ-ሲምቦል፣ መጽሐፈ ምውታን፣ የጊዜ መለኪያ፣ ሥነ ፈለክ)፣ አለዚያም የኑቢያ/ሱዳን (ኡሙ-ዱርማን፣ ሜሮዌ) መኾናቸውን ከታሪካቸው እንገነዘባለን። ኑቢያና ግብፅ በሥልጣኔ፣ በባህል፣ በእምነት፣ በታሪክ የተሳሰሩትን ያህል ከኢትዮጵያ ጋራ ያላቸው ዝምድና በግጥሙ ውስጥ ጎልቶ አይታይም፤ ጥቁር ዐባይ የሥልጣኔያቸው ዋናው መሠረት መኾኑን፣ የኩሽ ዝርያ/ቋንቋዎች ያላቸው መኾኑን ካልቆጠርን በስተቀር። "የዓለም ሥልጣኔ ምስማክ" የተባለለት ዐባይ ለፈለቀበት አገር (ደም-ቢያ?) ጥንትም ኾነ በተገጠመለት ዘመን ምን አተረፈለት? የትኛውን የጥበብና የሥልጣኔ መገለጫ አስገኝቶለት አቆየን? ለሚሉት ጥያቄዎች ግጥሙ በቂ ፍንጭ አይሰጥም — ታሪክ የዘከረው የኑቢያ ሥልጣኔ በስመ ኩሽ የኢትዮጵያም ሥልጣኔ ነበረ ካልተባለ በስተቀር።[6] የጥቂት ቃላት የድምፅ መመሳሰልም ከግብፅ ጋራ በዘር መዛመዳችንን አያረጋግጥም። ጸጋዬ "ቅኔ መወድሱን" የተቀኘው ከቴብስ ከተማ ኾኖ በታሪክ መነጽር ከክርስቶስ ልደት በፊት ብዙ ምዕተ ዓመታት ቀድሞ ወደ ነበረው ጥንታዊ የኑቢያና የግብፅ ሥልጣኔ እያማተረ ነው። ዐባይን ከኢትዮጵያ ምንጭነቱ ባሻገር ዛሬም ጥንትም ካለውና ከነበረው ከሐበሻ ሕዝብ የኑሮ ዘዬና ከአገሩ ገጸ ምድር አንጻር ማየቱን ግጥሙ አያረጋግጥልንም። የግጥሙ ዐባይ በዋናነት ከሐበሾች ድንበር ባሻገር የሚገኘውና ለሱዳንና ለግብፅ የምንጊዜም ባለወሮታ የነበረው የጥንቱ ዐባይ ነው።[7]

በጸጋዬ ግጥም ታላቅነቱና የሥልጣኔ ምንጭነቱ የተወደሰለት ዐባይ በስተኋላ ብቅ ባሉት ወጣት ገጣሚዎችም ካለፍ አገደም ተስተጋብቶለታል። ለምሳሌ የአሰፋ ጉያ "አባይና ቴቬረ" (በ1983 ዓ/ም በሮም ተደርሶ በ1984 ዓ/ም የታተመ) የዐባይን ታላቅነት በርዝመቱ፣ በታሪክ ቀዳሚነቱ፣ ባለብዙ ገባሮች እና የቀደምት ሥልጣኔ መሠረት መኾኑን በመግለጽ እንዲህ ይክበዋል፦

[6] ተክለ ጻድቅ መኩሪያ (1950 ዓ/ም) በዋናነት የፈረንሳይ አርኪዎሎጂስቶችን ዋቢ በመጥቀስ የጥንታዊቷ ኢትዮጵያ ግዛት ኑቢያን የሚያጠቃልል እንደነበረና ግብፅን በጦር ኃይል አንበርክከው የገዙትና መልሰውም የገነቧት ኃያላኑ የኑቢያ ነገሥታት (ፒያንኪና ሻባካ) ኢትዮጵያውያን እንደ ነበሩ ይዘክራል። ለስያሜው መነሻው እንደ ሆሜርና ሔሮዶቱስ የመሳሰሉት የግሪክ ጸሐፊዎች ከሜዲተራኒያን ባሕር በስተደቡብ በዐባይ ተፋሰስ ውስጥ የሰፈሩትን መልከ መልካም፣ ቁመተ ለግላጋ፣ ምግባረ ሰናይ በሚል ያሞካሿቸውን ጥቁር ሕዝቦች "ኢትዮጵያውያን" ብለው መጥራታቸው ነው። ጸጋዬ "አባይ"ን የደረሰው ይህን ትርክት ታሳቢ አድርጎ ከኾነ የኑቢያን የታሪክ ገድል ለዛሬይቱ ኢትዮጵያም በማጋራት ታሪኳን መካቡ ይኾናል። ጥንታዊያኑ ግብፆች በጊዜያቸው ኑቢያዎችን "የደቡብ ምድር ኩሽ" ብለው ቢጠሩም አብዛኞዎቹ የኩሻዊ ቋንቋዎች ተናጋሪዎች በአሁኑ ጊዜ የሚገኙት ሱዳን፣ ኤርትራ፣ ኢትዮጵያ፣ ጂቡቲ፣ ሶማልያ፣ ኬንያና ታንዛንያ ውስጥ ነው።

[7] ጸጋዬ በእንግሊዝኛ እጎአ በ1997 የደረሰው "Nile" የተሰኘው ግጥም ከአማርኛው "አባይ" ግጥሙ በብዙ መልኩ ይለያል። በእንግሊዝኛው ግጥም ውስጥ ተናጋሪዋ ኢትዮጵያ ናት፤ ዐባይም ጥሪቷን በየቦታው የምትዘራው ከርታታዋ ልጇ ናት፤ ምንም እንኳን ኹለቱን አንዳንዴ ግጥሙ ቢያደበላለቅም። በዚህ ግጥም ውስጥ የግብፅና የኑቢያ የሥልጣኔ መገለጫዎች አይቀርቡም። ትኩረቱ ኢትዮጵያ በዐባይ አማካኝነት ለግብፅ፣ ለሱዳን፣ ለመካከለኛው ምሥራቅ፣ ለአፍሪካና በአጠቃላይም ለዓለም ባደረገቻቸው አስተዋጽዖዎች ላይ እና ዓለም ዛሬ ይህን ውለታዋን ያለማወቁ ላይ ነው። የዐባይ ወንዝ በለገሰው በረከት አሁንም በግነት ቢወደስም የተናጋሪዋ ድምፀት ግን የዚህ ኹሉ በረከት ምንጭ እኔ መኾኔ እንዴት ተዘነጋ ዓይነት እሮሮ ነው።

አባይ ረጅሙ
የታሪክ ቅድሙ
የወንዞች ውህዱ
የስልጣኔ አሀዱ፤ (ገጽ 45)

ኾኖም በከተማው "ዱራዱር" (ሮም) ውስጥ የሚጎማለለው ቴቬረ ያለቦታው የተገኘ ይመስል፡-

ቴቨረ ዞራዞሩ
የከተማ ዱራዱሩ
መሆን ሲገባው ያንተ ገባር
እንዴት?
እንዴት ደፈረህ ጃል??? (ገጽ 45)

በማለት ሮማን በሚያክል ታላቅ ከተማ ውስጥ የቴቬረ ወንዝ ከዐባይ ተነጥሎ ብቻውን መንፈላሰስ የዐባይን ገናናነት የተሻማ ስለ መሰለው እንዴት ለዐባይ ሳይገብር ቀረ በሚል ቁጭቱን ይገልጻል።

የመስፍን ወልደ ማርያም "የበረሃው ጌታ" (2005 ዓ/ም የታተመ) ከላይ እንደቀረቡት ግጥሞች በአብዛኛው ለዐባይ አድናቆቱን የሚገልጽ ቢኾንም የዐባይ ባሕርይ ምሥጢራዊ፣ በተቃርኖዎች የተሞላ አያዎ (paradox) ነው። ተራኪው የዐባይን ሩጫ ምሥጢር ምንነት ሲጠይቅ ያባይ መልስ እንቆቅልሽ ዓይነት ነው። ዐባይ ያን ሁሉ በረሓ አቋርጦ፣ አሸዋ ምሶ፣ እያጓራ፣ እያቅራራ፣ የሚንደረደረው ለምንድነው? በሚል ሲጠይቀው

"ሁሉንም ጥሻቸው ትሩፋት ሠርቼ
ኮርቶ ለመንጋለል ውቅያኖስ ገብቼ
ለመጥፋት ለሕይወት
ሕይወት ለማበርከት!" (ገጽ 114)

በማለት የተቃርኖ መልሶቹን ይሰጠዋል። ያባይ ትልቅነትም ለመነጨበት አገር ሳይኾን በረሓ ለሚኖሩት ባዕዳን ነው። ተራኪውም ዐባይን በኢተጠየቃዊ ተግባሩ ይታዘበዋል፡-

የሕይወት እንጀራ የማያልቅ የሚፈስስ
የራሱን አራቁቶ ሌላውን የሚያለብስ፤
ወደላይ አትወጣ፤ ጉዞህ ወደታች ነው፤
ያንተ ትልቅነት እዚህ ላይ ነው ያለው! (ገጽ 114)

ይህ የዐባይ በአገሩ ኪሳራ ለባዕዳን ቸርነት ተራኪውን አያስቆጨውም፤ እንዲያውም ያወድሰዋል፡-

አንተ ድንግል ጉልበት
የኢትዮጵያ ትምክህት
የምድረ ግብፅ ሕይወት
የሱዳን አለኝታ
የበረሃው ጌታ! (115)

ዐባይ ግን ድንግል ጉልበቱን ባገሩ ሳያስነካ፣ ላገሩ መመኪያነቱን ሳያሳይ ድንበር ጥሶ፣ በረሓ አጠጥቶ ለባዕድ በረከቱን ያለማቋረጥ ይለግሳል። ስለዚህ የኢትየጵያ ትምክሕትነቱ ምኑ ላይ እንደ ኾነ ግጥሙ በቀጥታ አይነግረንም። ያባይ ድንግል ጉልበትነት በኢትዮጵያ ውስጥ የሚታየው፡-

እያጓራ ሲኻንደንድ
እያንከታከተ ሲወርድ
ያገኘውን ሲጠርግና ሲንድ (ገጽ 115)

ስለኾነ ይሄ ያልተገራ ጉልበቱ በአፍራሽነቱ ነው የተገለጸው። ስለዚህ አንባቢው መመለስ ያለበት ጥያቄ ዐባይ ድንበር አቋርጦ ለግብፅ ሕይወት፣ ለሱዳን አለኝታ መኾን ከቻለ ለአገሩስ ትሩፋቱን እንዲለግስ ይኽን ድንግል ጉልበቱን እንዴት እንጠቀምበት፣ እንዴትስ ላገሩ የጥፋት ኃይል ሳይኾን፣ የበረከት ምንጭ እናድርገው የሚል ነው። በመኾኑም ግጥሙ ያባይ ለኢትዮጵያ ትምክሕትነት በተግባር የተተረጎመ ሳይኾን ዕምቅ ዐቅም ነው የሚል አንድምታ አለው። መመኪያነቱን ከተለያየ አንጻር መተርጎም ይቻላል። የትምክሕት ምንጭነቱ ከታሪክ እንደምንገነዘበው ዐባይ የሱዳንና የግብፅ ሕይወት መሠረት መኾኑን የተረዱ ነገሥታት (ለምሳሌ፣ አፄ ዳዊትና አፄ ዘርዐ ያዕቆብ) የጥቁር ዐባይ ምንጭ ኢትዮጵያ ከመኾኗ አንጻር ወንዙን ለመቀልበስ መዛታቸው (መርሻ 2021 እ.ኣ፣ ገጽ 150-64፣ 210-12፤ ታደሰ 1972 እ.ኣ፣ ገጽ 256፣ 262) ለኹለቱ የዘላለም ሥጋት፣ ለኢትዮጵያ ደግሞ ማስፈራሪያ መኾኑ ሊኾን ይችላል። ሌላው የትምክሕትነቱ ማሳያ ለሱዳንና ለግብፅ ወንዙ ከሰጠው ትሩፋት አንጻር ኢትዮጵያም ዐባይን በሰፊው በማልማት ልታገኝ የምትችለው አገራዊ ጥቅም ነው። ግጥሙ የትኛውን ትርጓሜ እንዳዘለ ላንባቢው ስለተወ መፈታት ያለበት እንቆቅልሽም ይኸው ምሥጢራዊ አቀራረቡ ነው።

የዐባይ ትልቅነት ለደገኛው አገር ሳይኾን ለታችኞቹ የቆላ አገሮች ነው። በርእሱ እንደ ጀመረው ግጥሙን ሲደመድምም ከግብፅና ከሱዳን ጋራ አያይዞ ነው ዐባይን “የበረሃው ጌታ!” በሚል የሚገልጸው። ይኹን እንጂ በታችኞቹ አገሮች ዐባይ የታላቅነት ክብር የተጎናጸፈው ተራራቸውን ቦርቡሮ፣ ዐፈራቸውን ጠራርጎና ሜዳ ሸንተረራቸውን አራቁቶ፣ ሕዝባቸውን በድርቅና በረኀብ ቀጥቶ አይደለም። ከደጋው አገር ባመጣው ውሃ በረሓቸውን አጠጥቶ፣ ባግበሰበሰው ደለል ሜዳቸውን ልምላሜ አልብሶ፣ ለሕይወታቸውና ለብልጽግናቸው መሠረት ገንብቶ ነው። ይህ ደግሞ ወንዙ በተፈጥሮው ቁልቁል ስለ ተጓዘ ብቻ እንዳልኾነ ከፈርዖን ጊዜ ጀምሮ ታሪክ የዘከረው ነው። ስለዚህ ግብፅና ሱዳን እንዴት ቢገሩት ዐባይን የሕይወት ሲሳይ አደረጉት? ኢትዮጵያስ ምን ብታደርግ የዐባይን ታላቅነት ለአገሯ ሕዝብ ታረጋግጣለች? በአንባቢው መመለስ ያለባቸው ጥያቄዎች ናቸው። (ግጥሙ የተደረሰው ከሕዳሴው ግድብ ጥንስስ በፊት ይመስላል።) የግጥሙ የማይጣጣሙ

ባሕርያትን አደራርቦ ማቅረብና ዐባይን ያለመውቀሱ ምሥጢር በእነዚህ ጥያቄዎች ዙሪያ ይሽከረከራል። የግጥሙ ኪናዊ ኃይልና ውበትም ያንባቢን አእምሮ ኮርኳሪነቱ፣ አመራማሪነቱ ነው።

በመስፍን ግጥም ውስጥ ስለ ዐባይ ውበት "አንተ የውበት ኃይል፤ አንተ የኃይል ውበት" በማለት አድናቆት ሲቀርብለት ውበቱ ያለው ድንግል ጉልበቱና ግርማ ሞገሱ ላይ ነው። ሌሎች ግጥሞች ይህን አይጋሩም። ለምሳሌ በአቤ ጉበኛ "ጢስ ዐባይ" (1965 ዓ/ም) ውስጥ የዐባይ ውበት የሚገለጸው በፏፏቴው ነው። ግጥሙ የፏፏቴውን ትነት ያለእሳት እንደሚንፎለፎል ጢስ፣ የቀስተ ደመናውን ኅብረ ቀለማት ደግሞ እንደ መለኮታዊ የተስፋ ፋና አድርጎ ይሥለዋል፡-

እዩት ጢስ ዓባይን ሲሠራ ታምር፣
የሚፈላበት ድስት እሳቱም ሳይኖር፣
ወሀ ጢስ ሲተፋ ከዳር እስከዳር!
እዩት ጢስ ዓባይን የተስፋውን ፋና፣
ምልክቱን ሲገልጥ በቀስተ—ደመና! (ገጽ 31)

አቤ ተፈጥሮአዊውን በውሃ ግጭት የተፈጠረ ትነት ያለእሳት ከፈላ ድስት የወጣ ትነት አስመስሎ ነው የአስደናቂ ተአምር መገለጫ የሚያደርገው።

በአደም ሁሴን "ብቻዬን አይደለሁም" (2007 ዓ/ም) የዐባይ ፏፏቴ ከሀገርኛው ሙዚቃና ውዝዋዜ (ያሬዳዊ ዜማ፣ እስክስታ) ጋራ ተመሳስሎ፣ ድምፁ በሀገርኛ የሙዚቃ መሣሪያዎች (ከበሮ፣ እንቢልታ፣ ክራር፣ የእረኛ ዋሽንት) ታጅቦ፣ የቀስተ ደመናው ኅብረ ቀለም በዶርዜ ጥበብ ደምቆ፣ ሽታው በሐረር ሉባንጃ ታውዶ፣ በበረሓ ዕጣን ታጥኖ ለአድናቂው የብቸኝነትን ጥላ የሚገፍ ታማኝ ወዳጅ ኾኖ ነው የተሣለው። በግጥሙ ውስጥ ዐባይ ከውበት መገለጫነት ያለፈ ፋይዳ አልተሰጠውም። አቀራረቡ የተለያዩ የስሜት ሕዋሳትን (ውዝዋዜን፣ ጥዑመ ዜማን፣ ማራኪ ቀለማትን፣ የሽታ መዐዛን) ቀስቃሽ ኾኖ ነው አድናቆቱን የሚያጋራን።

የመላኩ አላምረው "ግሽ ዓባይ ጠብቂኝ" (2009 ዓ/ም) የሽገሩ ሰውዬ ግሽ ዐባይ ላለችው ፍቅረኛው ናፍቆቱንና ውዳሴውን የሚያኾጎደጉድበት ነው። በዚህ ውዳሴው ስለ ዐባይ የተለየ ምስል ይሰጠናል። ግሽ ዐባይ የታላቁ ወንዝ ምንጭ ብቻ ሳይኾን ጥዑመ መዐዛና ፈዋሽ ጠበል የሚፈልቅበት፣ ቅኔ የሚፈስበት፣ ውቦች የሚመነጩበት፣ የገነት በር፣ የደግ ሕዝብ፣ የጀግና አገር ኾኖ ተሥሏል፡-

መውጫው የገነት በር፣ ምንጩ ድንቅ ፈዋሽ፤
ሰማያዊ ምሥጢር፣ ለምድራችን አድራሽ።
ስሙ የገነነ፣ ግርማው የገዘፈ፤
ከሯጭም የሚሮጥ፣ ከአክናፍ የከነፈ።
ግዮን የተባለው፣ የወንዞቹ ንጉሥ፤
ከግሽ ሚወለድ፣ በአካል በመንፈስ።
ምስከር እንቁጠር?

የሰው ልጅ ከገነት፣ ሳይባረር ገና፤
መወለድ ሳይጀምር፣ ውሃ ከደመና።
በምድርም ሆነ፣ በሰማይ በሙብረር፤
ለኖሩት ፍጥረታት፣ መጠጥ ስለነበር።
ከአዳም ጀምሮ፣ ይመሰክራሉ፤
"የግዮን ማህፀን፣ ይህ ግሽ ነው እያሉ"። (ገጽ 113-114)

ስለዚህ የዐባይ ታላቅነት የውሃ አባት መኾኑ፣ የመጀሪያውን የሰው ዘርም በገነት ማጠጣቱ ነው ይለናል። ገነትና ምድርንም አስተሳስሮ የግዮን ከኢትዮጵያ መመንጨትም የሀገሪቱን ቅድስና ማሳያነቱንና ይህም በመጽሐፍ ቅዱስ የተመሰከረላት መኾኑን ግጥሙ በሌሎች ስንኞቹም ይነግረናል። በኦሪት ዘፍጥረት (ም.2፣ ቁ.10-13) ትርክት ላይ በመመሥረት የወንዙን ከገነት መፍለቅና አዳምና ሔዋንን ያጠጣ መኾኑን በመዘከር ዐባይን መንፈሳዊም ዓለማዊም ልዕልና ያጎናጽፈዋል። ዐባይ የቅኔ ብቻ ሳይኾን የፍቅርም መፍለቂያ ስለመኾኑ ከግሽ ዐባይዋ ጉብል ተፈቃሪነት እንረዳለን፡-

ከፈለገ ግዮን ከግሽ ተራራ ሥር፤
እየዘረፍን ቅኔ እየቀዳን ምስጢር፤
መኖር ይሻለናል፣ መልሽኝ ከሸገር፤ (ገጽ 116)

ከቀደሙት ግጥሞች በተለየ ከሱዳን ኾኖ ስለ ዐባይ አድናቆት በተደጋጋሚ የሚገለጽባቸው ደግሞ የሰይፉ መታፈሪያ ግጥሞች ናቸው። በዚህ ጽሑፍ ውስጥ የሚተነተኑት አስር የሰይፉ ግጥሞች በሙሉ ደራሲው በሱዳኑ የካርቱም ዩኒቨርሲቲ ውስጥ በዘመነ ደርግ ከ1967 ዓ/ም እስከ 1971 ዓ/ም በሚያስተምርበት ወቅት የተደረሱ መኾናቸውን ደራሲው በ2000 ዓ/ም ባሳተመው የግጥም መድበሉ መግቢያ ይነግረናል። "ባባይ ወንዝ ዳር" የተሰኘው ግጥሙ ስለ ዐባይ የሚተረክልን ደራሲው በዚያው ከተማ በወንዙ ዳር ሲንሸራሸር ከነበረው ዕይታ አንጻር ነው። የዐባይ ጉዞ እንደ ጌታ ተንፈላስሶ ነው፤ ምክንያቱም የሦስት አገር ነገሥታት አቻ ኾኖ ነው የሚጓዘው፡-

መሠ-ሠ-ሠሥ
ቅጠላ-ቅጠል መጣሰስ
ዐባይ ድፍርስርስ
ሥልጡን ንጉሥ፡-
ዐዜን
ፈርኦንን
እና ማሕዲን
በረኻ ለበረኻ ተናግዶቱን። (ገጽ 140)

ተራኪው የዐባይን ዘገምተኛ ጉዞ ተመልክቶ ሲሰናበተውም "እንደምመጣ ተመልሼ / ዐባይን ስሙን አንግሼ" በሚል አሻሚ አባባል ነው። ይህም አንድም ባሙቱ (በክረምቱ) ውሃው ሲሞላና ኃይሉ ከምንግዜውም በላይ ሲጨምር፣ እንደ ታቦት ለንግሡ እንደሚመጣ ማለቱ ሊኾን ይችላል። ወይም

ደግሞ ዐባይ በነዚህ በረኸኛ አገሮች ተገርቶ ለልማት መዋሉን፣ ከጥፋቱ ትሩፋቱ የላቀ መኾኑን፤ ሕይወታቸው በዐባይ ጸጋ ላይ በመመሥረቱም እውነተኛ ገዣቸው ስለኾነ እንደገና ዝናውን ለመዘከር እንደሚመለስ መግለጹ ሊኾን ይችላል። “ተናግዶቱን” የሚለው ቃልም አሻሚ ነው። በአንድ በኩል ከደጋው እስከ በረሓው ዘልቆ መንጎዱን፣ ያለማቋረጥ መጓዙንም ማለት ሊኾን ይችላል። በሌላ በኩል ደግሞ መነጋገድን፣ ልውውጥን ስለሚያሳይ ደገኛው ንጉሥ (አፄ) ጳጳስ ወስዶ በምትኩና በዋናነት የዐባይን ውሃና ለም ዐፈር ለሱዳንና ለግብፅ ሲሰጥ (ኃይሉ 2001 ዓ/ም፣ ገጽ 200-02) እነዚህ በረኸኞች ደግሞ ከዐባይ ልማት በተገኘው ምርት ይነጋገዳሉ ማለትም ሊኾን ይችላል። ከደገኛው አገር አኳያ ካየነው ደግሞ ዐባይን ስሙን አንግሼ እመለሳለሁ ሲል ዐባይ ባገሩም ሠልጥኖ፣ አገር ማራቆቱን ትቶ፣ ለሕዝቡ ሲሳይና የኑሮው ዋልታ በመኾን በሕይወታቸው ላይ ሲገንን ገጣሚው ወደ አገሩ ተመልሶ ዐባይን እንደሚጎበኘው ቃል መግባቱም ሊኾን ይችላል። ግጥሙ ፈርጀ ብዙ ትርጓሜ ቢኖረውም በዐባይ ላይ ግልጽ እሮሮ አያቀርብም።

የሰይፉ “ዐባይ መልካ ለመልካ” እንደ በፊተኛው ግጥም የዐባይን ቀሰስተኛ የበረሓ ጉዞ ቢገልጽም አጽንዖቱ በዚያ የፀሐይ ቃጠሎ እንዴት ከደጋው ባመጣው ውሃና ዐፈር በረሓውን በመስኖ እያራሰና እያደለበ እንደሚያለመልም ማሳየቱ ላይ ነው።

2. **ዐባይ፦ ስደተኛው የበረሓ ሲሳይ**

የተወሰኑት የሰይፉ መታፈሪያ የዐባይ ግጥሞች ደራሲው ባለበት ኅብረተሰብ ውስጥ ከሚሰማው የባይተዋርነት ስሜት የሚፈልቁና ይኸንኑ መንፈስ ለዐባይም የሚያጋሩው ይመስላሉ። ለምሳሌ “ይድረስ ላባይ ፉዋፉዋቴ” በሚለው ግጥም ተራኪው ጀልባይቱ ሽቅብ ዐባይ ወደመጣበት አቅጣጫ በንፋስ ተገፍታ ሲትነጉድ ሲያያት ዐባይ ወደመነጨበት ደጋው አገር ትዘልቅ ይኾን የሚል ሐሳብ ይመጣበታል። እናም ላገሩ ከፍተኛ የናፍቆት ሰቀቀን ስላደረበት ጀልባዋን የሚማፀናት ሰላምታውን ለሰዉ ብቻ ሳይኾን ባገር ምድሩ ላለው ኹሉ እንድታደርስለት ነው፦

ከምንጩ ስትደርሺ
ካባይ
እባክሽን ሳሚልኝ
ዐባይ ፉዋፉዋቴውን
ሰዉን!
እንስሳ - አራዊቱን
ሣር - ቅጠሉን!
አገር - ምድሩን
ካልቆለኛ ብለሽ
ከደገኛ
አልቆላው ቆለኛ
ላገሩ ሰው ባይተዋር። (ገጽ 267-68)

ይሄ ደገኛነቱ ካልለቀቀው የቆላ ነዋሪ የፈለቀው የባይተዋርነት ስሜት "ዐባይ ዐባዬ" በሚለው ግጥሙ ደግሞ ከራሱ አልፎ ወደ ዐባይ ይጋባል። "ዐባይ - ዐባዬ! -"ዐባይ - ዐባዬ! -" የሚሉት ስንኞች የልቅሶ እንጉርጉሮ ቅርጽ የያዙ የተራኪውን ሐዘን የሚያንጸባርቁ ናቸው። በዚህ ግጥም ዐባይ ከአገሩ ተሰዶና በሰው በረሓ ሀብቱን አስረክቦ የደኸየ የተራኪው ወዳጅ ኾኖ ተሥሏል፡-

ዐባይ - ዐባዬ! -
ዐባይ! - ዐባዬ - ውኀ!
በረሃ ወርዶ ደኀ
ከደጋ ወራጅ
    ወዳጅ
ካርቱም ያገኘሁት ያገሬ ልጅ። (ገጽ 246)

"ዐባይ በረኀኜ" በሚለው ግጥሙ ደግሞ ዐባይ ለምን እንደሚኮበልልና በሰው በረሓ የደረሰበትን ጉስቁልና ባገሩ ከነበረው ግርማ ሞገስ ጋራ እያነጻጸረ ያቀርበዋል። የጥቁር ዐባይን በክረምቱ የውሃ ሙላት (ከቃላቱ የትናጋ ድምፆች ድድርነትና ድግግሞሽ ጋራ በማመሳሰል) ከደጋው ቁልቁል እየተንደረደረ መውረድ ከጥቁር ዝሆን አረማመድ ጋራ ያመሳስለዋል፡-

ጥቁር ዐባይ ጥቁር
  ዝሆን
ዝሆን ከባድ
ቁልቁለት ሲወርድ
በገተር ገተር
ከደጋ አገር
ተወርወር ወርወር (ገጽ 250)

ዐባይ ከደጋው ሲነሳ ባዶ እጁን አይደለም፤ በጎ ሥርቶም አይደለም ለመኩብለል የበቃው፡-

እርስ በራሱ እየተናዳ
የውሃ ናዳ
ገደቡን ገርሰስ
ዐፈሩን ደርመስመስመስ (ገጽ 250)

ይህን ያገር ሀብት አግበስብሶ ወስዶ ለበረሓው ያራግፍና ተራኪው "ÅÑ–@ uqL mM ¨</ Ø`eU ¾K¨</ ¾T>Ypuƒ" እንዳለው ባላደገበት ቆላ ስሜቱን በሳቅ የማይገልጽ ጭምት ስደተኛ፤ ደገኛ ባህሉን በማያውቅለት ቆለኛ ዘንድ ደግሞ ያመጣውን ሀብት አስረክቦ ሌጣውን ስለቀረ እንደ ሞኛ ሞኝ መቆጠሩን ግጥሙ ይነግረናል። ይባስ ብሎም ከደጋው ባግበሰበሰው ዐፈር ገዝፎና ጠቁሮ እንደ ዝሆን እየተንደረደረ እንዳልመጣ ሁሉ በረሓውን ሲያቋርጥ ሥጋው በአሸዋው ተበልቶ፣ አካሉ በሐሩሩ ቀልጦ በዐፅሙ የቀረበትን ምስል በከችአርጌ ዘይቤዎችና በአስተጋቢ ድምፆች (onomatopoeia) ግጥሙ ይሥልልናል። በመስፍን ወ/ማርያም ግጥም የተነገረን ያባይ ለሰው

ሕይወት ሰጥቶ የራሱን የማጥፋት አባዜ በሰይፉ ግጥምም ይደገማል። በዚህኛው ግን ሞቱ የሚጀምረው ገና በበረሓ ጉዞው ላይ እያለ ነው፡-

ዐባይ አቋዋርጦ
        በረኀ
በሐሩር ቀልጦ
አካሉ አልቋዋል፤
ደሙ መጡዋል
ባጽሙ ነው ያለ
እየኼድኩ ነው ያለ
መቃብሩን እያሰላሰለ
        ሜዲተራኔን፡-
እሱው ሙዋች መኾን
እሱው ቀባሪ
ባሕርን ተቀላቅሎ አዳሪ። (ገጽ 251)

ይህን የዐባይን ራሱን በራሱ የማጥፋት ዕጣ ፈንታ በማየቱ ገጣሚው "ዋ! እኔን/ ዐባይ ዋ!/ ዋ! እኔን" በማለት ይጸጸታል፤ አስከሬን ሸኚ ሐዘንተኛ ይመስል ዐይኑን እንባ እየቀረቀረው። አቀራረቡ አንባቢው የገጣሚውን የሐዘኔታ ስሜት እንዲጋራና የዐባይ ዕጣ ፈንታ ይሄ ሊኾን አይገባም፤ ከለመደው ደጋ መውጣት አልነበረበትም ብሎ እንዲያስብ የሚገፋፋ ነው። የነዚህ የሰይፉ ግጥሞች የስደተኛ ምስሎች የሚሽከረከሩት በዐባይ ተጓዥነት ዙሪያ ነው።

3. *ቀሣፊው ዐባይ*

እስካሁን በቀረቡት ግጥሞች ለዐባይ የተሰጡት ምስሎች አንድም እንድናደንቀው አሊያም እንድናዝንለት የሚገፋፉን ሲኾኑ በሌሎች የተወሰኑ ድርሰቶች ደግሞ ዐባይ ቀሣፊ ኾኖ ነው የተሣለው። ከነዚህ ውስጥ በአፄ ኃይለ ሥላሴ ዘመን የተደረሰው የሀዲስ አለማየሁ ፍቅር እስከ መቃብር (1958 ዓ/ም) ቀዳሚውን ቦታ ይይዛል። ይህ ልቦለድ ስለ ዐባይ የሚያቀርብልን ምስል እነጸጋዬ ገብረ መድኅን የካቡትን ወሸነኔያዊ (romantic) የዐባይ ሚት (myth) የሚገረስስና በምትኩ መልአከ ሞት አድርጎት የሚሥል ነው። ኾኖም የልዩነቱ መሠረት እነጸጋዬና ሰይፉ ዐባይን በዋናነት ካገሩ ውጪ ሲያዩት እነሀዲስ ደግሞ ዐባይን ባገሩ ውስጥ ነው የሚያዩት።

ገና ከመነሻው ሰብለ በዛብህን ፍለጋ ወደ አዲስ አበባ በምትኮበልልበት ጊዜ ከሦስት ቀን ጉዞ በኋላ የዐባይ በረሓ አፋፍ ላይ ደርሳ ቁልቁል ስትመለከት የሚታያት አስፈሪ ምስል "ያባይ በርሀ የሲኦልን ግርማ ተጎናጥፎ እስሩ ያባይ ወንዝ ያናቱና የጅራቱ መጨረሻ እንደማይታይ ዘንዶ ተጋድሞ" ነው (ገጽ 492)። ሲኦል የማያበራ ስቃይ ቤት ሲኾን ዘንዶም በእግዜር የተረገመው እባብ ተወካይና የሰይጣን ምሳሌ ነው። ፍቅርን ሰንቃ በተስፋ ለምትጓዘው ሰብለ ይህ አስፈሪ ያባይ ምስል መጥፎ ምልኪ ነው። የበዛብህን አዲስ አበባ አለመኖር ዐውቃ እሱኑ ስታሳድድ ጎሐ ጽዮን እንደ ደረሰች ስለ ዐባይ የሚቀርብልን ገለጻ ይኸንኑ ስቃይና ሞትን ያቆራኘ የመከራ ትንቢት ነው፡-

አባይ ለቆላው የመኪና መንገድ ለወንዙ ድልድይ ሳይሰራለት ከጎጃም ወደ ወዳዲስ አበባ ካዲስ አበባ ወደ ጎጃም የሚሄድ መንገደኛ ሁሉ ጎህ ጽዮን ወይም ደጀን እስኪደርስ ድረስ ልክ የመከራ ትንቢት እንደ ተነገረበት ሰው ካሁን አሁን መከራው ደረሰብኝ ብሎ ልቡ እዬፈራና እዬራደ የሚያልፍበት ቦታ ነበር።

አባይ አንድ ሞት ብቻ አይደለም፤ ብዙ ሞት ተሰብስቦ የሰፈረበት ብዙ ስቃይ ብዙ ጣር ተሰብስቦ ያረፈበት ቦታ ነበር!

ባንድ አመት ውስጥ ያባይ ውሀ የሚወስደውን አዞ የሚበላውን ሽፍታ የሚገድለውን እባብ ነድፎት ወይም ወባ አሞት የሚሞተውን ተደብድቦ ወድቆ አውሬ የሚቀራመተውን ልብሱ የሚገፈፈውን ሀብቱ የሚዘረፈውን ይህን ሁሉ ሞት ይህ ሁሉ ጣር መከራው የደረሰበት ቤት መከራው የደረሰበት ቤተ ሰብ ይቆጥረዋል እንጂ ይህን ያክል ነው ሊል የሚችል የለም።

አባይ ውስጥ ተሰብስቦ ከሰፈረው ሞትና ስቃይ የበለጠ ደግሞ ወሬው ያስፈራ ነበር.... (ገጽ 531)

ስለዚህ ከጎጃም ወዳዲስ አበባ ወይም ከዚያ አልፈው የሚሄዱ መንገደኞች ደጀን አፋፍ ላይ ሆነው አባይን ክረምት እንደ ሆነ በጉም፣ በጋ እንደ ሆነ በጭጋግ ተሸፍኖ የሚታወቀውንም ሆነ የማይታወቀውንም ሞትና ጣር ሁሉ በጉያው ሸሽጎ እንደ ሲኦል ንጉስ በሚያስፈራ ግርማ ከላይ እስከታች ተጋድሞ ሲመለከቱት ልባቸው ሲሸበር ይቆይና ወዲያው ከጉሙ ወይም ከጭጋጉ በላይ አሻግረው ሲያዩ እዚያ ከደረሱ ሞቱ ሁሉ፣ ጣሩ ሁሉ ወደ ሁዋላቸው የሚቀር እንጂ ወደ ፊት የማይገጥማቸው ሆኖ ስለሚታያቸው ጎህ ጽዮን በደህና የሚደርሱበትን ዘዴ ብቻ ማሰብ ማሰናዳት ይጀምራሉ። የጉዞዋቸው መጨረሻ ጎህ ጽዮን እንደ ሆነ ሁሉ ምኞታቸው፣ ጸሎታቸው፣ መሰናዶዋቸው ሁሉ እዚያ ለመድረስ ይሆናል.... (ገጽ 531-32)

ይህ ሁሉ የገሃነምና የሰቆቃ፣ የሞትና የጭንቀት፣ የጭካኔና የምዝበራ ምስል ለመንገደኞች የሚከሡተው ያባይ መሻጋገሪያ ባለመበጀቱ፣ በተለይም የመኪና መንገድና ድልድይ ባለመሠራቱ፣ በአካባቢው ለነጋዴውና ለሌላው መንገደኛ ለደኅንነቱና ለንብረቱ አስተማማኝ ጥበቃ ባለመዘጋጀቱ፣ ለታመመው መታከሚያ የጤና አገልግሎት ባለመኖሩ ነው። ይሁን እንጂ ይህ ያባይ ጽልመታዊ ምስል በቀረበበት ዐውድ ውስጥ ዋና ፋይዳው ለዐባይ መሻገሪያ የኹሉናቀፍ ልማት ጥሪ ማቅረብ አይደለም። ገና ዐባይን ሳትሻገር በአፋፉ ላይ የዱር አውሬዎች ሲሳይ ከመኾን ለጥቂት ያመለጠችው ሰብለ ገዷ ለዘለቄታው እንዳልቀና፣ ወደ አዲስ አበባ የምትጓዝበትም ኾነ ከዚያም በጥድፊያ የምትመለስበት ተልእኮዋ እንደማይሳካ መተንበይ፤ በሌላ በኩል ደግሞ የበዛብህን ከአዲስ አበባ የመልስ ጉዞ ዕጣ ፈንታ ተአማኒ ማድረግ ነው። ስንቱን ለስቃይና ለሞት ሲዳርግ የነበረው ዐባይ እሱንም አልማረውምና። "አዲስ አበባ ቆይቶ ወዳገሩ ሲመለስ እግዚአብሔር ይህን መቅሰፍት አዘዘበት!" (ገጽ 536) በማለት ነው አስታማሚዋ ወ/ሮ የሽመቤት የበዛብህን ፍዳ ለሰብለ የሚያወሷት። ሁለቱ ወጣቶች ኮብልለውም እንደ ሌሎች ባለትዳሮች አብሮ የመኖር ሕልማቸውን በመጨረሻው ላይ ያጨናገፈባቸው ዐባይ ነው። ስለኾነም የተዋደዱ ወጣቶች የሚሹትን መደበኛ

የትዳር ሕይወት በመንፈግ ዐባይ የፍቅር፣ የደስታ፣ የደኅንነት መቅሠፍት ኾኖ ነው በልቦለዱ ውስጥ የተሣለው።

በሀዲስ ልቦለድ የተሣለው የዐባይ ጽልመታዊ ምስል በኢሕዴግ ዘመን በተደረሱ አንዳንድ ሥራዎችም ይደገማል። ለምሳሌ የታደለ ገድሌ "ዐባይ ሰይጣን አለ!" (1999 ዓ/ም) በዐባይ ሸለቆ በየጊዜው የሚከሠተው የመሬት መንሸራተትና የድንጋይ ናዳ በመንገደኞች ላይ የሚያደርሰውን አደጋ በሽፍታና በሰይጣን ሥራ መስሎ እንደሚከተለው ያቀርባል፦

> ዐባይ ሰይጣን አለ ነፍስ ገዳይ ሽፍታ፣
> ከገደሉ በላይ በናዳ እሚመታ
>
> ....
>
> ዐባይ ሰይጣን አለ የሚጥል አደጋ
> መንገዱን በናዳ ድንገት የሚዘጋ። (ገጽ 78)

የአንተነህ ግዛው "የዐባይ ልጅ" (2003 ዓ/ም) የተባለ አጭር ልቦለድ ደግሞ ዐባይን በቁም የሚገድል ቂመኛ መለኮታዊ ኃይል አድርጎ ይሥለዋል። ዋናው ገጸ ባሕርይ ወርቁ ለእናቱ አራተኛ ልጅ ነው። ከሱ በፊት የወለዷቸው ሦስቱ ልጆቻቸው ተራ በተራ ስለ ሞቱባቸው እሱን ሲፀንሱ እሱንም ሞት እንዳይነጥቃቸው ለዐባይ ይሳላሉ። ወደ ዐባይ ማዶ ሰፈር የስእለት ልጃቸውን እየወሰዱት ወንዙ ዳር ካለች ዛፍ ሥር ቆመው በያመቱ የገብስማ ዶሮ እና የአረቄ የስእለት ግብራቸውን ለዐባይ ያቀርባሉ። ልጁም እያደገ ሲኼድ በዚህ የስእለት ግብር ይሳተፋል። "እጁን ደም እያጨቀየው ሦስት ጊዜ እናቱን አዙሮ ወደ ዐባይ ዶሮዋን ይወረውራታል። ይሄን ተከትለው እናቱ ለዐባይ ዶሮውን ማወራረጃ አረቄ ይፈነጥቁለታል — ከዓመት ዓመት።" (ገጽ 74) ዩኒቨርሲቲ ሲገባም እናቱ "ዐባይ ያውቃል። እሱ ሰጠኝ፣ እሱ ለወግ አበቃልኝ። መጀመሪያህም መጨረሻህም ዐባይ ነው። ሁሉም በእሱ በዐባይ አምላክ ይሆናል ብለውታል። ሲሸኙትም ከአደራ ጋር ነበር። የዐባይን አምላክ መለማመኑን እንዳይተው።" (ገጽ 74) በዚህ ዓይነት ኹኔታ ወርቁ እናቱ የመከሩትን እየፈጸመ ቆይቶ ዩኒቨርሲቲ የሦስተኛ ዓመት ትምህርቱን እንደ ጨረሰ ክረምቱን ከቤተሰቦቹ ጋራ አሳልፎ ወደ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ሲመለስ አብረውት በአውቶቡስ ዐባይን በመሻገር ላይ ያሉ ወጣት አዛውንቱ ኹሉ ያላቸውን ሳንቲምም ኾነ ብር ወደ ዐባይ ወንዝ እየወረወሩ "ዐባይ አንተ ታውቃለህ!" በማለት ሲማፀኑ ይታዘባል። ወርቁ ግን "ይገርማል... ለበድን ውሃ ከንቱ መስዋዕት..." የሚል ሐሳብ እያሰላሰለ የእናቱን ማስጠንቀቂያ ይዘነጋል። የዐባይ ቆሌ ግን የስእለት ልጁ እንደ ከዳው አልረሳም። እናቱ እንዳሉት ኹሉ ወርቁን በኼደበት እየተከተለው ያቺን ክህደት ያሰበባትን ለጋ አእምሮውን በምሥጢራዊ ስልቱ ያብሰለስለዋል። የናቱን አደራ ሙብላቱ ዩኒቨርሲቲ ድረስ ተከትሎት ወርቁን በፍርሃት ያሸብረዋል። የሰሚስተሩ የፈተና ውጤቱም ያሽቆለቁላል። ይባስ ብሎ አማካሪ መምህሩ የመመረቂያ ጥናቱን ርእስ ችግር ፈቺ አይደለም በማለት ሲጥሉበት የወርቁ አእምሮ ፈሩን መሳት ይጀምራል። ከጓደኞቹም መነጠል ይጀምራል። በመጨረሻ እብደቱ ሲለይለት ራሱን እንደ ዐባይ ቆጥሮ የዩኒቨርሲቲውን ግንብ አትገድቡኝ እያለ የሙጥኝ ይዞ ይስማል። ወደ አራት ኪሎ የነጻነት ሐውልት ሮጦ ደግሞ ለዐባይ የሚገብረው ገብስማ ዶሮ እንዲሸጡለት ሐውልቱ ላይ የተቀረጹትን ምስሎች ይወተውታል። እንደ ታረደች ዶሮ ራሱን ቆጥሮ እናቱ ለዐባይ አረቄውን እንድትረጭ እንደ

ዶሮ ኳከ! ኳከ! ኳ... እያለ ይጮኻል። እነሆም ዐባይ የቀረበትን የስእለት ግብር የእናትዬዋን ተስፋ በመቅሠፍ ይወስዳል። እናቱ እንደተነበዩትም ዐባይ የወርቄ መፈጠሚያውም ይኾናል።

የወርቄ ታሪክ ዐባይን እንደ ምሕረት የለሽ መለኮታዊ ኃይል ቢሥልም የልቦለዱ ፋይዳ ዐባይ በማኅበረሰቡ ሥነ ልቦና፣ በተለይም በዘልማዳዊ እምነት ተኮትኩቶ በታነጸ ሊጋ አእምሮ ላይ ያለውን ግዙፍ ተጽዕኖ ማሳየት ነው። በባህላዊ እምነትና በዘመናዊው ትምህርት መካከል የሚከሠት ሥነ ልቦናዊ ግጭት የሚያስከትለውን አደጋም ይጠቁማል። ለዚህ ጭብጥ ማራመጃ ዐባይ ቂመኛ ተዋናይ ኾኖ ቀርቧል። የወርቄ ወደ ነጻነት ሐውልት መሮጥና ተማፅኖ ከተተበተበበት አጓጉል ባህላዊ እምነትና ተጽዕኖ ነጻ ለመውጣት መሻትን የሚገልጽ ትእምርት ተደርጎ ሊተረጎም ይችላል።

4. መዘዘኛው ዐባይ

ሕይወታቸው በዐባይ በረከት ላይ የተመሠረተው ሱዳንና ግብፅ ከረጅም ጊዜ ጀምሮ የወንዙ ዋና ምንጭ የኾነችውን ኢትዮጵያን በሥጋት ዐይን ሲያዩ ቆይተዋል። የነሱ ቅኝ ገዥ የነበሩት ኃይሎችም ዐባይን ከነምንጩ ለመቆጣጠር ሲያሤሩ ኖረዋል። ስለዚህ በነዚህ ኃይሎች በኢትዮጵያ ላይ ለሚሸረብ ደባ ዐባይ አንዱ መንስኤ ኾኗል (Trimingham 1952, ገጽ 114-122፤ Rubenson 1976, Ch V; Yaqob 2007, ገጽ 224)። ይህን ኢትዮጵያን በማንኛውም ዘዴ አንበርክኮ ወንዙን በብቸኝነት ለመጠቀም የሚደረግ ፍላጎትና ጥረት ሰይፉ መታፈሪያ "ዐባይ — ፈንጂ የቀበረ ውኀ" በሚለው ግጥሙ አለዝቦ ያቀርበዋል። ግጥሙ ሱዳንና ግብፅን በግመል ወክሎ፣ ውሃ ቀጂዋን ሴት ደግሞ በኢትዮጵያ ወክሎ ያቀርባል። ኹለቱም ውሃ ፈላጊ ሲኾኑ ሴቷ በእንሥራዋ ውሃውን እንዳትቀዳ እንሥራ እንሥራዋን ዕያዩ ውሃዬን አትንኪ በሚል ዓይነት ግመሉ ጠብ ሊያነሳ ይከጅላል። እሷም ዐባይ የኔ ውሃ ነው በማለት እያዜመች ባለቤትነቷን ትገልጻለች። ይህን እሰጥ አገባ ተራኪው በሚታዘብበት ወቅት ጥቁር ዐባይ ከነጭ ዐባይ ጋራ ተዋሕዶ፣ የሱዳንንና የግብፅን በረሓ እያቆራረጠ ይነጉዳል። ተራኪውም ለነዚህ ሕዝቦች የዐባይን ትሩፋት ምንነት እንደሚከተለው ይገልጸዋል፦

እነሱን ባቁዋረጠ
    ዐባይ
ጸደቀ
ዐባይ ዐባዬ
    ውኀ!
እና ባስታጠቀ
አረንጉዋዴ መቀነት
ያንን ንጣት
    በረኀ
ዐባይ የጸደቀበት
    በሀ፦     (ገጽ 26)

እነዚህን አገሮች ዐባይ የጸደቀባቸው በሀ አድርጎ ማቅረቡ ዐባይ ባይኖር አገራቸው ሰውን የማያኖር ድንጋይና ነጭ አሸዋ ብቻ ይኾን ነበር ለማለት ነው። የዐባይ ሲሳይ ደጋው ለቆላው ኢጋሩ የኾነበት ቢኾንም ከነሱ አፀፋው ለደጋው በጎ ምኞት አይደለም። ይህ ኢጋርነት በበጎ ፈቃድ የተደረገ ልግስና ብቻ ሳይኾን ከመነጨበት ከደጋው አገር አንደኛ ዐባይን የሚያለማ ጠፍቶ፣ ኹለተኛ የሚያስከትለውን መዘዝ (በተቀበረ ፈንጂ የተመሰለውን ጦርነት) ፈርቶ መኾኑን በቁጭት ይገልጻል። የሐሴ ዲላማ በድፍረት እጦት ወንዙን ያላለሙት የደጋው አገር መሪዎች ናቸው፦

*ውኀ*
*እየጠማው*
*ያባይን ልጅ*
*እሚያዘጋጅለት ቢጠፋ*
*እሚያበጃጅ*
*ለልማት የሚያመቻች*
*ዐባይን*
*አኮላሽቶለት ፈንጂውን።* (ገጽ 26)

የሰይፉ "*ያሻቀቡ ወራሪዎች*" የዐባይ ጦስ እንዴት ለጥቁር ሕዝቦች እንደ ተረፈ ያወሳል። ነጮች ዐባይን እናቀናለን በሚል መጥተው በጥቁሮች ላይ የቅኝ አገዛዝ ቀንበር እንደጫኑባቸውና ጉልበታቸውንና ሀብታቸውን እንደ በዘበዟቸው ይተርካል። ገጣሚው ካርቱም በነበረበት ጊዜ የተጻፈ ስለኾነ እንግሊዝ የሱዳን ቅኝ ገዢ በነበረችበት ጊዜ ዐባይን ለመስኖ እርሻ በመጠቀም በተለይ ለአገሯ የጨርቃ ጨርቅ ኢንዱስትሪ የሚኾን ጥጥ በምታመርትበት ጊዜ የነበረውን ብዝበዛ ያወሳል፦

*ሥጋውን በሉ*
*እነሱ*
*ደሙን ጠጡ*
*እነሱ*
*እና ተሞሉ*
*በደሙ! ደሙ!*
*የባላገሩ! ባላገሩ።* (ገጽ 257)

ግጥሙ የሚቋጨው የዐባይ ደም የባላገሩ (የአገሩ ባለቤት/ገጠሬው) ደም እንደ ኾነ በመግለጽ ነው። የየትኛው ባላገር? አንድም በመስኖ እርሻ ላባቸውን አንጠፍጥፈው ሀብቱን ያፈሩትን የሱዳን ገበሬዎች ማለቱ ነው፤ ግን በዚህ አይወሰንም። "*ያሻቀቡ ወራሪዎች*" የሚለው ርእስ በወረሩት አገር ላይ የነጮቹን የበላይ ገዥነት ብቻ ሳይኾን ዐባይን ደገኛው አገር ገድቦ እንዳይጠቀምበት ከመከላከላቸው አንጻር ወረራው በተዘዋዋሪ ወደ ደገኛውም ያሻቀበ ነው ብሎ መገመት ይቻላል። በዚህ እሳቤ ዐባይ የደገኛውን ባላገር መሬት ዐፈር ጠራርጎ፣ የሱን ዥረቶች ውሃ ሰብስቦ፣ እሱን ለድኽነት ኢጋልጦ ለበረኸኞቹ አልሚዎች ስለሚያስረክብ ያ ወራሪዎቹን የሞላው ደም የደገኛውም ደም ነው የሚል አንድምታ አለው። ስለዚህ ያሻቀቡት ወራሪዎች ደገኛውንም ከርቀትም ቢኾን አልተዉትም።

ከሰይፉ ግጥሞች በላቀ ዐባይ የውጭ ኃይሎች፣ በተለይም የግብፅ፣ የሤራ መሸረቢያነቱ ጎልቶ የሚወጣው በኢሕዴግ ዘመን በተደረሱ ልቦለዶች ውስጥ ነው። ከዚህ አንጻር የአየለ ዲ. ሚደቅሳ የዓባይ ቋያ (2003 ዓ/ም) ዓይነተኛ ምሳሌ ነው። ታሪኩ የሚሽከረከረው ዐባይን ለማልማት በምሥጢር ስለተዘጋጀው የፕሮጀክት ዕቅድ ዝርዝር መረጃ ለማግኘት የግብፅ የስለላ ድርጅት "ኦፐሬሽን ብሉ ናይል - 009" የሚል ግዳጅ የተሰጠውና አሊ ሳብሪ በተባለ ግብፃዊ የሚመራ ምሥጢራዊ ቡድን በኢትዮጵያ ውስጥ በሚያደርጋቸው የስለላና የግድያ ተግባራት ዙሪያ ነው። ለኦፐሬሽኑ መነሻ የኾነውም የግብፅ የደኅንነት ዋና ቢሮ ከቻይና፣ ከሕንድና ከኮርያ የተገኙ ለግዙፍ ግድብ ሥራ የሚኾን የብድር ጥያቄ ጭምጭምታዎች ስለደረሱትና የግብፅን መንግሥትንም ሰላም ስለ ነሳው ነው ይለናል ተራኪው። ስለዚህ አስተማማኝ መረጃ የሚገኘው ከፕሮጀክቱ ሰነድ ስለኾነ ቡድኑ ይህን በእጁ ለማስገባት በኢትዮጵያ ውስጥ በየመሥሪያ ቤቱ የስለላ መረቡን ይዘረጋል፤ የግብፃውያን ፋብሪካ ሠራተኞችንና ቅጥረኛ ኢትዮጵያውያንን ለተልእኮው ያሰልፋል። የግድቡ ፕሮጀክት ዕቅድ ነዳፊ ናቸው የተባሉ ሰባት የውጭና የኢትዮጵያ ዜጎችን በመለየት ያሳድዳል፤ ብዙዎቹንም ይገድላል። በመጨረሻም ቁልፉን ሰነድ በእጁ አስገብቶ አሊ ሳብሪ ቦሌ አውሮፕላን ማረፊያ ሲደርስ ባለቀ ሰዓት ላይ በኢትዮጵያ የደኅንነት ሠራተኞች ተደርሶበት እዚያው ይገደላል።

የልቦለዱ ሤራ አመክኖአዊነትና ተአማኒነት በሌላቸው ብዙ ኹነቶች የተዋቀረ ነው። በመጀመሪያ የአንድ አገር ግዙፍ ፕሮጀክት ብቸኛ ሰነድ በአንድ ከውጭ የመጣ ኢትዮጵያዊ እጅ በቤቱ ውስጥ የሚቀመጥበት ኹኔታ ኢተአማኒ ነው። ሁለተኛም የፕሮጀክቱ ነዳፊ የተባሉት የውጭ ሀገር ባለሙያዎች አንገታቸው እየተቀላ በየቦታው ሲጣሉና የተቀሩት ባለሙያዎች ሲሳደዱ በዚህ ግድያ ተጠቃሚው ማነው ብለው የኢትዮጵያው የደኅንነት ባለሙያዎች ለረጅም ጊዜ ግብፅን መጠርጠር የሚሳናቸው መኾኑ ነው። እንዲያውም ልቦለዱ ኢትዮጵያን አይበገሬ አድርጎ ለመሣል ከተነሳበት ዓላማ በተቃራኒ የመረጃና የደኅንነት ሠራተኞቹና አለቆቻቸው የሙያ ክሂሎታቸው እንጭጭ፣ እንቅስቃሴያቸው ቅልጥፍና የሌለውና ከአንድ አነስተኛ ሠርጎ ገብ የግብፅ ቡድን ያነሰ ኾኖ ነው የተሣለው። የልቦለዱ ደራሲ ስለ ወንጀል ምርመራ ስልት በቂ ንባብና መረጃ ያለው፤ በዚህ ዘርፍ የሚጻፉ ልቦለዶች የሚጠቀሙበትን የትረካ ብልሃትም ያጤነ አይመስልም። እነዚህ ሕጸጾች በሌሎቹም የግብፅን ሤራ ለማሳየት በሚጥሩ ልቦለዶች ተደጋግመው የሚከሠቱ ናቸው።

በዚህ ልቦለድ ውስጥ የግብፃውያኑ ጉዳይ አስፈጻሚዎችና መንገድ መሪዎች፣ እንዲሁም የውስጥ ባንዳዎችን መልማዮች ኤርትራውያን ኾነው ቀርበዋል። ተራኪው "ቅጥረኞች" የሚላቸው ኤርትራውያን በኢትዮጵያ ተወልደው ካይሮ ሲኖሩ በግብፁ የስለላ ተቋም ተመልምለው ኢትዮጵያ ውስጥ ሠርገው እንዲገቡና ኹኔታዎችን ለዐረቦቹ እንዲያመቻቹ የተደረጉ ናቸው። ምንም እንኳ የኤርትራ መንግሥት በዚህ የስለላ ተልእኮ ውስጥ ምንም ሚና ባይሰጠውም የኤርትራውያኑ የኢትየጵያን ብሔራዊ ጥቅም በሚጎዳ ተልእኮ የዐረብ ተላላኪ ኾነው መቅረብ በአገር ውስጥ መገናኛ ብዙኃን ስለ ኤርትራውያን ፀረ ኢትዮጵያነት ይነዛ የነበረውን የጊዜው ትርክት የሚያስተጋባ ነው። ኹለቱ ኤርትራውያን በዚህ ተልእኮ ለመሳተፍ የተነሱበትን ምክንያት ተራኪው ሲገልጽ "በቂም በቀል ስሜት የተሞሉ ስለሆኑ ኢትዮጵያን ለማዋረድ የሚሰጣቸውን ማንኛውንም ግዳጅ ይወጣሉ" ይለናል (ገጽ 24)። የዚህ ዓይነቱ ትርክት የኢትዮጵያ ሕዝብ ስለ ኤርትራውያን ወንድሞቹና እህቶቹ የሚኖረውን አመለካከት የበለጠ የሚያጠለሽ፣ ለጊዜያዊ የፖለቲካ ፍጆታ የዋለ ፕሮፓጋንዳ ነው።

ሌላው ከዐባይ ግድብ ግንባታ ጋራ ተያይዞ የሕዝብ ድጋፍን ለማሰባሰብ በልቦለዱ የቀረበ ማማለያ የግድቡ ውሃ ቤኒሻንጉልን፣ ወለጋን፣ ጋምቤላንና ሌላውንም በረሓማ ቦታ ለሰፋፊ እርሻ እንዲያለማ ይቀለበሳል የሚል ነው (ገጽ 55—57)። ይኼም የሕዳሴውን ግድብ በሚመለከት የመንግሥትን ተጨባጭ ዕቅድ፣ እንዲሁም የድንበር ተሻጋሪ ወንዞች የሚገዙበትን ዓለም ዐቀፍ ሕግጋት ያላገናዘበ ፕሮፓጋንዳ ነው። ግድቡ የኤሌክትሪክ ኃይል ከማመንጨት አልፎ ውሃውን በመስኖ ቀልብሶ ለነዚህ ሁሉ ክልሎች እርሻ ማስፋፊያ ለመጠቀም ግዙፍ መዋዕለ ንዋይ ከመጠየቁም በላይ ለታችኞቹ አገሮች የሚደርሰውን ውሃ በማቆም ወይም በከፍተኛ ደረጃ በመቀነስ በህልውናቸው ላይ ከፍተኛ ጉዳት በማድረስ ድርጊቱ ዓለም ዐቀፍ ሕግን የሚጥስ ይሆናል። ይህ ደግሞ እነግብፅ የዐባይን ውሃ ፍሰት በመቀነስ ህልውናቸውን በሚያናጉት ላይ ኃይል ለመጠቀም ለሚያቀርቡት ሙግትም ኾነ ዛቻ ሕጋዊ ሽፋን ይሰጣል (ኃይሉ 2001፣ ገጽ 155-159፤ ተስፋዬ 2002 እጎአ፣ ገጽ 1542-1543)።

የካሣ አያሌው ተልዕኮ ምፅዓት (2004 ዓ/ም) ዋና ጭብጡ የዐባይ ግድብ ባይኾንም በተደራቢነት የግብፅን አፍራሽ ሚና ይተርካል። የልቦለዱ ዋና ትኩረት ፒተር ሃንሰን የተባለ የሲ.አይ.ኤ. የቀድሞ ባልደረባ የጽንፈኛ ጽዮናውያንን ቡድን ከተቀላቀለ በኋላ የነሱን "የተልዕኮ ምፅዓት" ግብ ለማሳካት ከግብፅና ከሳውዲ ዐረቢያ ግብረ አበሮቹ ጋራ ወደ ኢትዮጵያ በመግባት አገሪቱን ለማበጣበጥና ለማፈራረስ በሚሸርበው ሤራና ጥፋት ላይ ነው። የተልእኮው ግብ እንደሚከተለው ይነገረናል፦

> ተልዕኮው ዋነኛ ግቡ ታላቅና ለዓለም ሕዝብ ሁሉ አዳኝ የምትሆን እሥራኤልን መፍጠር ነው። ለዚህ ደግሞ በዋናነት ጥንታዊ ማንነታችን የሚገልፁት ቅርሶቻችን ከተዘረፉበት መሰብሰብ አለባቸው። ጥንታዊቷ እየሩሳሌም በጥንት ንብረቶቿ ካልተሞላች ገናናዋ እሥራኤል ልትፈጠር አትችልም.... የዚህ ሁሉ ማሳረጊያ የሆነው ዋና ጉዳያችን ኢትዮጵያ ይገኛል። መሳለሚያችን፣ ማክበሪያችን ብሎም ብቸኛው የእድላችን ምንጭ ታቦተ ፅዮን እዚያ ትገኛለች። ህልውናችን እንዲቀጥልና ገናናነታችን እንዲመለስ ካስፈለገ የትኛውንም አማራጭ ተጠቅመን ሁሉንም በእጃችን ማስገባት አለብን። (157-58)

ለዚህ ኢተአማኒ ግብ ስኬት በሙስሊም ወንድማማቾች ተጽዕኖ ሥር የወደቀችው ግብፅ፣ የዋሃቢ እምነትን በምሥራቅ አፍሪካና በመካከለኛው ምሥራቅ በማስፋፋት በአካባቢው ለመግነን የምትጥረው ሳውዲ ዐረቢያና በአካባቢው ተቀናቃኞቿ ላይ የጦር የበላይነቷን አስጠብቃ ህልውናዋን ማስከበር የምትሻው ጽዮናዊት እስራኤል "የጠላቴ ጠላት ወዳጄ ነው" በሚል መርሕ በኢትዮጵያ ላይ ያብራሉ። ተልእኮዋቸውን ለማሳካት ስለሚከተሉት ስልትም ፒተር ለግብረ አበሮቹ እንዲህ ይገልጽላቸዋል፦

> እንደምታውቁት ዋናው ተልዕኳችን በመላ አገሪቱ አለመረጋጋትን በመፍጠር የመንግሥትን ትኩረት ማስቀየር ነው። መንግሥት ትኩረቱን ከዐባይ ውሃ ላይ ሊያነሳው የሚችለው ብቸኛ መንገድ ማኅበራዊ ቀውስ መፍጠር ሲቻል እንደሆነ ተስማምተናል። ይህ ደግሞ በሌላ ጎን የሌሎቻችንን አላማም ለማሳካት ይጠቅመናል። በእምነት ተቋማት፣ በከተማ፣ በገጠር፣ በት/ቤቶች፣ በሥራ ቦታዎች... በሁሉም አካባቢ የተቃውሞና የተቃርኖ ውጥረቶችን ለማስፈን እየተንቀሳቀስን ነው። እነኚህ አካሄዶች አካባቢዎቹ የተለያዩ እንደመሆናቸው መጠን የተለያየ ስልትን እንድንከተል አስገድደውናል። (ገጽ 107-08)

ከላይኛው ገለጻ ልቦለዱ ስለ ግብፅ ማስተላለፍ የፈለገው ዋናው መልእክት ኢትዮጵያ የዐባይ ግድብን እንዳትገድብ ግብፅ ማንኛውንም እርምጃ ከመውሰድ ወደ ኋላ እንደማትልና ይህን ግቧን ለማስፈጸም አገሪቱን ለማመስ እንደምትጥር፣ አገሪቱ እንዳትለማና እንዳታድግ ቀን ከሌት እንደምትሠራ፣ ከአገር ውስጥም ከውጭም ለዚህ ከሚረዳት ማንኛውም ፀረ ኢትዮጵያ አካል ጋር እንደምትተባበር፣ የሕዝብ ብሶትንም አቅጣጫ ለማስለወጥና በመንግሥት ላይ ተቃውሞ በማስነሳት ከልማት ዕቅዱ ለማዘናጋት የምትሰማራ መኾኗን ነው። ለዚህ የመጀመሪያ አጋሯ ሳውዲ ዐረቢያ እንደኾነችና ይህች አገርም (ካሁን በፊት በተለይ በኦሮሚያ ክልል በበሻሻና በጅማ አካባቢዎች እንደታየው) ጽንፈኛ የሃይማኖት እምነቷን በአካባቢው በማስፋፋት የበላይነትን ለመጎናጸፍ በኢትዮጵያ ሽብርና ዐመፅን፣ የእርስ በርስ ግጭትንም በገንዘቧ እንደምትደግፍ፣ ወጣቶችን በጽንፈኝነት ለመመልመል እንደምትሞክር ልቦለዱ ለማሳየት ይሞክራል።

በልቦለዱ ውስጥ ሌሎች የፕሮፓጋንዳ መልእክቶችም ቀርበዋል። "ተስፋ ለሁሉም" የተባለው በጎ አድራጎት ድርጅት የሜራው አንዱ ቀንደኛ ተዋናይ መኾን (ገጽ 92-95) የኢሕአዴግ መንግሥት የ1997 ዓ/ም ምርጫን ተከትሎ የዜጎችና ሰብአዊ መብቶች ተሟጋቾችን ነጻ እንቅስቃሴዎች ለማፈን ያወጣውን ዐዋጅ (ዐዋጅ ቁ. 621/2001) ቅቡል ለማድረግ በሲቪል ማኅበረሰቡ ላይ በመገናኛ ብዙኃን አማካኝነት "በጎ አድራጎት ድርጅቶች የግል ጥቅም ማስከበሪያና የባዕዳን አጀንዳ አራማጆች ናቸው" የሚለው የማጥላላት ዘመቻ ተቀጥያ ነው። ከዚህ ሌላም ልቦለዱ በተለያዩ ቤተ እምነቶች ተከታዮች መካከል በተደጋጋሚ የሚከሠተው ግጭት እና በኢሕአዴግ መንግሥት ላይ በየቦታው የሚነሳው የዜጎች ተቃውሞ የባዕዳን ቅስቀሳ ውጤት እንደኾነ በመጠቆም፣ ዜጎች በራሳቸው ተነሳሽነት የኢኮኖሚ፣ የዴሞክራሲና የፖለቲካ ጥያቄ አያነሱም የሚል አንድምታ ያለው ጭብጥ ያራምዳል። ልቦለዱ የግል መገናኛ ብዙኃንንም ሲያጠለሽ የባዕዳንን አጀንዳ ለማራመድ ሲሉ ሕዝባዊ ብሶት ያለ አስመስለው የሚያራግቡና የፈጠራ ዜና በገንዘብ እየተገዙ የሚነዙ ያደርጋቸዋል (ገጽ 92-93)።

የእርቅይሁን በላይነህ ታዳኤል (2005 ዓ/ም) እና የበላይ ማናዬ አዙሪት ዘአልፋ (2005 ዓ/ም) የይስማዕከ ወርቁ ዴርቶጋዳ (2001) እና የዚሁ ተከታታይ ልቦለዶቹ ግልጽ ተጽዕኖ የሚንጸባረቅባቸው፣ ጥቂት የተማሩ ግለሰቦች ከመንግሥት መዋቅር ውጪ ተሰባስበው በራሳቸው ጥረት ኢትዮጵያን በቴክኖሎጂና በልማት ለማስፈንጠር የሚታትሩበት ሳይንስ መሰል የፋንታሲ ልቦለዶች ናቸው። "ታዳኤል ማለት ጠላት የማያጠቃው ማለት ነው" (253) ተብሎ ይነገረናል። በዚሁ መሠረት ዋናው ገጸ ባሕርይ ኢዛና እና ባልደረቦቹ "የሰው ልጅ በምድር ላይ ሕያው ሆኖ እንዲኖር የዕፀ በለሷን ፍሬ ዳግመኛ መብላት አለበት" (ገጽ 44) በሚል ይቺን ዘላለማዊ ሕይወት የምታጎናጽፍ ፍሬ ለማግኘት የመጽሐፍ ቅዱሱ ግዮን ወደሚፈልቅባት ገነት ለመግባት ግሸ ዐባይ ምንጭጋ ኼደው ይቆፍራሉ። በዚህ የኒኢዛና ትረካ ውስጥ ልቦለዱ ምንም የሳይንስ ቅንጣቢ እንኳን ጠብ ያላለበትን የተአምራት ጋጋታ ያዥጎደጉዳል። እነኢዛና ዓላማቸው ፍሬውን በእንክብል ወይም በክትባት መልክ ቀምመው ለኢትዮጵያ ወታደሮች በመስጠት ከአካላዊ ሕመምና ሞት ለመከላከልና በግብፅ የጦር ኃይል ላይ የበላይነትን ለመቀዳጀት፣ እንዲሁም ግድቡን ለመሥራት የሚያስፈልገውን ሀብት ለማሰባሰብ ለባለጸጎች መድኀኒቱን መሸጥ እንደ ኾነ ይተረከልናል። የዚህ ዓይነቱ ሕልማዊ ትርክት የሚያራምደው አገሪቷ ያለመለኮታዊ ጣልቃ ገብነት በዜጎቿ ዕውቀት፣ ላብና ቁርጠኛነት

ብቻ ለመልማትም ኾነ ባላንጣዎቿን ለመቋቋም ይሳናታል የሚል የተንበርካኪዎች ሥነ ልቦና ይመስላል።

የፕሬዚዳንት ሙባረክን መንግሥት የተካው ጊዜያዊ ወታደራዊ መንግሥት በዐባይ ጉዳይ ከኢትዮጵያ ጋራ ያለውን ሙግት ለጊዜው አገራቸው እስክትረጋጋ በዲፕሎማሲ መንገድ ለመፍታት መወሰኑን፣ ኾኖም ጥቂት ከፍተኛ ወታደራዊ መኮንኖችና የደኅንነት አባላት ይህን ባለመቀበል ምሥጢራዊ ቡድን መሥርተው ኢትዮጵያ ውስጥ እንደሚንቀሳቀሱ ልቦለዱ ይተርካል። እነሱም የኢትዮጵያን የደኅንነት ሚኒስትር ከነምክትሉና ሌሎች ሠራተኞች የግብፅ ቅጥረኛ ኾነው የነኢዛናን የፕሮጀክት ፕሮፖዛል ለግብፅ ለመሸጥ እንዲስማሙ ያደርጋሉ። ቅጥረኞቹም ለነኢዛና ጥበቃ እንዲደረግ ጠቅላይ ሚኒስትሩ የሰጠውን ትእዛዝ በመተላለፍ የነኢዛናን ቡድን አባላትና በግብፅ ያሉትን የኢትዮጵያ ሰላዮች ለግብፅ ደኅንነት አሳልፈው በመስጠት እስከ ማስገደል ይደርሳሉ። ስለኾነም የእርቅይሁን በላይነህ ታዳኤል ከተነሳበት ኢትዮጵያን አተልቆ የመሣል ዓላማ በተቃራኒ ለግብፅ የፕሮፓጋንዳ ገጸ በረከት ኾኖ ያርፈዋል — የኢትዮጵያ ባለሥልጣናት አገራቸውን ከመታደግ ይልቅ የግል ጥቅማቸውን ስለሚያስቀድሙ ለጠላት መሣሪያ ኾነው ጀግኖቻቸውን ከመግደል አይመለሱም የሚል ፕሮፓጋንዳ። የልቦለዱ ሌላው ፕሮፓጋንዳ ደግሞ ከጠቅላይ ሚኒስትሩ በስተቀር የቀሩት ባለሥልጣናት የአገር ፍቅርና አገራዊ ርእይ የላቸውም የሚል የአንድን ግለሰብ ገጽታ ለመገንባት ያነጣጠረ ነው። “ዶክተሩ ፍሬው ከማንም በፊት ለከፍተኛ ባለሥልጣናት በቅድሚያ መሰጠት አለበት ሲባል እምቢ ብሏል። ይህ ማለት ለተራው ሕዝብ በመስጠት ተራውን ሕዝብ ዘላለማዊ ማድረግ፣ የተከበሩትን የሀገራችንን ባለስልጣናት ለሞት መገበር ማለት ነው። ይህ ማለት ደግሞ አዳዲስ ባለስልጣናት መንበረ መንግሥቱ ላይ ይወጣሉ። እነሱ ገገር የእኛ ወገኖች ተገገር ይሆናሉ ማለት ነው” (ገጽ 112) የሚለው የኮንስትረክሽን ሚኒስትሩ ክርክር እና “የኔ ሹመኞች ሆድ እንጂ ህሊና የላቸውም” (ገጽ 103) የሚለው የኢዛና ፕሮጀክት ደጋፊ የኾነው የጠቅላይ ሚኒስትሩ አስተያየት የሚያሳየው ይህንኑ የመሪውን ገጽታ የመገንባት ጥረት ነው።

የበላይ ማናዬ አዙሪት ዘአልፋ (2005 ዓ/ም) ደግሞ በአንድ የዩኒቨርሲቲ የሕግ መምህር አደራጅነት የተሳበሰቡ ተማሪዎችና በውጭና በአገር ውስጥ ያሉ ጥቂት ምሁራን ኢትዮጵያን በቴክኖሎጂ፣ በልማትና በጦር ኃይል ለማመንጠቅና በአገሪቱ ውስጥ የዴሞክራሲን ሥርዓት ለመገንባት የሚያደርጉትን ኅቡእ እንቅስቃሴ የሚተርክ ነው። በከርሰ ምድር ውስጥ እንደ ዴርቶጋዳ ከምርምር ማእከል አልፎ የጦር አውሮፕላኖችን ጭምር የያዙ ሰፈሮችን መንግሥት ሳያውቅ የሚገነቡት የቡድኑ አባላት መንግሥት ያላወቀውን፣ ከካይሮ ስለ ግድቡ መረጃ ለመሰብሰብ የመጣ ሰላይ ከአውሮፕላን ማረፊያ ጀምሮ ባሕር ዳር ድረስ ተከትለውት ኼደው ይጠልፉትና ከመረመሩት በኋላ የመረጃ ዐቅማቸውን አሳይተውት ወደ አገሩ እንዲመለስ ገንዘብ ጭምር ሰጥተው ይለቁታል። በልቦለዱ ውስጥ የኢተአማኒ ኹነቶቹ መብዛት ከሌሎቹ ልቦለዶች ጋራ ያለው ተመሳሳይነት እንደ ተጠበቀ ኾኖ ከላይኞቹ ልቦለዶች የሚለየው ለግብፅ መንግሥት ስለላ አፀፋ መስጠት የሚችል መንግሥታዊ ያልኾነ የአገር ወዳዶች ስብስብ እንዳለ ማሳየት ቢኾንም ውጤቱ ግን የውጭ ኃይሎችን ሤራ አነፍንፎ የማክሸፍ ቀዳሚ ኃላፊነት ያለበትን የመንግሥትን ዐቅም አኮስሶ በመሣል የሕዝብ አመኔታን መሸርሸር፣ የአገርን ገጽታም ማጠልሸት ነው። በአንጻሩ ግን የትኛውም የግብፅ መንግሥትም ኾነ ኃላፊ ዐባይን በሚመለከት የአገሩን ጥቅም ለማስከበር ምንጊዜም ተግቶ በአንድ ልብ እንደሚሠራ ልቦለዱ ማሳየቱ አልቀረም።

## 5. ከዳተኛው ዐባይ! በደለኛው ዐባይ! ...ይከስሳል ደገኛው

ከደርግ ዘመነ መንግሥት ጀምሮ እስከ የሕዳሴው ግድብ ግንባታ ጅማሬ (መጋቢት 2003 ዓ/ም) ድረስ ለንባብ ከበቁት የዐባይ ግጥሞች አብዛኛዎቹ የእሮሮ ድምፆች ናቸው። በመካከላቸው ያለው ዐቢይ ልዩነት የድምፀታቸው መከረርና መለዘብ፣ እንዲሁም በሚቀርቡት ሙግቶች ውስጥ የከሳሹና ተከሳሹ መለዋወጥ ነው። መጀመሪያ ለዘብ ካለው የሰይፉ መታፈሪያ የብሶት ግጥም "ዐባይ በበረሃ" እንጀምር። ቀደም ባሉት ግጥሞች እንዳየነው ኹሉ ዐባይ ከአገሩ ባመጣው ለም ዐፈር የሰው በረሓ ቢያለማም ባይተዋርነቱ እንዳልቀረለት ይሄኛው ግጥሙም ይገልጻል። ተጠቃሚዎቹ ዐባይ ለሰጣቸው በረከት ምንጭ ለኾነው አገር በማወቅም ኾነ ባለማወቅ ዕውቅና እንዳማይሰጡ ግጥሙ ይነግረናል፦

ሕዝቡ አያውቅ
    ከየትነቱን
ማለት ጣና ምንጩን
ቢያውቀውም አያሳውቅ
የሱነቱን ማድመቅ
    ከነምንጩ። (ገጽ 467)

እናም ምፀቱም አብሮ ቀርቧል — ያባይ ልጅ በሱዳን አገር ውሃ ቢጠማው ያባይን ውሃ በሱዳናዊው ሲጋበዝ። ግን የሌላ ሕዝብ ሀብትነቱን ሱዳናዊው ለምን ብሎ ዕውቅና ይስጠው? ለበረሓው ቃጠሎው ነፍስ አድን ውሃውን፣ ለዕለት ጉርሱ ለም ዐፈሩን የሚያመጣው ጥቁር ዐባይ ከሌላ ሕዝብ በነጻ የተወሰደ ሲሳይ ነው ማለት በሕልውናው ላይ በስተኋላ መዘዝ መጋበዝ ነው። የኢትዮጵያን የወንዙ ባለቤትነት ማወቅ ማለት እሷ ወንዙን ለራሷ በሚጠቅማት መልኩ ብታለማ ተቃውሞን ለማንሣት ሕጋዊ መሠረት ማጣትን ሊያስከትል ስለሚችል። የሱዳን እንግዳው ሐበሻ ግን በዐባይ ወንዝ "ሕዳጎች" ያለውን እርሻና ዕፀዋት በመጥቀስ ሱዳኖች እንዴት ከዐባይ ውሃና ደለል እንደ ተጠቀሙ በቁጭት ትዝብቱን ይነግረናል። የደገኛው ሕዝብ ገራገርነት ራሱ በስላቃዊ ምፀት ነው የሚቀርበው። ቸርነቱ ገደብ የለሽና ኢአመክኖአዊ በመኾኑ፣ ራስን እያቆረቆዙ ለሌላው ልግስና፣ ሊያውም ምስጋናም ዕውቅናም ለማይሰጥ ወገን መኾኑን እንዲህ ይገልጸዋል፦

ላመቱም ሰጥቶ
ዐባይ
ላመቱም!፦
  ..
ጨረሰው
የገመሰውን ያገሬን ዐፈር
የደጋ አገር
ደጋ-'ገር
ገር!
እየተበዘበዘ እማይናገር። (ገጽ 466)

ይህ የዐባይ ሥራ ግን ለተራኪው እንደ ኹለት ሞት ይታየዋል። ባንድ በኩል አገሩን አራቁቶ የሰው በረሓ በማልማቱ፣ ኹለተኛም ያገሩ ልጅ በበረሓ ጥም ሲቃጠል ድፍርስ ውሃ በማጠጣቱ። እዚህ ላይ ተራኪው “የጋጠኝ ሳያንሰው/ጀርባዬን” ሲል ኢትዮጵያን ኾኖ ስለሚናገር የግጥሙ እሮሮ የእሷ ይመስላል፡-

እና የኔ አባዜ
ሁለቴዬን መገደል
ዐባይ እኔን ሲበድል
የጋጠኝ ሳያንሰው
  ጀርባዬን
ዐፈሬን እያጋዘው
  ካገር ምድሬ
የደጋው የጋተኝ
ብጥብጥ ነው። (ገጽ 465)

ሰይፉ “ዐባይ ሲጋለጥ” በሚለው ግጥሙም አሁንም ዐባይን ኹለቴ እንደ ገደለው በመጥቀስ ይወነጅለዋል። በዚህኛው ግጥሙ ግን ዐባይን በመክሰስ ብቻ አያቆምም። ዐባይ የሕዝቡን ዐፈር እንዲህ “ለማንም ሰጥቶት” አለማፈሩ ገራገር ሸማግሌ ቢኾን ነው ቢባልም የአገር ሀብት ለባዕድ አሳልፎ መስጠቱ ትልቅ ጥፋት ነውና ታሥሮ እንዲፈረድበት ተበዳዩ አቤቱታውን ያቀርባል፡-

ዐባይ አጥፍቱዋል
    በርግጥ
ሀብት አባክኑዋል
    የሕዝብ፤
ስለዚህ ይታሠር
    ተይዞ
ይመርመር
በሣር-ቅጠል ፍታብሔር። (ገጽ 337)

በግጥሙ ውስጥ ዐባይ “ይታሠር”፣ “በሣር-ቅጠል”፣ “በፍታብሔር” የሚሉት ዘይቤአዊ ቃላት የግጥሙን ዋና ፍሬ ሐሳብ ያዘሉ ናቸው። ዐባይ ተይዞ የሚታሠረው ሲከተር ነው። ውሃና ዐፈሩን አግዞ የራሱን አገር ምድረ በዳ ከማድረግ ይልቅ በግድብ ታግቶ በመስኖ አገሩን እንዲያለመለም፣ እርሻውን በሰብል፣ ሜዳ ሸንተረሩን በሣር በቅጠል እንዲሸፍን፣ ፍትሐዊ፣ ሕጋዊ መንግሥታዊ እርምጃ እንዲወሰድበት የልማት ጥሪ የሚያስተላልፉ ዘይቤዎች ናቸው።

የአያልነህ ሙላቱ “ዐባይ በጉልበቱ” (2004 ዓ/ም) እንደ ሰይፉ ግጥሞች በደርግ ዘመን (በ1974 ዓ/ም) ደራሲው በሱዳን (አየር) ላይ ሲበርር የተገጠመ ሌላው የቁጭት መገለጫ ነው። አያልነህ የሣለው ዐባይ እንደ መስፍን ወልደ ማርያም ዐባይ ጉልበተኛ ነው። ጉልበቱ ደግሞ ለመድፍ ኾነ ለሌላ የጦር መሣሪያ ሳይበገር የአገሩን ሀብት ዘርፎ ለሱዳንና ለግብፅ ማራገፉ ነው። ስለዚህ ዐይናችን

እያየ፣ ጆሮአችን እየሰማ ወዛችን ሲጠረግና መብታችን ሲገፈፍ "የእኛን ንብረት እኛ ቆመን አንቀማ" በማለት አገሬው መብቱን እንዲያስከብር ጥሪ ያቀርባል። የዐባይ ወንጀል ከዚህም አልፎ የባሰ አደጋ በአገር ላይ ስለ ደቀነ በወሬና በስንፍና ከመተብተብ ተላቆ አገሬው አፋጣኝ እርምጃ እንዲወስድ ተራኪው ይወተውታል፡-

እኛ ጦም ስናድር ያበላነው ሁሉ
ዛሬ እኛን ሊውጠን አሰፍስፏል አሉ።
ታዲያ በስንት በኩል ቁመን እንበላ
አንዱን በስንፍና.. ሌላውን - በሌላ።
ባይሆን ስንፍናውን ለማረም እንንቃ
ወዛችን በግዮን መታጠቡ ይብቃ!
የሱዳን አሸዋ የግብጹ ሰሃራ
ነገም በእኛ እስኪሆን.. ቁመን ቧልታ አናውራ። (ገጽ 667)

ስለዚህ ሊወሩን ያሰፈሰፉትን መመከት ብቻ ሳይኾን ዐባይን ካላለማን እንደ ሱዳንና ግብፅ ወደ በረሓ የመለወጥ ዕድልም ይጠብቀናል በማለት ግጥሙ የአደጋ ማስጠንቀቂያውን ያሰማል። በ1978 ዓ/ም በደረሰው "ዐባይ ንጉሡ" በሌሎች ጥቅም አስከባሪነት ዐባይን ቢከሰውም እነሱም የትም አይደርሱም ሲል ይጽናናል።

የእኛ አባይ ታላቁ የእኛ አባይ ንጉሡ
አንተን ከላይ አርገው ሌሎች ገሥገሡ
ትዝብቱ ነው እንጂ.. እና! የት ሊደርሱ? (ገጽ 899)

አያልነህ ሙላቱ በ"አባይ በጉልበቱ" ያቀረበው የአደጋ ማስጠንቀቂያ በቴዎድሮስ ጸጋዬ "እዬዬ" (1999 ዓ/ም) መልኩን ቀይሮ ይቀርባል። ግጥሙ ዐባይ ለጨኸቷ ማስታገሻ "ከኀዋ" ቢላክም፤ ለሌላው ወገን የመድኀን ወይን ሲኾን ለኢትዮጵያ ግን አባሽ ያጣ የደም እንባ መኾኑን ይገልጻል፡-

ከዓይኖችዋ ስርቻ ሲፈልቅ
ደም ቀላቅሎ የሚወጣ፣
ወዲያ ማዶ ግን
ወይን ሆኖ ለህላዌ የሚጠጣ
እግራቸው ሥር የሚሠጣ፣
አባይ የኢትዮጵያ እምባ ነው
የሚያብሰው ብልኀ ያጣ። (ገጽ 20)

ግጥሙ ዐባይ ሌሎች ወገኖች (ሱዳንና ግብፅ) እግር ሥር መነጠፉ ባርነቱን፣ አገሩን ክዶ ለነሱ አገልጋይነቱን፣ ወዙን ለነሱ በመገበር ለህልውናቸው መሠረት መኾኑን ሲያመላክት ከኢትዮጵያ ይዞት የኼደው ውሃና ዐፈር ግን በኢትዮጵያ የደም እንባ ተመስሎ፣ የአሳሯ መገለጫ ኾኖ ቀርቧል።

ይህን የዐባይን ክህደት በማስቆም የሚታደጋት ብልኅ ልጅ ስለሌላት እናት ኢትዮጵያ እሮሮዋን ታሰማለች በማለትም ይወቅሳል።

የቴዎድሮስ "ወዮላት" (1999) እንደ ላይኛው ግጥሙ ስሞታ በማሰማት ብቻ አይወሰንም። ርእሱ እንደ አያልነህ ግጥም የአደጋ ማስጠንቀቂያ ቢኾንም በረሓነቱ ዛሬውኑ መከሠቱን ነው ግጥሙ የሚያወሳው። ግጥሙ ትናንት በአልቦ፣ በጉትቻ የተንቆጠቆጠች፣ በውብ ሸማ አካላቷን የሸፈነች፣ ማራኪይቱ ሴት ወይዘሮ ዛሬ ምንተ ኀፍረቷን እንኳን መሸፈን ተስኗታል በማለት የዐባይ ጥፋት እስከምን እንዳዋረዳት በዘይቤአዊ አቀራረብ ያሳያል፦

እንኳን ከዳን ልትፈትል  
    የጨርቋን አዝራር ቁልፍ  
        ለመቆለፍ ታክታ፣  
መለመላዋን ብትቀር  
    ገላዋን አጋልጣ  
        ለጣይ ለቁር ሰጥታ፣  
ኃፍረቷ እንቅልፏ  
    በአላፊ አግዳሚው እየተነበኘ፣  
"ኸረ ልብሷስ?" ቢባል  
    ቁልቁል ተንሸራቶ  
        ግብፅ ወድቆ ተገኘ። (ገጽ 41)

የልብሷ መገፈፍ ዘይቤ ዐባይ ያገሩን ለም ዐፈር ብቻ ሳይሆን በሜዳውና በሸንተረሩ ላይ ያገኘውን የምድሪቱን አረንጓዴ ልባስ ኹሉ ጠራርጎ ለግብፅ በማስረከብ የራሱን አካባቢ ምድረ በዳ ማድረጉን ነው የሚገልጸው። **ወዮላት** የሚለው ርእስ ኢትዮጵያ ለተጋረጠባት አደጋ በቶሎ መፍትሔ ካላበጀች ችግሯ እንደሚባባስ በመጠቆም ለዐባይ ተፋሰስ ልማት በተዘዋዋሪ ጥሪ የሚያቀርብ ነው።

የአበራ ለማ "አብዬ ዐባይ" (1994 ዓ/ም) ዐባይን እንደ ከፋው አኩራፊ፣ እንደ ስደተኛም፣ እንደ ከዳተኛም አድርጎ ይሥለዋል። ዐባይን የከፋው ተርበን ስላልበላነው፣ ተጠምተን ስላልጠጣነው፣ ታርዘን ስላልለበስነው እንደ ኾነ ተራኪው ይነግረናል። ስለኾነም በዳተኝነታችን የተከፋው "አብዬ" (አባታችን ወይስ አዛውንቱ?) ዐባይ ከድቶን ወደ ባዕድ አገር ተሰዷልና ዝም ብላችሁ አትዩ፤ የጎበዝ ያለህ ድረሱለት ይለናል። ዐባይ ተራ ወንዝ አይደለም፤ የዘር ግንዳችን ነው — የካም፣ የኩሽ ይለናል። ይህ የኢትዮጵያ "አንድዬ" ልጅ፣ የልጆቿ መሰደድ ሳያንስ እሱም ተሰዶ፣ አገሩን ከድቶ በባዕድ ጦር ሊያስወጋ በመዳዳቱ ይወቅሰዋል፦

አብዬ ዐባይ፣ ያፍሪካ ቀንድ  
የእምዬ ልጅ፣ የታሪክ አምድ  
የእኛ ሳያንስ፣ አንተም ደሞ ልትሰደድ?  
አንተም? አንተም ደሞ እንደሌላ  
ጦር ልታስጭን፣ ጉድ ሊፈላ?

አንተም ደግሞ ጨከንክብን
ከዘመኑ ተሸርጠህ፣ አደምክብን?
አብዬ ዐባይ ጦር ላክብን? (ገጽ 43)

ዐባይ ፊቱን በወገኖቹ ላይ ያዞረው አገሪቷ በአዲሶቹ ገዢዎቿ ስትታመስ አይቶ እሱን ለማልማት ዝግጁ አለመኾናችንን ታዝቦ ስለኾነ "ላብዬ ዐባይ ስጡት መላ" በማለት ዐባይን የማልማት ጥሪውን ያስተላልፋል። በአንድ በኩል በሱ ምክንያት አገሪቱ ከጎረቤት አገሮች ጋራ ጦርነት ውስጥ እንዳትገባ ሲማለድ በሌላ በኩል ደግሞ ዐባይን ከሕዝቡ በማቆራረጥ አስከፍተውታል፤ ሕዝቡንም ለልማት ከማስተባበር ይልቅ ሰላም ነስተውታል የሚላቸውን የወቅቱን ገዢዎች እንደሚከተለው ይወቅሳል፡-

ማን ይሁነን ጋሻ፣ ማን ይሁነን ጠበቃ?
"ዐባይ ለያእቆብ፣ ዐባይ ለየሱፍ ምኑ ነው?"
የሚል ሃሳዊ መሲህ፣ በዘመናችን ነግሦ
ቢያበላን ጦርነት፣ ቢያጠጣንም ከሶ፣
የዛር ውላጅ ይመስል፣ ደም ላይ ተጎንብሶ
ይኸው ያምሰናል፣ ክፉ ቀን ደግሶ፣ (ገጽ 44)

"ዐባይ ለያእቆብ፣ ዐባይ ለየሱፍ ምኑ ነው?" የሚለው አባባል የቀድሞው ጠ/ሚኒስትር መለስ ዜናዊ ባንድ ወቅት በመንግሥት መገናኛ ብዙኃን "የአክሱም ሐውልት ለወላይታው ምኑ ነው?" ያለውን በስላቕ ለማስታወስ የገባ ስላቅ ይመስላል። ስለዚህ ዐባይ የፖለቲካ ተቃውሞንም መግለጫ መሣሪያ ኾኗል። ግጥሙ ዐባይ እንዲለማ ጥሪ ቢያደርግም ለዚህ ምቹ ኹኔታ እንዲፈጠር ሕዝቡ ለአስተዳደሩም መላ እንዲፈጥርለት ጭምር ነው የሞረሸ ጥሪ የሚያቀርበው።

የልብሴ በላይ "እንደ ስሞታ ለጣና" (1991 ዓ/ም) ዐባይ ላደረሰው በደል ለአባቱ ለጣና ስሞታ ያሰማል። ዐባይ ባገሩ እንደ አምላክ ታምኖ መሥዋዕት ሲገበርለት፣ ሕዝቡ እየቸገረው ምልጃ ሲያቀርብለት ቢቆይም እሱ ግን ክብር አልወድለት ብሎ ለባዕድ በማደሩ በከዳተኝነት ይወቅሰዋል፡-

ከርሱን ላይሞላለት - ቢያመው ላይጠይቀው፣
መከበር ባገር ላይ መሆኑን ሳያጣው - ምነው ውጭ አሰኘው?
ባዕድ አስናፈቀው...እሱነቱ ጠፋው?
የደላን መስሎት - ሁሌ ስንከበው፣
ባንዱ አምላክ መስለን ሁሌ ስንከበው፣
ጠጅ ስናቋድሰው፣ አረቄ ስንረጨው ...
ይመለሳል መስሎን፣
ልመና አልወድ ብሎ ከተሳለቀብን ...ጣና ንገርልን፣
እንዲያውም ከእንግዲህ ላጉል ባህል ምርኮ፣ ለቆሌ እንቶፈንቶ ጊዜ እንደማይኖረን። (ገጽ 130)

ገበሬው ወደ ሰማይ እያንጋጠጠ በተስፋ ሲጠባበቅ ዝናቡን ኑቢያ በማራገፉ፣ የራሱን እያስራበ ግብፅን በማጥገቡ ዐባይ ላገሩ መኾን ካልቻለ፣ ጣናም ልጁን ዐባይን እንዲረግመው ይማፀነዋል፡-

ቢሆንም እርገመው - ስቀህ ካላዘዝከው፣
እሱን ያዘልክበት - ጀርባህን አሳየው።
የተኩራራበትን ጉልበቱን ሽባ አርጎ - ባንተ ውስጥ ያስቀረው፣
ካገር አይሻገር - ድንበር ላይ ያስጥመው -
ጨክነህ እርገመው
....
ለጠላት ማደርን - ካረገው ቁም ነገር፣
“ግልገል” እንደተባለ - እንደሜጨ ይቅር።” (ገጽ 131)

ዐባይ ላደረሰው በደል በርግማን ብቻ የሚተው ሳይኾን ወደ ፊት ገባሮቹን በማልማት ያለመጋቢ ብቻውን እናስቀረውና ያኔ ሲመናመን እንዳሻን ወደፈለግንበት ቦታ እየመራነው እናስገብረዋለን በማለት ለመስኖ በመከተር ብድር መመለሻው ቀን እንደሚመጣም ይተነብያል፡-

አናሳ ብሄረሰብ - ሙብትን እንዳወጁ
ትናንሽ ጅረቶች - በየቀበሌያቸው ታግለው ሲደረጁ፣
አባይ ቀኑ ደርሶ - ድንጋዩን ታቅፎ እርቃኑን ሲዘረር
ኃይሉ ተመናምኖ - ለመሞት ሲያጣጥር፣
ሺህ፣ ሚሊዮን ዘመን እንዳላበገነን፣

በእያንዳንዱ ቀዬ - እንደ እውር ተመርቶ እናስታመዋለን!
ማን ያውቃል - አንድ ቀን? ... (ገጽ 132)

በዐባይ በደል በመመረር ከሚቀርበው ቁጭት ይበልጥ የከረረ እርግማን በሌሎች ግጥሞችም ተደጋግሞ ይስተዋላል። ጌትነት እንየው በ1994 ዓ/ም በጻፈው “አባይ” (2004 ዓ/ም) የተባለ ግጥሙ በነሐሴው ክረምት ከወላጆቹ አምባ ግንዱን ነቃቅሎ ጭኖ፣ ጥቁሩን ዐፈር አጋብሶ እንደ ሌባ ሲሸሽ ያየውና በዐባይ ድርጊት ያፍራል፣ ይጠላዋል፣ ይረግመዋል፡-

“ጨለማ ይዋጥህ፣ ተመንገድ ያስቀርህ
አይንህ ይፍሰስ” አልሁት። (ገጽ 92)

ዐባይ ግን በአውጋዡ የዋህነት አዝኖ፣ በርግማኑ ስቆና አፌዞበት በቆመበት ትቶት፣ የለመደውን ጓዙን ተሸክሞ ይጋልባል። ታዛቢውም ዐባይ ዐፈር አዝሎ በመጣ ቁጥር ቢራገምም ውጤት ያጣል፡-

ያን አባይ'ረግሜ፣ ዘወር ስል ደግሞ
ሌላ አባይ አየሁኝ አገር ተሸክሞ፤
እሱ ሲሄድ ደግሞ...
አሁንም ሌላ አባይ፣ ጥቁር አፈር ቅሞ
እሱ ሲሄድ ደግሞ...
አሁንም ሌላ አባይ አገር ተሸክሞ!
እሱ ሲሄድ ደግሞ...
እሱ ሲሄድ ደግሞ (ገጽ 93)

ይህ በስላቃዊ ትዕይንት መልክ የቀረበልን የዐባይ ተደጋጋሚ ዝርፊያና ለታዛቢው ውግዘት ቁብየለሽነት የሚጠቁመን ባዶ ቁጭት ፋይዳ እንደሌለውና ዐባይ "አገር ተሸክሞ" መጓዙን ከቀጠለ ወደ ፊት አገርየለሽ ስለምንኾን ከቃላት ያለፈ የተግባር መፍትሔ እንደሚያስፈልግ ነው።

እንደ ጌትነት ግጥም ሁሉ ዐባይን በሌብነት የሚወነጅለውና እርግማን የሚያወርድበት ሌላው ግጥም የአበባው መላኩ "አባይ" (1999 ዓ/ም) ነው። በዚህ ግጥም ውስጥ የዐባይ ወንጀል ዐፈር ወሃውን አግዞ፣ ባዕድ አፍቅሮ መኮብለሉ ብቻ አይደለም፤ ለሰው ስቃይ አይራሬነቱም ነው። እንደ ልብሴ በላይ "እንደ ስሞታ ለጣና"፣ በአበባው ግጥምም ሕዝቡ ዐባይን በቅኔ መወድስና በጉባኤ ቃና ሲከበው መቆየቱን፣ ፈለገ ግዮን፣ የጤግሮስና የኤፍራጥስ ወንድም፣ ገነትን ያጠጣ እያለ ለሺ ዓመታት ሲያወድሰው መኖሩን፣ ለዚህ ማስረጃም የመጽሐፍ ቅዱስን የዘፍጥረት ትርክት እና የጸጋዬን "አባይ" አልፎ አልፎ ይጠቃቅስና ሕዝቡ ሲራብ ዐባይን ቁብ ስላልሰጠው በጭካኔው፣ በክህደቱ፣ በስርቆቱ ይታዘበዋል። ሕዝቡንም በደለኛውን ዐባይ በከንቱ በማወደሱ በስላሽ ይሳለቅበታል፦

የኮብላይ ሌባ አመልህን
  ክፉ ጠባይህን ሳንገራ፤
ይኸው... አንተም ወደአልፈለጉህ
  ወደአልጠሩህ ቤት ስትሮጥ፤
እኛም ከነራባችን
  ላንተ መወድስ ስንመርጥ፤
ያው ዛሬ ላይ ደርሰናል...
ድህነትን በጀርባ አዝለን
  ጠኔን በጉያ አዝለናል፤ (ገጽ 53-54)

ዐባይ ለፈለቀበት አገር ሕዝብ አይራሬ ብቻ ሳይኾን ይባስ ብሎ ለትውልዱም መጥፎ አርአያ በመኾን ለስደት ስለዳረገው ይረግመዋል፦

እራሱ ሸፍቶ እንዳይቀር
  ሺ ዓመት ሙሉ ኮብልሎ፤
በጦሱ ስንቱን በክሎ

ካገሬ ልውጣ አስብሎ፤
ስንቴ በቁም ይግደለን
በሲፖል ምክሩ ደልሎ፤
አይ አባይ የጅህን ይስጥህ አንተንስ
የዘራኸውን ያቅምህ፤
ባንተ መከራ እንዳየንብህ
አንተንም አሳር ያሳይህ፤ (ገጽ 54)

ከርግማኑ ባሻገርም ኢትዮጵያን የወላድ መካን ያደረጋትን ዐባይን በግድ "ሰንገን" እና "ጠፍረን" (ማለትም ገድበን) እናስቀረው፤ የወንዝ ሽፍታን የማወደስ ወጋችንም ይቁም ሲል ጥሪ ያስተላልፋል።

ከአበባው ግጥም በተቃራኒ የበፈቃዱ ሞረዳ "አደራ" (1994 ዓ/ም) ስለ ዐባይ የሚነገረውን ብሂል የሚያስተባብል አስመስሎ ሀብት ከመዝረፍ የከበደ አደጋ ጥሎብን እንደሚጓዝ ይገልጻል፡-

"አባይ
አዳር የለው
ግንድ ይዞ ይጓዛል"
ይላል ብሂላችን።
አባይ ምኑ ሞኝ?
ይዞስ የሚጓዘው
ነፍስና ሥጋችን። (ገጽ 23)

ዐባይ ነፍስና ሥጋችንን ይዞ ይጓዛል የሚለው ጥልቅ ዘይቤአዊ አባባል ነው። ዐባይ የሚወስደው የሕዝቡን ህልውና ጭምር መኾኑንና መፍትሔውም እሱን ከመከተር ያለፈ መኾኑን ይነግረናል፡-

ጌታ ሆይ አደራ
ሥራ፣ ተዐምር ሥራ።...
...በሀገሬ ምድር ሠላምን አፅድቀው
...ታለመልም ዘንድም አባይን አድርቀው። (ገጽ 23)

አገሪቱ በዐባይ ምክንያት ለእልቂት እየተዳረገች ነው በሚል ፈጣሪ ዐባይን በማድረቅ ተአምሩን እንዲሠራ ገጣሚው ይማፀናል። ከአገሪቱ ሕዝብ ዐቅም በላይ የኾነ የሰላም እጦት፣ የእርስ በርስ ፍጅት ችግር በአገሪቱ ላይ ተጋርጧል ከሚል እሳቤ ተነስቶ ነው ዐባይ እንዲደርቅ አምላኩን የሚማፀነው። ዐባይ ቢደርቅ፤ ያኔ አገሩም ሰላም ይኾናል፤ ምድሩም ልምላሜን ይላበሳል ይላል ግጥሙ። አገሩ ለምን ሰላም አጣ? ይሄስ ከዐባይ ጋር ምን አገናኘው? ብሎ አንባቢ እንዲጠይቅ ግጥሙ ይገፋፋል። ዐባይ ከአገሩ አግበስብሶ የሚጓዘውን ሲሳይ የሚያስረክበው ለሱዳንና ለግብፅ ስለኾነ፣ ለሕይወታቸው ዋልታ የኾነው ዐባይ በኢትዮጵያ እንዳይገደብ እና እየጠራረገ የሚወስደው ውሃና ለም ዐፈር በመነጨበት አገር እንዳይቀር ኹለቱ ጎረቤቶች ደግሞ በውክልና ጦርነት ሕዝቡ

እርስ በርሱ እንዲፋጅና ሀብትና ጉልበቱን ለልማት እንዳያውል ያደርጋሉ[8] የሚል ውንጀላም አንባቢው ከታሪኩ ስለሚገነዘብ ለግጥሙ ይኸን ትርጓሜ እንዲሰጠው ይገፋፋል። ዐባይ ቢደርቅ ግን ዐፈሩም፣ ውሃውም ወደ ውጭ ስለማይጋዝና መሬቱም ከመራቆት ስለሚድን ይለማል። ኹለቱ ጎረቤት አገሮችም እኛን የሚያበጣብጡበት የህልውና ምክንያት ያጣሉ። ሰላም ሲወርድም ሕዝቡ በልማቱ ላይ ያተኩራል የሚል አንድምታ ግጥሙ አለው። ከሌሎች ብዙ ግጥሞች የሚለየውም ከዐባይ ችግር ለመታደግ እናልማው ብሎ ከመሚገት ይልቅ እስከናካቴው ህልውናው እንዲያከትም መማፀኑ ነው። በምጥን ቃላትና ቅኔአዊ አቀራረብ የሰላም እጦታችንና የድርቃችን መሠረታዊ መንስኤው ዐባይ ከኾነ እሱ ባይኖርስ ብለን እንድናስብ ይገፋፋናል። ዐባይ እስካለ ድረስ ሰላማችን ኹልጊዜም አደጋ የሚደቀንበት ስለኾነ፣ ሕዝቡ ገድቦት ውሃውን ቢያቆመውም ዞሮ ዞሮ የሱ ጥገኛ ከሆኑት አገሮች ጦርነትን መጋበዙ ስለማይቀር በዘላቂታዊ መፍትሔነት መለኮት-አከል ጣልቃ ገብነት ይጋብዛል። ግጥሙ በዐባይ ጦስ መታከትንና በወንዙ ላይ ተስፋ መቁረጥን ያንጸባርቃል።

ከዚህ በተቃራኒ የኤፍሬም ሥዩም "አባይ ፩" (2008 ዓ/ም) ሕዝቡን ነው ተጠያቂ የሚያደርገው፡-

> አባይ ወንዝ አይደለም ምራቅ ነው
> ምድረ-በዳ የሚከድን ረጅም
> የሀበሻን ተንኮል
> እግዜር ተጸይፎ - መሬት ላይ የተፋው። (ገጽ 30)

በዚህች ባለአራት ስንኝ እምቅ ግጥም ዐባይ ለሐበሾች መጥፎ ምግባር መገለጫ ትእምርት ኾኖ ነው የቀረበው። በዚህ ሚናው ራሱ ዐባይ እግዜር እንደ እርኩስ ነገር አንቅሮ ምድረ በዳ የተፋው፣ ለአገሩ የማይጠቅም ኾኖ ነው የቀረበው። በሌላ አኳያ ደግሞ ዐባይ በረከት እንኳን ቢኖረው ሐበሾችን በክፋታቸው ለመቅጣት ሲል እነሱ እንዳይደርሱበት ድንበር አሻግሮ ወደ በረሓ ያሽቀነጠረው ኾኖ ነው የተሣለው። ግጥሙ የኦሪት ዘፍጥረትን የግዮን ትርክት (ም.2፣ ቁ.10-13) እንደ ሌሎቹ በዐባይ ላይ የተደረሱ የእርግማን ግጥሞች ገለባብጦ ባናቱ ያቆመ ነው።

"አባይ ፪" (2008 ዓ/ም) በሚለው ግጥሙ ግን ኤፍሬም የበፊቱን የመረረ ውግዘቱን አለዝቦ ነው የሚያቀርበው። በዚህኛው ግጥም ዐባይ በተራ ውዳሴ የሚሸነገል ግብዝ፣ ዓላማና ርእይየለሽ፣ ለአገሩ ታማኝ ያልኾነና ለሕዝቡ ብሶት ልበ ደንዳና ኾኖ ተሥሏል። ነገር ግን "አባይ ቁ. ፪" ዐባይን በመውቀስ አይወሰንም። እንደ አበባው ግጥም ሕዝቡንም ዐባይን ያለግብሩ በማሞካሸቱ ይወርፋል። የሸንገላውን መቀጠል አግባብነትም ያጠይቃል። ዐባይንም በቃላት መደለሉ እንዲበቃው ይማፀነዋል፡-

---

[8] ግብፅ በዐባይ ውሃ ላይ ያላትን የበላይነት ለሁሌውም ለማስቀጠልና ኢትዮጵያ ወንዙን ለራሷ ልማት እንዳትጠቀምበት ለመከላከል ዐቅሟን በኢኮኖሚ፣ በወታደራዊ ኃይል፣ በፖለቲካና በዲፕሎማሲ በቀጥታና በተዘዋዋሪ ስታዳክም መቆየቷ፣ ለዚህም እንዲረዳት ለምሳሌ ለሱማሌ መንግሥት ወረራዎች፣ እንዲሁም ለሱማልኛ ተናጋሪ ተገንጣዮች፣ ለኤርትራ ተገንጣዮችና ለሌሎችም የማእከላዊውን መንግሥት በትጥቅ የሚቀናቀኑ ንቅናቄዎች ስትሰጥ የነበረው ዘርፈ ብዙ ድጋፍ በተለያዩ ተመራማሪዎች ተዘግቧል። ለምሳሌ ከነዚህ ውስጥ የጊልክስ (1994 እጎአ፣ ገጽ 722-726)፣ የኃይሉ (2001 እጎአ፣ ገጽ 140-167)፤ የተስፋዬ 2002 እጎአ፣ ገጽ 1542-1546)፣ የተፈሪ (2004 እጎአ፣ ገጽ 144-146) እና የካርልስ (2006 እጎአ፣ ገጽ 44-45) ጥናቶች ይገኙባቸዋል።

ዐባይ ተረት ብቻ
የተራ ዘፋኞች የቃል መጫወቻ
(ሆነህ ቆይተሃል)
እስከመቼ ድረስ
በወንዝ የሚዘረፍ የቃላት ጨዋታ ይሄ ሕዝብ ይችላል? (ገጽ 124)

....

ያለቦታህ ማጌጥ ያላገርህ መንገሥ
የራስ ልጅ ሲያነባ የጎረቤት ማበስ
ባልሆኑት መወደስ ባልገነቡት መግነን
ዘፈን
የውሸት ዘፈን አባይ ግዮን መባል
(ባከህ ይበቃሃል) (ገጽ 125)

“አባይ ግዮን መባል”ን ከውሸት ዘፈን ጋራ በማመሳሰል ዐባይ በመጽሐፍ ቅዱስ የተሰጠውን ከገነት የመመንጨትና ገነትን የማጠጣት ክብርና ሞገስ እና ከዚሁ ጋራ ተያይዞ በደገኛው ክርስቲያን የኢትዮጵያን በእግዚአብሔር የመመረጥ፣ የውሃውንም ፈዋሽነት የዘመናት ትርክት ያጣጥለዋል። ይሄ ከገነት መነጨ የሚል ተረት የሚነገርለት ዐባይ ሕዝቡን ሲያስለቅስ የኖረ ከሃዲ እንደ ነበር፣ የዐባይ ትሩፋት ለመነጨበት አገር አለመኾኑን በመግለጽ ከአሁን በኋላ ይሄን በደል ሕዝቡ ለመሸከም እንደማይፈልግ ለዐባይ ይነግረዋል፡-

የዚህን ምስኪን ሕዝብ...
ፈገግታና ሳቁን ከፊቱ ላይ ጠርገህ በንባ ተክተሃል
የወንዝነት በደል...
ያለ ሐገር መብቀል... ያለ ሐገር ማብቀል
ከሚመነጩበት ከሞሉበት መጉደል
ሕዝቡ ስለበቃው...
ግፉ ሥለገፋው ይበቃል ... ብሎሃል
(ይበቃኛል በለው)...
ይበቃሃል ግዮን
ሳይፈፅሙ መጓዝ ያለ ሕልም መፍሰስ
እዚህ ደም ማስለቀስ እዚያ እንባን ማበስ
የራስ ጎጆን ንቆ...
መሠረት በሌለው ..ባሸዋ በፀና በሠው ቤት መኮፈስ (ገጽ 125)

በግጥሙ ውስጥ ዐባይን “ተኛ”፣ “ጥቂት ጋደም በል”፣ “ጥቂት አረፍ በል” በማለት እንዳዝማች የሚቀርቡት ተማፅኖዎች የዐባይን መገደብ በተራ ቋንቋ ከመግለጽ ይልቅ በዘይቤአዊ ዘዬ ለመጠቆም የተደረገ ስልት ነው። ዘይቤው ከዚህም አልፎ ሰው ካልተኛ ሕልም እንደማያይ ሁሉ ዐባይም እንዲሁ ከአገር አቋራጭ ጉዞው ታቅቦ፣ በአገሩ መሬት ተንጋልሎ እንዲያልም ይነግረዋል፡-

የተራ ገጣሚ የቃል መጫወቻ - ሆነህ ቆይተሃል
አሁን ግን ይበቃል...
ሕልም አለብኝ በለው...
እናም ሕልሜን ላልም እያሸለበኝ ነው በልና ተናገር
የወንዝነት በደል እንደበቃህ መስከር...
ኢትዮጵያ ሰማይ ላይ ዐይኖችህን አትኩር።
ጥልቅ እንቅልፍ እስኪሆን
በጀርባህ ተኝተህ ከዋክብቶች ቁጠር (ገጽ 126)

የዐባይ ሕልም ተራ ሕልም አይደለም — ርእይ ነው፤ ለሕዝቡ ብሩሕ ሕይወትን የመታደግ ርእይ። ይኸን ደግሞ ለዘመናት እንደ ለመደው ድንበር አቋርጦ በመሰደድ ለመነጨበት አገር እውን አያደርገውም። የመተኛት ዘይቤው ፍቺ የዐባይን ወደ ባዕዳን አገር መንጎድ ማቆምን፣ በመነጨበት አገር ውስጥ በግድብ ተከትሮ፣ ውሃው ሰው ሰራሽ ሐይቅ ሲሠራና ለልማት ሲውል ነው። ለዚህም ነው ገጣሚው እየደጋገመ ዐባይን ሕልም አልባ፣ የመነጨህበትን አገር ስለምታለማበት፣ ሕዝብህን ስለምትታደግበት፣ የሕዝብህን የጉስቁልና እንባ ስለምታብስበት ኹኔታ ምንም ርእይ የሌለህ ኾነህ አትፍሰስ የሚለው፡-

ለብዙዎች እረፍት ...
ከመነጨህበት መሬት ላይ ተንጋለል
"ለምን?"... ብትል...
በተፈጥሮም ትእዛዝ...
አንዳንዴ ለማለም መተኛት ግድ ይላል
ውብ አበቦች ፍጠር...
አረንጓዴ ቅጠል የተስፋ ሀገር አልም... (ገጽ 124)

ይህ የኤፍሬም ግጥም ትኩረቱ ራሱ ዐባይ ላይ ኾኖ ባለበጎ ርእይ እንዲኾን ቢማፅንም በተዘዋዋሪ ርእዩን እውን እንዲያደርግ ለሕዝቡ የተላላፈ ጥሪ ነው። ሐሳቡ የሚቀርበው ግን በብዙዎቹ የቅስቀሳ ግጥሞች እንደሚታየው ያልተመሠጠሩ ቃላትን በመጠቀም አይደለም። በዘይቤአዊ ዘዬ፣ በዐባይ ላይ ወቀሳውን፣ ተማፅኖውን፣ ወዮልህን እያፈራረቀ፣ እያዋዛ ነው የሚያቀርበው፡-

አባይ ያገር ሲሳይ
አባይ የሕዝብ ፀሐይ... ብቶን ይሻልሃል ብቶን ይበጅሃል። (ገጽ 126)

"የሕዝብ ፀሐይ" የሚለው አሻሚ አባባል ከኹለት አኳያዎች ሊተረጎም ይችላል። አንዱ በዐባይ መገደብ ሕዝቡ ቀን እንደሚወጣለት፣ በልማት፣ በእድገት ኑሮው እንደሚሻሻል የሚጠቁም ነው። ኹለተኛው ደግሞ ግድቡ በሚያመነጨው የኤሌክትሪክ ኃይል የብዙኃኑን ቤት የሙብራት ተጠቃሚ በማድረግ በማገዶ ላይ ያለውን ጥገኝነት እንደሚያስቀርለት፣ ይህም በተዘዋዋሪ የአካባቢን መራቆት በመቀነስ "ውብ አበቦች ፍጠር.../ አረንጓዴ ቅጠል የተስፋ ሀገር አልም..." የተባለውን እውን ማድረግን የሚጠቁም ተደርጎ ሊተረጎም ይችላል። ወንዙ ተከትሮ ውሃው

በመስኖ ቢሠራጭ ደግሞ አካባቢውን በምርትና በልምላሜም ይሞላዋል። ስለዚህ ከዚህ ቅኔያዊ አቀራረቡ በመነሳት የኤፍሬም "ዐባይ ቁ. ፪" ዞሮ ዞሮ ለርእይ ትግበራ ጥሪ ቢኾንም መመራመርን እምብዛም ከማይጋብዙት ዝርው የቅስቀሳ ግጥሞች በአንጻራዊነት የተሻለ አንባቢን የመማረክ ኃይል አለው። "አባይ ቁ. ፩" እና "አባይ ቁ. ፪" የቀረቡበት መድበል ከግድቡ ግንባታ ጅማሮ በኋላ የታተመ ቢኾንም ግጥሞቹ ምናልባት ከሕዳሴው ግድብ ጅማሮ በፊት የተገጠሙ ሳይኾን አይቀርም። አለዚያ ግድቡ በመገንባት ኺደት ላይ እያለ ዐባይን ለሕዝብ ፀሐይ ብትሆን ይሻልሃል የሚለው ምክር-አዘል ማስጠንቀቂያ ፋይዳ አይኖረውም። የዐዋጁን በሹክሹክታ የማውጋት ዓይነት የመሸበት ቅስቀሳ ይኾናል።

ቀደም ብለው የቀረቡት ግጥሞች በተለያየ ድምፀት ዐባይን በበዳይነት እና በከዳተኛነት ቢከስሱትም ዞሮ ዞሮ የሚያጠነጥኑት ዐባይ ይልማ የሚል ጭብጥ ነው። ከነዚህ ባቀራረቡ በመጠኑ የሚለየው በ2000 ዓ/ም የተደረሰው የደስታ ተከስተ "ተስፈኞች" (2002 ዓ/ም) ነው። ግጥሙ ትናንት ባለማወቅ "አባይ ...ያገር ሲሳይ" እያልን ስናዜምለት የነበረው፣ ዛሬ አገር ንዶ ዐፈር በማጋዙ ያበገነን ዐባይ፣ ነገ ከስንፍና አዚም ነቅተን ስናለማው የፍሬው ተቋዳሽ እንኾን ይኾናል ይለናል፦

ነገ...
የታሰርንበት አዚም ተፈትቶ፣
የዛለው ክንዳችን ጠንክሮ፣
የሥራ ባህላችን ዳብሮ፣
አባይም ሲፏልል ማሳ ለማሳ፣
ዕናየው ይሆናል...
በእርሱ ያለማነውን፣
እሸት ጠግበን ስናገሳ!!
ያድርግልን...!! (ገጽ 81)

6. **ተጠየቅ ደገኛ! ይሟገታል ዐባይ**

በአምስተኛው ንኡስ ክፍል ውስጥ የቀረቡት 14 ግጥሞች ዐባይን በበዳይነትና በከዳተኛነት በተለያየ ድምፀት የሚከስሱ ናቸው። በነዚያ ግጥሞች ውስጥ ዐባይ በሰውኛ ዘዴ ዋና ተዋናይ፣ አድራጊ፣ ፈጣሪ፣ ሰጪ፣ ነሺ፤ በአንጻሩ ደግሞ ሕዝቡ አንድም እጁን አጣጥፎ ተመልካች፣ አለዚያም በከንቱ አወዳሽ፣ ወይም ምንም ጥረት ሳያደርግ መናን ከዐባይ ጠባቂ፣ ዕቅም የለሽ አልቃሽ፣ ወይም ተበዳይ ከሳሽ ኾነው ነው በአብዛኛው የተሣሉት። "ዐባይ ውኀዬ-ውኀ!" በሚለው የሰይፉ መታፈሪያ ግጥም ዐባይ በስደተኛ፣ በከዳተኛ እና በባርያ ተመስሎ በሱዳን ሲጓዝ ግን በተራው እየከፋው ነው፦

መልኩ ድፍርስርስ
ዐባይ
ፊቱ ጥንስስ
ግምባሩም ክስክስ (ገጽ 307)

ዐባይ ፊቱ ላይ መከፋት የሚታይበት ለምንድነው? አንደኛ፣ ያለውዴታው የሰው መሬት በማድለቡ፣ ኹለተኛም፣ አንድ ቀን ያለአግባብ በከህደት ወንጀል መጠየቁ እንደማይቀርለት ስለተገነዘበም ነው። እናም ይህን ኢፍትሓዊ ውንጀላ ለመቋቋም እሱም በፈንታው ከሳሾቹን እንደሚፋረዳቸው ይናገራል። ይሄ የሰይፉ ግጥም ዐባይ ወቃሾቹን መልሶ የሚከስበት የመጀመሪው ግጥም ሳይኾን አይቀርም።

የሚናገር መሰለኝ አማርኛ
ዐባይ የኛ
እና የሚለኝ
እይ እሰጣለሁ
ሳልወድ
የሰው መሬት
--
አንድ ቀን እከሰሳለሁ
በእርግጥ
አይቀርም
ወይ የሥራኸው እባላለሁ፤
እኔ ባልከሳቸው
መልሼ
ስንፍናቸውን አንግሼ። (ገጽ 308)

ስለዚህ ዐባይን የባዕዳንን በረሓ ለማልማት ያስገደደው ዋናው ምክንያት በመነጨበት አገር በነገሠው ስንፍና መመረሩ ነው። “ስንፍናቸውን አንግሼ” የሚለው በሕዝቡ ዘንድ የስንፍናውን መንሠራፋት፣ ማለትም ዐባይን እንደ ግብፅ ሕዝብ ለማስገበር፣ ለማሠልጠን፣ አልምቶ ለመጠቀም ትርጉም ያለው ጥረት አለመኖሩን ጠቋሚ ነው።

በሰይፉ ግጥም ውስጥ ለዘብ ብሎ የቀረበው የዐባይ ወቀሳ “ምን እንበለው ለዐባይ” (2002 ዓ/ም) በተባለውና በ1979 ዓ/ም በተደረሰው የፀሐይ መልአኩ ግጥም ከረር ብሎ ይቀርባል። በግጥሙ ውስጥ ዐባይ የሚበሳጨው ሕዝቡ የራሱን ከፍተኛ ስንፍና ዘንግቶ ለችግሩ እሱን በመክሰሱ ነው፡-

ፍቅሩን አንድነቱን ወኔውን ተሰልቦ
ዳቦ እየረገጠ የሚለምን ዳቦ
አግበስብሰህ ወሰድከ አፈርና ውሃ
አለማህ አጠጣህ የባዕድ በረሃ
ይለኛል አበሻ እያብጠለጠለ
በዕድሜው ላይ ተኝቶ ጊዜ እየገደለ። (ገጽ 72)

ልክ በሰይፉ ግጥም ውስጥ እንደቀረበው ኹሉ እዚህም ዐባይ የሰው አገር ማልማቱን አይክድም፤ በደለኛነትም አይሰማውም። ወቃሾቼ ዕውቀትና ብልሃት አጥታችሁ፣ ያለኝን ሀብት ምንነትና እኔን መንከባከቡን ስላላወቃችሁበት ብልጦቹ ቢወስዱኝ ጥፋቱ የናንተ ነው ሲል ይሟገታል ዐባይ፡-

አዎ ወስደውኛል ብልጦቹ ጀግኖቹ ምቾቴን ጠብቀው
ሕይወትና ሲሳይ እንደምሆን አውቀው።
እኔም መሰሎቼም በረከት ታቅፈን
እናንተ እስክትነቁ እንጄዳለን አልፈን። (ገጽ 73)

የፀሐይ ግጥም ሱዳኖችንና ግብፆችን ከብዙዎች በተለየ በበጎው ነው የሣላቸው — ዐዋቂ፣ ብልጥ፣ ጀግና አድርጎ። ዐባይም ተንከባክበው ስለያዙት በኼደበት አገር ቅሬታና ባይተዋርነት አይሰማውም። ሲሳዩን ቢለግስም ጉዞው የተዝናኖት ነው። ግን ዐባይ በወቃሾቹም ላይ ቂም አይቋጥርም። ወደ ፊት ለሐበሻም ሲሳዩን የሚያቋድስበት ጊዜ እንደሚመጣ ተስፋውን ከምክር ጋራ ያጋራቸዋል፡-

ይልቅስ ሀበሾች ወሬውን ትታችሁ
ለልማት ለሥራ ራዕይ ሰንቃችሁ
ላኩብኝ ቀጠሮ ቂም ነገር ይዛችሁ።
እስከዚያው ነጓጅ ነኝ ብልጣ ብልጦቹ አገር
እነሱ ሊበሉኝ እኔ ልንሸራሸር። (ገጽ 73)

ግጥሙ የሚደመደመው በርእሱ የቀረበውን ጥያቄ በመድገም ሐበሾች ዐባይ ላቀረበው ወቀሳ መልስ መስጠት እንዳለባቸው በሚያሳስብ (በተዘዋዋሪም የልማት ጥሪን በሚያቀርብ) መልክ ነው።

ዐባይ ካሳሾቹን የሚወቅስበት ሌላው ድርሰት አያልነህ ሙላቱ በ1983 ዓ/ም ደርሶት በ1992 ዓ/ም በኢትዮ-ኤርትራ ጦርነት ወቅት ለመድረክ አብቅቶ ያሳተመው "ሾተላይ" የተባለ ባለአንድ ገቢር ተውኔት ነው። ተውኔቱ በዋናነት ሻዕቢያ፣ ሕወሐት/ኢሕአዴግ፣ ደርግ እና ኢትዮጵያ በኅብረ አምሳላዊ (allegorical) መልክ የተወከሉበትን የእርስ በርስ ጦርነት ይተርካል። በአምስተኛው ትዕይንት ውስጥ ግን ስለ ዐባይ ጦስም ይነግረናል። በዚህ ክፍል የጦርነቱ ሰለባ የኾኑት ሙታን በኅብረ ዘማሪያን (chorus) መልክ ጦርነቱን ከጀርባ ኾነው የሚቆሰቁሱትን ወገኖች ይከስሳሉ፡-

እናት አንቺን እርስ በእርስ ሊያባሉሽ...ጎረቤቶችሽ መጡልሽ።
ልጆችሽ ታደልን ጠመንጃ... ለእኛ በእኛ መፋጇ።
ለውጪ ጠላት ባትመቺ... ሊያጠፉሽ ነው አንቺን ባንቺ። (ገጽ 18)

እነዚህ ጎረቤቶች ለኢትዮጵያ ጥፋት እንዲተጉ የሚገፋፋቸው ዋናው ምክንያት የዐባይ ወንዝ መኾኑን በመግለጽ በአገር ክህደት ኅብረ ዘማሪያኑ እንደሚከተለው ይወነጅሉታል፡-

የእኛ ጠብ ጫሪ ደባይ፤ የእኛን ውሃ-አፈር አቀባይ
እርሃብ ቸነፈር ለእኛ አዳይ፤ ለእኛ ጠላቶች ዋና ሲሳይ፤
ትላንትም ዛሬም አባይ።
እኛን በእኛ...የሚዋጋ፤ እኛን በእኛ የሚያናጋ
የውጭ አሊጋ የውስጥ ቀጋ፤ ለኛ ጭንቀት ...ለባዕድ ፀጋ።
ቋሚ ችግር ለእኛ ሠፈር፤ አንት ያባይ ውሃ ያባይ አፈር።
የእኛነታችን አጥፊ ጠላት፤ ያባይ ወንዝ ነህ! ያባይ ሙላት። (ገጽ 57)

ኢትዮጵያን የምትወክለዋ እናትም ዐባይን ዐፈር-ውሃዋን ብቻ ሳይኾን የደም ግብር እያስገበረ የራሱን አገር አድርቆ በረሃብ እያሰቃየና እያደኸየ ባላንጣዎቿን አስከብሮ ስላስጠቃት ትኮንነዋለች። የዐባይ ቆሌም መጥቶ ከቀረበበት ውንጀላ ራሱን ይከለከላል። ችግሩ ያለው ከልጆቿሿ ነው፤ እርስ በርስ አልተባበሩም፣ እኔን ለማልማት አልጣሩም፣ ገድበውኝ የኤሌክትሪክ ኃይል አላመነጩም ይላታል። ዐባይ ቢገደብ ስለሚያመጣው አደጋ ሥጋቷን ስትነግረውም ያጣጥልባታል፡-

| | |
|---|---|
| አሮጊቷ፡- | ያንገራገረን ግን አለ... የፎከረ! የሸለለ!<br>“ካባይ አንድ እፍኝ ውሃ ቢነሳ...<br>አባይን ያህል ደም ይፈሳል” ያለ ...[9] |
| ቆሌ፡- | ቢልስ! አንቺን እና! ምን አስፈራሽ... መብትሽን ሰጥተሽው ጭራሽ።<br>ባለቤቷ አንች ተቀምጠሽ... ሐብትሽን ለሌላ ሰጥተሽ።<br>ከሩቅ አንችን እያስፈራሩ... ውሃ አፈር እያስገበሩ ቁጭ አደረጉሽ በብያኔ<br>... በርሃብ፣ በድርቅ! በጠኔ!<br>ጥፋቱ ያንች? የነሱ? ወይስ የኔ? (ገጽ 60-61) |

እናም ዐባይ “የመጣው ቢመጣ በይና በኔ ዐፈር-ውሃ መስኖ አልሚ፣ ኃይል አመንጭተሽ ተጠቀሚ፣ ከዚያ በኋላ ያን እየበላሽ የመጡብሽን ተፋለሚ” በማለት እርግማኑን ትታ፣ ፍርሃቷን አራግፋ ለልማት ታጥቃ እንድትነሳ ምክሩን ለግሶ ላይመለስ ትቷት ይኼዳል። ስለዚህ ተውኔቱ ዐባይንና ጎረቤት አገሮችን ከማማረር በመኻላችሁ ሰላም በማስፈን ወንዙን ከነገባሮቹ ለማልማት ቆርጣችሁ ተነሱ ይላል።

---

[9] እነዚህ ደራሲዎችና ሌሎችም ቀደም ያሉት ኹለቱን ጎረቤቶች በዐባይ ምክንያት በደመኛ ባላንጣነት በተደጋጋሚ የሚከስሱት ያለምክንያት አይደለም። ግብፅ በ19ኛው ምዕተ ዓመት ዐባይን ለመቆጣጠር ስትል ኢትዮጵያን በተደጋጋሚ ወርራ በሽንፈት ብትመለስም ከዚያ ወዲህ የነበሩት መሪዎቿ (ከጋማል አብደል ናስር እስከ ዛሬው አብደልፈታህ ኤል-ሲሲ ድረስ) ኢትዮጵያ ዐባይን ብትገድብ ወይም “አንዲት ጠብታ ውሃ ብታስቀር” በጦር ኃይል ለማጥቃት በአደባባይ መዛታቸውና መንግሥታቸውም ከኃይለ ሥላሴ ዘመን ጀምሮ ኢትዮጵያን ለመበታተን ለዐማፅያን በኅቡእና በግልጽ ድጋፍ ማድረጉ በተለያዩ ጸሐፊዎችና በመገናኛ ብዙኃን በስፋት ተዘግቧል። (ኃይሉ 2001 እጎአ፣ ገጽ 140-167፤ ተስፋዬ 2002 እጎአ፣ ገጽ 1542-1546)። ጄነራል አልበሽርና የቀደሙት የሱዳን መሪዎችም የአፄውንም ኾነ የደርግን መንግሥት ለመጣል ለሚፋለሙ የኢትዮጵያ ዐማፅያን እስከ ኤርትራ መገንጠል ድረስ ሙሉ ድጋፋቸውን ሲሰጡ እንደ ነበር የአደባባይ ምሥጢር ነበር። (የአብርሃም ያየህና የገብረ መድኅን አርአያ ቃለ ምልልስ 1982 ዓ/ም፣ ገጽ 36-38፤ ፍስሐ ደስታ 2008 ዓ/ም፣ ገጽ 428-431)

የመሠረት አበበ "ደንበሌ" (2000 ዓ/ም) ከላይ ከቀረቡት የፀሐይ መልአኩ ግጥምና ከአያልነህ ሙላቱ ተውኔት ለየት ባለ መልክ ያባይን ወቀሳ ያቀርባል። ይህ ኀብረ አምሳላዊ ግጥም በኹለት ተፋቃሪዎች መካከል ያለ የቃላት ልውውጥ ሲኾን ወንድየው ዐባይን የወከለችውን ሴት "የኔ ቅባ ቅዱስ ነይልኝ ደንበሌ" እያለ ያወድሳታል። እሷም ቁልቁል ወራጅ መኾኔን እያወቅህ በባዶው ከምታወድሰኝ ብትገድበኝ ኖሮ ነጭ እንጀራ ትበላ ነበር፤ ነዳጅ ሽማችም ባልኾንክ ነበር በማለት ውዳሴውን ታጣጥልበታለች። የዚህ ፍሬ ነገሩ ዐባይ ቢገደብ ለኃይል ፍጆታ የሚያስፈልገውን ነዳጅ ከውጭ ከመሸመት በተገደበው የኤሌክትሪክ ኃይል መጠቀም ይቻል ነበር ለማለት ነው። ወንድየው ምድሩን እየሸረሸርሽ ሸለቆ ስላደረግሽ ለመገደብ አስቸገርሽ፤ ከአረንጓዴ ምድር ወደ ጨውማ ባሕር መኼድ ጎመጀሽ፤ ስለዚህ በፈለግሽበት ኺደሽ ቅሪ፣ ለእኔም እሱ ያውቅልኛል በማለቱ ትወቅሰዋለች፡-

እሱ ያውቃል አትበል እሱ አውቆ ፈጥሮሀል
በሰው የሚሠራን መሥራት ይገባሀል
ደንበሌ አትበለኝ በለሰለሰ እጅሀ
በሥራ መንገድ ነው እኔ የምቀርብሀ
የአባይ ወንዝ ሸለቆ በራፉ ይዘጋ
አይሁን ለሀገር ጉዳት በደንበሌ አደጋ። (ገጽ 118)

ማምረሯን ሲያይ እሱም ተስፋው ያንሰራራና ሐሳቧን ይጋራል፤ ዐባይን ገድበን እናስቀረው ሲሉም በአንድነት ጥሪ ያስተላልፋሉ። የዐባይን ጥቅም ማወቅ የፈለገም ከግብፅ ይማር ይላሉ። ግጥሙ ዐባይን ለመገደብ ሕዝቡ እንዲተባበር ቅስቀሳ ከማድረግ ባለፈ ግብፅን በጠላትነትም ይፈርጃል። ዕጣ ፈንታዋና ሕልውናዋ በኢትዮጵያ እጅ ያለ መኾኑንም በዛቻ ያስገነዝባል። ጭብጡ በጋራ የመጠቀም ሳይኾን የግብፅና የኢትዮጵያ ጥቅሞች ተጻራሪና የማይጣጣሙ ኾነው የቀረቡበት ነው። "የእስካሁኑ ይብቃው" የሚለው አሻሚ ቃልና ግብፅን ሀገራችንን የበጠበጠ ዲያብሎስ አድርጎ የማቅረቡ አንድምታ ይህንኑ የሚያሳይ ነው። አልፎ ተርፎም ዐባይን ብቻ ሳይኾን ገባሮቹንም በመጥለፍ ሀገሪቱን ምርት በምርት ማድረግ እንደሚቻልና በዚህ ጉዳይ ውይይት እንዲኖር የሚጠይቅን ዜጋ ኹሉ ለግል ጥቅም ያደረ የሀገር ከሃዲ አድርጎ በማቅረብ የተለየ ሐሳብን አፈናም ያራምዳል፡-

በዚህ የሚያቅማማ የሚል እንዎያይ
የጠላት አጋር ነው የግል ጥቅም የሚያይ
ራስን እየሼጡ በትንሽ ጥቅማጥቅም
ከጠላት መወገን ሀገር መጉዳት ይቁም (ገጽ 119)

በዚህ ንኡስ ክፍል ቀደም ሲል ያየናቸው ግጥሞች ውስጥ ለቀረበበት ክስ መልስ ሰጪው ራሱ ዐባይ ነው። የትእግስት ጌታቸው "የአባይ ሸኝት" (2000 ዓ/ም) ውስጥ ግን ሕዝቡን ወቃሿ ተራኪዋ ናት። እንደ ሌሎች ዐባይን እናልማው ግጥሞች ዐባይ ያገሩን ሀብት ለባዕድ ማስረከቡ ቢነገረንም እንደ ሰይፉ "ዐባይ ውኀዬ-ውኀ!" ግጥም ኹሉ እዚህም ዐባይ ይህን የሚያደርገው እየከፋው ነው፡-

የኛ ወርቅ ለሰው ሲፈስ
ለምን ፈራን ለመቋደስ
ዋይ እያለ ሲፈስ
እያነባ እየጮኸ
እሰው አገር ሲገሰግስ (ገጽ 5)

ግጥሙ ዝም ብሎ ዐባይን እንዲሰደድ የተወውን ሕዝብ የሚወቅስ ነው። ከሌሎቹ ልዩነቱ ዐባይ መሰደዱን በደስታ ሳይኾን በጩኸት፣ የድረሱልኝ ዋይታ እያሰማ[10] መኾኑና እኛ ደግሞ አካኼዱን ከቱሪስቶች ጋራ እያዳነቅን መሸኘታችን ነው በማለት ነው ወቀሳውን በአገሬው ሕዝብ ላይ የሚያቀርበው።[11] ስለዚህ የዐባይን ወርቅ ለመካፈል መፍራት የለብንም፤ መትጋት አለብን ነው የሚለው። ሌላው ልዩነቱ የሰዉንም ስደት ከዐባይ ጉዞ ጋራ ማመሳሰሉ እና ራሳችን ችላ ያልነውን እንደገና ዞረን ዐባይ ጥሎን ኼደ ብለን ስሞታ ማሰማታችን አግባብ አይደለም ይለናል፡-

በአየር ሰውን
በምድር ውሃ እየሸኘን
አባይ አባይ
ጥሎን ሄደ እንላለን። (ገጽ 5)

---

[10] በትእግስት ግጥም የቀረበው የዐባይ ጩኸትና ዋይታ በሌይኩን ብርሃኑ (ዶ/ር) "ፀፀት" የተባለ ልቦለድ ውስጥም ይደገማል። በልቦለዱ ውስጥ የዐባይ ወቀሳ የሚቀርበው በራሱ በዐባይ ሳይኾን በዋናው ገጸ ባሕርይ በፅዳል ሐሳብ ውስጥ ነው። ፅዳል የዐባይ ፏፏቴን አወራረድ ሲመለከት ዐባይ ለወገኖቹ ሳይታደግ ለሰው ሲሳይ በመኾኑ በብስጭት እንደ ነደደ እና ራሱን ከገደል ላይ እንደ ወረወረ አድርጎ ያስባል። ዐባይ ፈዋሽ ጠበል በመኾኑ ሕዝቡ ለመጠጥ፣ ለንጽሕና ወይም ለግብርና እንዳይገለገልበትና ቅድስናውን እንዳያራክሰው በማለት ሕዝቡንም ገዢዎቹንም በመገዘት የግብፅ ጳጳሳት ለአገራቸው ወግነው ኢትዮጵያውያን ዐባይን እንዳያለሙ በሃይማኖት ስም ሲያከላክሉ እንደ ቆዩ ሌላው ገጸ ባሕርይም ይናገራል። (ይህን ቅንጭብ ትረካ የያዘውን ሁለት ገጽ የልቦለዱ ክፍል በኃይሉ (2001 ዓ/ም ገጽ 163-65) ጥናታዊ መጽሐፍ ውስጥ ተጠቅሶ ነው የዚህ ጽሑፍ አቅራቢ ያየው እንጂ ሙሉውን ልቦለድ ለማንበብ ዕድል አላገኘም።)

[11] ብዙዎቹ ሕዝቡን በስንፍና የሚወቅሱ ድርሰቶች ከአልጋ ወራሹ ራስ ተፈሪ መኮንን ጊዜ ጀምሮ ዐባይንና መጋቢ ወንዞቹን ለማልማት ወይም ጣና ሐይቅን ጨምሮ በነዚህ ላይ የኢትዮጵያን ጥቅም ለማስከበር ላደረጉት ጥረት ዕውቅና አይሰጡም። ይህም ምናልባት ጥረቶቹ ጎልተው በሕዝብ ግንዛቤ ውስጥ ስላልሰረጹ ሊኾን ይችላል። ዐባይ ያለመጋቢ ወንዞቹ እስከ ዛሬ ያለውን የኢኮኖሚ ፋይዳና ማእረግ እንደማያገኝ የግብፅንና የሱዳንን ያህል ሁሉም ሕዝብ ላይረዳም ይችላል። ለምሳሌ በ1925 ዓ/ም እንግሊዝና ጣሊያን የኢትዮጵያን ፍላጎት ሳይጠይቁ ስለ ጣና ሐይቅ ልማት ስምምነት ሲፈራረሙ አልጋ ወራሹ ራስ ተፈሪ መኮንን ለዓለም መንግሥታት ማኅበር ተቃውሞዋቸውን አሳውቀዋል። በ1927 ዓ/ም ደግሞ አንድ የአሜሪካን ኩባንያ በ20 ሚሊዮን ዶላር የጣና ሐይቅን ለመገደብ ጥናትና ዕቅድ እንዲዘጋጅ ኢትዮጵያ ብትዋዋልም እንግሊዝና ግብፅ በተናጠል ባደረጉት ስምምነት በጣሉት ገደብ ምክንያት ሳይተገበር ቀርቷል። ጥቁር ዐባይን ለኤሌክትሪክ ኃይልና ለመስኖ ለመጠቀም በኢትዮጵያ ጥያቄና በአሜሪካ ትብብር ከ1958-64 ዓ/ም ሰፊ ጥናት ተደርጎ ነበር። ጥናቱ ዲዴሳ፣ ዳቡስ፣ በለስና ግልገል ዐባይንም ለመስኖና ለኤሌክትሪክ ማመንጫ እንዲውሉ ያካተተ ነበር። ነገር ግን ወጭውን ለመሸፈን በገንዘብ እጥረት (ግብፅ ብድር እንዳይሰጥ ጫና ስለምታደርግ) እና በኢትዮጵያ ውስጥ በተፈጠረው የፖለቲካ አለመረጋጋት ምክንያት ሳይተገበር ቀረ። ኾኖም በፊንጫ ወንዝ ላይ በኋላ (በደርግ ጊዜ) የኤሌክትሪክ ማመንጫ ግድብና የመስኖ ፕሮጀክት ሊተገበር ችሏል። (ኃይሉ 2001 ዓ/ም፣ ገጽ 120-21፣ 149-51)

እንደ ትእግስት ግጥም ሁሉ ነቢይ መኮንን በ1993 ዓ/ም የገጠመው "ይልቅ ዐባይ ጨዋታ አምጣ" (1999 ዓ/ም የታተመ) በዐባይ ላይ ለቀረበው ወቀሳ መልስ ሰጪው ዐባይ ሳይኾን ተራኪው ነው፤ ወቀሳውም ሕዝቡ ላይ ያነጣጠረ ነው። በዚህ ግጥም የሐበሻ ወግና ተረት፣ የዐባይ መወድስ ቅኔ (የጸጋዬ ገ/መድኅንን ጨምሮ) ተደረማምሶ ለሐበሻ ስንፍና፣ ለሐበሻ ሐሞት መፍሰስ መሳለቂያ ኾኖ ቀርቧል፦

"ላገሬ ውሃ አብቃኝ" ይላል፣ አበሻ ፀሎቱን ሲያደርስ
ውሃውን በጧት ሸኝቶ፣ ማምሻውን በድርቅ ሲያለቅስ
"ላገሬ አፈር አብቃኝ" ይላል፣ አበሻ ፀሎቱን ሲያደርስ
አፈሩን በዐባይ አንቀልባ፣ ጭኖ ልኮ ግብፅ ሲፈስ
"የመቃብር አፈር" ይላል፣ ይለምናል በቁም ፀሎት
በአገር አማን ሲያንቀላፋ፣ አገር-ምድሩን ውሃ ወስዶት፤
ዐባይ ንገረኝ በሞቴ — ይሄ አሁን አማርኛ ነው?
"ግንድ ይዞ ይዞራል" አሉኝ "ዐባይ መኖሪያ ሳይኖረው"
የግብፅ አልቤርጎ የት ሄዶ ከነግንዱ የሚያስተኛው?
ለምለም ቁጠማ ጎዝጉዞ፣ "አብሽር!" "ተማም!"
ብሎ እሚያቅፈው። (ገጽ 139)

ግጥሙ በዐባይ ውሃና ዐፈር ግብፅ ስትጠቀም፣ በአንጻሩ ሐበሻ ወጉን እየጠረቀ በድርቅ ሲሰቃይ ኖሯል በሚል ትችቱን ያቀርብና በወንዝ ውሃ ሽሚያ ጦር መማዘዝ የተለመደ ስለመኾኑ ከመካከለኛው ምሥራቅና ከእስያ ምሳሌዎች ይጠቃቅሳል። ዐባይን ከማወደስ ባለፈ ስለ ወደፊት ዕጣውና ስለ ዕድላችን አቁመን አላናገርነውም፣ በውሃ መጣላት በዓለም የተለመደና በሕግ የሚታቀብበት መንገድ ስላለው ዋናው ትግላችን ዐባይን አቁሞ (ገድቦ) ማነጋገሩ (ማልማቱ) ላይ ነው በማለት ስልቱን ይጠቁማል።

"ዐባይ የጥቁር ዘር ብሥራት፣
የኢትዮጵያ ደም የኩሽ እናት"፣ አልኩህ እንጂ በፊደሌ
መች አቁሜ አነጋገርኩህ ስለ ዕድልህ ስለዕድሌ
ካንተው ጋር እንጂ ሙግቴ፣ መቼ ከጎረቤት ጥሌ
እንጂ አለምማ መች ያርፋል፣ ውሃ ካለማ ጦር አለ
አይምሰል እንጂ ውል አለው፣ በቅጡ አይቶ ላስተዋለ። (ገጽ 139)

በአንድ በኩል ጦርነት ስለ ታከተን ዐባይን ከጎረቤት ጋራ ጦር እንዳያማዝዝ ይማፀነዋል። በሌላ በኩል ደግሞ "የሰው ጉልበት ካልባረከህ"/ "አእምሯችን ካልዋኘብህ"/ …"መልክ መቼም ውበት አይሆንህ" በማለት ዐባይን በስምምነት/በብልሃት፣ በላባችን፣ በዕውቀታችን አልምተን ከቃላት ሽንገላ ባለፈ እናስውብሃለን ሲል ተራኪው ቃል ይገባለታል። ጥሪው ጦርነት ውስጥ ሳንገባ ዐባይን እናልማ ነው።

## 7. *ፈለገ ግዮን — ፈለገ ትንሣኤ*

የታላቁ የሚሌንየም (በኋላ የሕዳሴ) ግድብ የማእዘን ድንጋይ መጋቢት 24 ቀን 2003 ዓ/ም በጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊ ከተቀመጠ በኋላ የተደረሱት አብዛኛዎቹ የአማርኛ ግጥሞች (የአቀራረብ ስልታቸውና በተያያዥ የሚያነሷቸው ሐሳቦች በመጠኑ ቢለያዩም) ዋናው የሚያስተላልፉት ጭብጥ የዐባይ ግድብ ግንባታ የኢትዮጵያ ዳግማዊ ትንሣኤ ብሥራት መኾኑን ነው። ለ7ኛው ንኡስ ክፍል "ፈለገ ግዮን — ፈለገ ትንሣኤ" የሚል ርእስ የተሰጠው ዐባይ በአሪት ዘፍጥረት ከገነት መንጭቶ ገነትንም ሲያጠጣ እንደ ነበረ ሲሰበክ ከነበረው ትርክት አንጻር የዐባይ ግድብም ለሕዝቡ የሚያመጣው ትሩፋት ኢትዮጵያን ምድራዊ ገነት የሚያደርግ ያህል በበርካቶቹ ግጥሞች ውስጥ ተጋንኖ ስለሚቀርብ ይህንን የብሩሕ ተስፋ ዕይታቸውን ለመጠቆም ነው።

ድኅረ-2003 ዓ/ም ግጥሞች ከፊሉ በገጣሚዎቹ የግል ተነሳሽነት የተዘጋጁ ሲኾኑ ሌሎቹ ደግሞ በምን ኹኔታ እንደ ተገጠሙ የተሰባሰቡበት መድበል መግቢያ የሚከተለውን መረጃ ይሰጠናል፦ "...ከጥር 21-26 ድረስ በአዲስ አበባ የታላቁ የኢትዮጵያ ሕዳሴ ግድብ ማስተባበሪያ ጽ/ቤት አማካይነት የኪነ ጥበብ ባለሙያዎች ወደ ስፍራው ተጉዘዋል። በኢትዮጵያ ደራስያን ማኅበር በኩል [የ]ተጓዙት አስር ገጣሚያን ... በቦታው ተገኝተው የተሰማቸውን ስሜት በብዕራቸው ገልጸውታል። " በነዚህ የኢትዮጵያ ደራስያን ማኅበር (ኢደማ) አባላት የተደረሱት ግጥሞች 22 ሲኾኑ በግድቡ ግንባታ ማስተባበሪያ ጽ/ቤት ድጋፍ በአንድ ጥራዝ "አዲስ መዝሙር እና ሌሎች የግጥም ስብስቦች" በሚል ርእስ በ2007 ዓ/ም ታትመው ለንባብ በቅተዋል። በዚህ መድበል ግጥማቸው ከተካተተላቸው የኢደማ አባላት አንዳንዶቹ እስከ ስምንት (ለምሳሌ አንዱዓለም አባተ - ሦስቱን በ2005፣ አንዱን በ2006 ዓ/ም የደረሳቸው)፣ አንዳንዶቹ አራት (ለምሳሌ ታደለ ገድሌ)፣ አንዳንዶቹ ደግሞ ሦስት (ስንቅነሽ አጣለ እና ገብረ ክርስቶስ ኃይለ ሥላሴ)፣ የተቀሩት ሦስቱ ደራስያን አንዳንድ ግጥም አበርክተዋል። ከእነዚህ ሰባት ደራስያን ውስጥ ስለ ዐባይ ከግድቡ ግንባታ መጀመር በፊት ከታደለ ገድሌ በስተቀር አንዳቸውም የዐባይ ጉዳይ አሳስቧቸው ያበረከቱት ድርሰት ይኼንን ጸሐፊ አላጋጠመውም። ስለዚህ ግድቡን ማየታቸው አነሳስቷቸውም ይኹን ለጉብኝቱ ድጋፍ ያደረገው የአዲስ አበባው ማስተባበሪያ ጽ/ቤት ስለ ግድቡ በጎ ገጽታ መገንቢያ ድርሰቶች ስላስፈለጉት፤ ዞሮ ዞሮ ግጥሞቹ ተግባራዊ ግብ ነው ያነገቡት። በመድበሉ ውስጥ የተካተቱትም ኾነ ያልተካተቱት አብዛኛዎቹ የድኅረ-2003 ዓ/ም የልማት ጥሪ ግጥሞች የኪናቸው ዋና መገለጫ ቤት መምታታቸው ስለኾነ ዞሮ ዞሮ ፋይዳቸው ለብሩህ ሕይወት ግድቡን ተባብረን እንገንባ ከሚል ቅስቀሳ አያልፍም። የግድቡ ግንባታ ሲጠናቀቅም እነዚህም ኾኑ ከሕዳሴ ግድብ በፊት ዐባይ እንዲገደብ የቀሰቀሱት ግጥሞች ዘመን ተሻጋሪ ስላልኾኑ ዕጣ ፈንታቸው ለታሪክ ቅርጫት መዳረግ ይሆናል። ስለዚህ ይዘታቸው በአጭሩ ተዳስሷል።

### *ሀ/ በራሳቸው ተነሳሽነት ስለ ዐባይ ግጥም የጻፉ*

በድኅረ-ሕዳሴ ግድብ ጅማሮ ለንባብ ከበቁት ቀዳሚ ግጥሞች ውስጥ አንዱ የአበባየሁ ለገሠ "የአባይ ከተራ" (2004 ዓ/ም) ነው። አበባየሁ የግድቡ ግንባታ ከመጀመሩ ቀደም ብሎ በታኅሣሥ 2001 ዓ/ም "አባይ - ነዳጅ" የሚል በ2004 ዓ/ም የታተመ ግጥም የጻፈ ሲኾን በዚህ ግጥሙ ዐባይ ያለብዙ ልፋት የተገኘ የነዳጅ ድፍድፍ ቢኾን ኖሮ ታሪካችን ሌላ ይኾን ነበር ሲል ትዝብቱን ይገልጻል፦

አባይ ነዳጅ ሆኖ
ቢያገኘው ሕዝብ ሁላ
ታሪክ ተቀይሮ
ይጻፍ ነበር ሌላ። (ገጽ 24)

በሐምሌ 2003 ዓ/ም በተደረሰው "የአባይ ከተራ" ውስጥ ደግሞ ዐባይ እንኳን ተገደበ ይለንና ከዚያም ይህ የግድብ ሥራ ግን ገባሮቹም ያለጥቅም ባክነው ከሚቀሩ ለትውልድ ትሩፋት እንዲኾኑ ይቀልበሱ ሲል ጥሪ ያቀርባል። ነገር ግን የአበባየሁን ግጥም ለየት የሚያደርገው ይህ በሌሎች ገጣሚዎችም ቀደም ብሎ የተነሣው ሐሳብ ሳይኾን የግብፆችና የሐበሾች አንድነት ነው፡-

ሀበሻ'ኮ ለምስር
ልዩነት የለውም
ያው አንድ 'ሥር። (ገጽ 25)

ግጥሙ ኢትዮጵያና ግብፅ አንድ ናቸው ሲል ይህ አንድነታቸው በዘር ግንድ ይኹን ወይም በዐባይ ወይም በሌላ ኹኔታ ግልጽ አያደርግም። ሌላው የአበባየሁን ግጥም ለየት የሚያደርገው ሐሳብ ሕዝቡ በድርቅ የተጎዳበትን ምክንያት ከዲሞክራሲ እጦት ጋራ ማያያዙ ነው፡-

ቀድሞም ቢሆን የኢትየጵያ ልጅ
ውሃ በሞላበት ጥሙን ያልቆረጠው
በዲሞክራሲ ዕጦት
ዕቅድ ወጥቶበት ነው (ገጽ 25)

አበባየሁ በዚሁ ዓመት ስለ ዐባይ የደረሰው ሌላው ግጥም "ሐዋርያው አባይ" የሚል ሲኾን ዐባይ በየአገሩ የሚዞረው እንደ ሐዋርያት በእስትንፋሱ ሕብስተ መናን ሊያዳርስ ነው በማለት ስለ ዐባይ በረከት በዘይቤ ለመግለጽ የሚሞክር ነው።

የመንግስቱ ዘገዬ "አለው መላ መላ!" (2005 ዓ/ም) ስለ ግድቡ ግንባታ በቀጥታ ባይጠቅስም ከዐውዱ አንጻር ማንኛውም እንቅፋት በሕይወት ጉዟችን ቢያጋጥመን ወደ ኋላ ማፈግፈግ የለብንም የሚል መልእክት ያዘለ ነው። ይህን በምሳሌ ሲያስረዳም ዐባይ የትኛውም እንቅፋት ቢጋረድበት መጓዙን እንደማያቆም ኹሉ፣ ዐባይ ራሱም መንገዳኛውን አላሳልፍ ብሎ ያሻውን ያህል ቢያስፈራራም የሀገሩ ሰዎች መላ ፈልገው መሻገራቸው እንደማይቀረው ኹሉ በዐባይ ምክንያት የሚመጣ ችግርንም እንቋቋመዋለን በማለት ተስፋ አለመቁረጥን ያበረታታል፡-

አባይና ህይወት፣
ህይወት እና ጅረት፣
መጣሁብህ ብለው፣ ከተዥጎረጎሩ፣
ልጥልህ ነው ብለው ከተገዳደሩ፣
ያ'በሻ ልጅ ፋኖ፣ ያ'በሻ አባ ነብሮ፣
የህይወት ጅረቱ፣

ሲገተር ከፊቱ፣
የኑሮን ጎዳና፣ ሀዲዱን ሰባብሮ፣
ዘራፍ ነው አመሉ፣
ወገቡን ቀስሮ፣ ወኔ ስንቁን ቋጥሮ። (ገጽ 137)

የታደሰ ሥዩም "የዓባይ ልጆች" (2006 ዓ/ም) የታላቁ የኢትዮጵያ ሕዳሴ ግድብ በመገንባቱ ምክንያት የአገሪቱ ብልጽግና እውን መኾኑን ያበሥረናል፦

ድህነት ገደል ገባ
አዘቀጠ እንዳሸዋ
ችግር ባባይ ግድብ ሲሰዋ (ገጽ 68)

ይህ ግድብ ለአፍሪካ ሕዝብም ድል መኾኑን፣ ከአድዋ በኋላ ሌላው ድል መኾኑን፣ ግድቡ የኢትዮጵያ የእድገት መላ ስለኾነ ከዚህ በኋላ ድኻ በሚል መመዝገብ እንደሌለብንም ያሳስባል፦

አባይ ቀለም ሁንና አጥፋልን
ድሃ ነበር ስማችን
የዓለም መዝገበ ቃላቶች ተሰብሰቡ
እውን ሊሆን ተጽፏል ግድቡ
ኢትዮጵያ ሀብታም ብላችሁ ቶርቡ (ገጽ 69)

የግጥሙ ዓላማ ይህን የተስፋ ዳቦ መግቦ ለግድቡ ሕዝባዊ ድጋፍ ማሰባሰብ ስለኾነ ለዚሁ ጥሪውን ያቀርባል። "A Gate Way to Prosperity" በሚለው በዚሁ መድበል በቀረበው የእንሊዝኛ ግጥሙም እንዲሁ ግድቡ ድኽነትን ከምድረ ኢትዮጵያ ጠራርጎ እንደሚያጠፋ ይገልጽልናል።

ይከበር በሪሁን "ዓባይ" (2006 ዓ/ም) በሚለው ግጥሙ በዐባይ ድርጊት ፍትሕ ተዛብታለች በሚል ስሞታ ያቀርብና ዐባይ እናት አገሩን እየገመሰ በባዕድ አገር መንከራተቱን ትቶ በአገሩ መስክ ላይ እንዲለመልም ምኞቱን ይገልጻል፦

አ ዓባይ!
ጥለቅ ከእሙ ሰማይ፤
ለምልም ባገርህ ላይ፤
አብብ በመስክህ ላይ፤
አትውጣ አትውረድ በባዕድ ሀገር ላይ። (67-68)

ግጥሙ ከሕዳሴው ግድብ ግንባታ መጀመር በኋላ ቢደረስም የገጣሚው ምኞት ዐባይ ድንበር ተሻግሮ መሰደዱ እስከናካቴው እንዲገታ ነው።

የታደሰ ሥዩምን ያልተጨበጠ ተስፋ የሚጋራው የምንዋጋው ተመስገን "ትእምርተ ሚጠት" (2008 ዓ/ም) ለቴዎድሮስ "እዬዬ" ምላሽ መኾኑን በግርጌ ማስታወሻው ይነግረናል። የቴዎድሮስ "እዬዬ"

ዐባይን የማልማት ጥሪ ስለኾነ የምንዋጋው ግጥም በአንድ በኩል በሕዳሴው ግድብ ጥሪህ ይኸው ተመለሰልህ የሚል ይመስላል። በሌላ በኩል ደግሞ የዐባይን መገደብ ዜና ሲሰሙ ስደቱን የሚሹ የሐዘን እንባ አነቡ ስለሚል እነዚህ ባለቅሬታዎች ሱዳንና ግብፅ ይኹኑ ወይም ሌሎች ግልጽ አይደለም። ነገር ግን ዐባይ እኛ ነን፤ ስደተኞቹም እኛው ነን፤ ስለዚህ ከስደት እንገደብና እንኑር ካለን በኋላ በሕዳሴው ግድብ ምክንያት ስደተኞች ከያሉበት ስለመመለሳቸው ምኞቱን ያወጋናል፡-

ከዓባይ ግድብ ጀርባ ወደር የለሽ ደስታ ሐሴት ይንጠኛል፤
ኢትዮጵያውያን ከተበተኑበት ስደት ከኖሩበት መጥተው ያወጉኛል
ተስፋ አለኝ። (ገጽ 34)

የደስደስ ተስፋ "የዓባይ ዘመን" (2007 ዓ/ም) እንደ ታደሰ ሥዩም እና ምንዋጋው ተመስገን ግጥሞች የትንሣኤ ብሥራት በግልጽ ባያውጅልንም ወድቆ የመነሳትን ምኞት ያንጸባርቃል። የኢትዮጵያ ታላቅነት መገለጫ የነበሩት እንደ የአድዋ ድል፣ የአክሱም ሥልጣኔና የላሊበላ ውቅር ቤተ ክርስቲያናት የመሳሰሉት ዝና በረሃብ ታሪክ በመሸፈኑ የኢትዮጵያ አካኼድ ከላይ ወደ ታች የመውረድ ስለኾነባት የዐባይ ግድብ የኢትዮጵያን ሕዳሴ እንዲያመጣ ጸሎቷን ታቀርባለች፡-

እባክህ ፈጣሪ ጎደሎ ጅምራችን ሙላና
አኑረን እንደገና
"የኋለኞች ፊት" መሆንን ትንቢት
በእኛ ዘመን ፈጽምና። (ገጽ 72)

ከብዙዎቹ የዐባይ ግድብ ተስፈኛ ግጥሞች የሷ የሚለየው ተሐድሶው እውን እንደ ኾነ ከመስበክ ይቆጠባል። እንዲውያም የግድቡ መጠናቀቅና የኢትዮጵያን ትንሣኤ የማምጣቱ ነገር የአገሪቱን ዐቅም የሚፈታተኑ ብዙ ተግዳሮቶች ስለሚደቀኑበት የፈጣሪ ረድኤት ካልታከለበት በቀላሉ ላይሳካ እንደሚችል በመጠቆም ስለ ግድቡ የሚስተጋባውን የወቅቱ ሆይሆይታ በስክነት እንድናይ ይገፋፋል።

የግርማ ተስፋው "ዐባይ ውኃ አይደለም" (2005 ዓ/ም) ከ2003 ዓ/ም በኋላ ለንባብ የበቁ ሕዳሴ-ነክ ግጥሞችን የኢትዮጵያ ትንሣኤ ዝማሬ በሰቆቃ እንጉርጉሮ የሚተካ ፖለቲካዊ ግጥም ነው። በግጥሙ ውስጥ ተራኪው ዐባይ መጠጊያ ያጣ የቀትር እባብ፣ የባዘነ ስደተኛ፣ ገነትን የሚያጠጣ፣ ሕይወትን የሚታደግ፣ እርዛትን የሚገረስስ፣ በፍቅር ተማግሮ ተስፋን ሰንቆ የሚጓዝ ወንዝ ይመስለው እንደ ነበር ከገለጸልን በኋላ ዐባይ ውሃ ሳይኾን ባጣች በገረጣች፣ ፍዳ ባልተለያት፣ ዋይታዋ በማያባራ እናት (ኢትዮጵያ) እንባ ተሞልቶ የሚፈስ ጅረት መኾኑን ይነገረናል፡-

ዐባይ ውኃ አይደለም
እንባ ነው፤
ጅረት ነው።
ከለተቱ ጡቶች ከደረቁ ዐይኖች
ከታጠፈ ወገብ ከቦዙ ተስፋዎች። (ገጽ 53-54)

ዐባይ ውሎዋ ቁዘማ፣ ሐዘኗ ተራራ የኾነባት እናት አገር የሰቆቃዋ ትእምርት ኾኖ ቀርቧል፡-

ዓለም ቅልስልሱ
ዐባይን ሲጎነጭ ውኃ ይመስለዋል፤
በጳጉሜ ያካፋ የሩፋኤል ጠበል።

ዐባይ ግን እንባ ነው
ተስፋ ከሳሳበት ከሐዘን ተራራ ከቁዘማ ገዳም
ከትካዜ ጋራ የሚሄድ፣ የሚነጉድ ለዓለም ዘላለም። (ገጽ 54)

ስለዚህ ምንም እንኳን ግጥሙ ለንባብ የበቃው የእድገት፣ የተድላ፣ የብሩህ ሕይወት መጻዒ ዘመን ብሥራትና በር ከፋች መኾኑ የተተነበየለት ታላቁ የሕዳሴ ግድብ የማእዘን ድንጋይ ከተቀመጠ ከኹለት ዓመት በኋላ ቢኾንም ለዚህ ግድብ እስከ መኖሩም ዕውቅና አይሰጥም። ብዙ የተዘመረለትን የተስፋ ወጋገን የጽልማሞት ማቅ በማልበስ፣ የሕዝቡ ብሶትም ማብቂያ የሌለው መኾኑን በማወጅ ይደመድማል። ይህ ምስሉ ከሌሎች የብሥራተ ትንሣኤ ግጥሞች በተቃራኒው የሥርዓቱን አራማጆች ለመከራው በስላሽ ተጠያቂ ያደርጋል — መላውን ሕዝብ ካላስከፋት እንባው ጅረት አይኾንምና።

ለ/ የኢደማ አዲስ መዝሙር

በኢደማ የግጥም መድበል ተሰባስበው የቀረቡት በርካታ ግጥሞች ዐቢይ ሚናቸው የግድቡን ማኅበረ-ኢኮኖሚያዊ ፋይዳ በማጉላት ለግንባታው ስኬት የሕዝቡን በጎ ፈቃድና ድጋፍ ማበረታታት ነው። ምናልባት ይኸን ተልእኮ የተሻለ ወክሎ ይገልጸዋል በሚል ታስቦ ይኾናል የአንዱዓለም አባተ “አዲስ መዝሙር” (2007 ዓ/ም) የመድበሉ ርእስ ኾኖ የተመረጠው። የወቅቱ አዲስ መዝሙር የሕዳሴው ስኬት እና የአገር ትንሣኤ የምሥራች የሚዜምበት መኾኑንና ይኸን ተስፋ የሚጋራ ለወገን ተቆርቋሪነቱን በተግባር የሚያሳይበት ጊዜ ነው የሚል መልእክት አለው የአንዱዓለም ግጥም። ይህንንም በባሕላዊው ዘፈን (ይኸን ያለ/የፈለገ ... ይኸን ያድርግ) ስልት ያቀርበዋል፡-

ከበረሃው ጉያ...ከነዲዱ መኻል ...ነገን ያፀደለ፣
በጸናን ትግል ውስጥ...ካባይ የተቀዳ...አዲስ መዝሙር አለ።
ቤቱን ቤቱን ያለ...አገሬና ዐፈሬን...ምድሬን ምድሬን ያለ፣
ለጦቢያ ምሥራች...ለሕዳሴው ስኬት...ወገን አገር ያለ፣
ለጦቢያ ምሥራች...ለሕዳሴው ስኬት... ወገን አገር ያለ (ገጽ 34)

የአስፋው ዳምጤ “በዐይኔ አየሁህ ዐባይ” (2007 ዓ/ም) በጉብኝቱ የሚያየው ድፍርስ የነበረው ወንዝ ቀን ከሌት ብርሃን ለብሶ፣ እሱም በሰመመን ውስጥ ኾኖ ስለ ወገኖቹ ሥርየት የሚያልመውን ነው፡-

*ዐባይ አንተ የብዙኃን ሲሳይ!*
*ስላንተ ከጨቅላነቴ ጀምሮ ስሰማ ኖሬ ኖሬ*
*"ሌቱ ብርሃን፣ ቀኑም ብርሃን" ሆኖልህ ዛሬ*

...

*ዐይኔ ሳይከደን ሰመመን ውስጥ እየዋኘሁ*
*ለጉስቅል ወገኔ፣ ረ-ኸ-ም ሕልም አየሁ!* (ገጽ 3)

የስንቅነሽ ዐጣለ *"ዘመንና ትውልድ"* (**2007 ዓ/ም**) ደግሞ የዐባይ መገደብ የዐፈር መሸርሸርን እንደሚያቀምና ልማቱም ከራሱ አገር አልፎ ጎረቤቶችን እንደሚያጠግብ ያበሥራል፦

*ዐፈር መሸርሸሩን ማራቆቱን ትቶ*
*በውሃነቱ ላይ ኃይልን ተቀዳጅቶ*
*የእኛን ጓዳ አርክቶ ሊያጠግብ ጎረቤት*
*ዐባይም ዘመነ ታደመ ለልማት።* (ገጽ 4)

የስንቅነሽ ግጥምና መሰሎቹ ውሃ በግድብ በመጠራቀሙ ብቻ ዐፈር መሸርሸሩ የሚያቆም ያስመስላሉ። ዐፈር በወንዝ ብቻ ሳይኾን በዝናብ ውሃም ይሸረሸራል። የዐባይንና የገባሮቹን ተፋሰስ የአካባቢ ጥበቃ ለማጠናከር በብዙ ሙአዕለ ንዋይ የተደገፈ መጠነ ሰፊ ርብርብ እስካልተደረገና በየጉብታውና ተዳፋቱ እየተስፋፋ የመጣው ባሕላዊ እርሻ እስካልተለወጠ፣ የደን ምንጣሮውም ተገትቶ ዳገት ቁልቁለቱ በደን እስካልለበሰ ድረስ እንደ ቆቃ ግድብ የሕዳሴውም በደለል ይሞላ ይኾናል እንጂ ዐፈር መሸርሸሩ እንደማያቆም ገጣሚዎቹ ያጤኑ አይመስሉም። ይሄ ከእውነታ ጋራ የተፋታ ተስፋ የመመገብ አባዜ በስንቅነሽ "ለካ ዛሬም ጀግኖች አሉሽ" (2007 ዓ/ም) ግጥምም ይደገማል። ግጥሙ በግድቡ ግንባታ የሚሳተፉትን ታሪክ ሠሪ ትውልድ በማለት ያወድሳቸዋል። በእርግጥም በግዙፍነቱ በአፍሪካ ወደር የለውም የተባለውን ግድብ፣ በዚያ በረሓማ ቆላ ያለምቾት ቀን ከሌሊት ግድቡን የሚገነቡት ሠራተኞች ታሪክ እየሠሩ ስለኾነ ለመሥዋዕትነታቸው ዕውቅና ይገባቸዋል። ኾኖም ግጥሟ ከዚህ ያልፍና የግድቡ ግንባታ ገና በጅማሮ ላይ እያለ አገሪቱ በብልጽግና ተንበሽብሻ ዝናዋ በዓለም እንደ ናኘ ያበሥረናል፦

ተነሺ ኢትዮጵያ እልል በይ የዜማ ጊዜ ነውና፣
ሀገሬ ተነሺ አብሪ የፍሬ ጊዜ ደርሷልና፣
ከአጽናፍ እስከ አጽናፍ ያስተጋባ በዓለም ያንቺ ዝና፣
በልማት ዐውድ ድህነትን ገድለሽ ቀብረሻልና። (ገጽ 6) (አጽንዖት የኔ)

"ሕያው ምስክርነት በጎረቤት" (2007 ዓ/ም) የሚለው ግጥሟ የሱዳን ሕዝብ በግድቡ ግንባታ እሱም የብልጽግና ተቋዳሽ መኾኑን በማወቁ በደስታ አብዝቶ መፈንጠዙን ያወሳል። የአልበሽር መንግሥት ሲወድቅ ግን ሱዳንም ብትኾን ከግብፅ ጎን በመሰለፍ የግድቡ ሌላዋ ቀንደኛ ተቃዋሚ በመኾኗ መሪዎቿ "ዘላቂ ጥቅም እንጂ ዘላቂ ወዳጅ የለም" ባዮች ኾነዋል። የፈንጠዝያው ግነት

ሚዛኑን ቢስትም ግጥሙ ዐባይ የጋራ ሀብት መኾኑን ዕውቅና በመስጠቱ ከሌሎች ግጥሞች ለየት ይላል።

የገብረ ክርስቶስ ኃይለ ሥላሴ "ዐባይ የዘር ግንድ" (2007 ዓ/ም) የካምና የኩሽ እትብትና ሥልጣኔ የተቀበረበት፣ ጉባ ላይ የጥንት ማንነታችንንና ክብራችንን ልንመልስ ዳግም ከዐባይ ጋራ ተገናኘን ይልና ዐባይ በመገደቡ ታሪክ እንደሚታደስና ዓለምም እንደሚደመም ያወሳል፡-

በነዚህ ጀግኖችህ ከበውህ በቆሙ፣
ባንተ የብርሃን ጦር ችግር ሲፋለሙ፣
የከንቱ ሩጫህን ስደትህን ሲያስቆሙ፣
ታሪክ ይታደሳል ያውቀናል ዓለሙ። (ገጽ 10)

"የበኩር ልጃችን" (2007 ዓ/ም) የተባለው ግጥሙ (በግድቡ ምክንያት) ዐባይን ጠፍቶ እንደተመለሰው የበኩር ልጅ ሲሥለውና ሕዝቡም ዐባይን በፍቅር ታቅፎ ልማቱን እንዳፋፋመው ሲያበሥርልን፣ "ማንነቴ ክብሬ" (2007 ዓ/ም) በሚለው ግጥሙ ዐባይ የረኀብ፣ የእርዛት፣ የጦርነት ምንጭ የነበረ ቢኾንም ልክ በስንቅነሽ ግጥሞች ውስጥ ምኞትና እውነታ እንደሚፋቱት ኹሉ እዚህም ዛሬ በግድቡ ምክንያት የድቀት ታሪክ እንደ ተለወጠ ያወሳል፡-

የሀገሬ ልጆች
ተባብረው ባንድነት፣
ልዕልናና ክብሬን
የጥንት ኃያልነት፣
አየሁ ሲመልሱት
ወደነበረበት፣
    ችግሬም ሲወገድ ሲሆን ተረት - ተረት። (ገጽ 11)

የአንዱዓለም አባተ "ትውልድን ጭምር ነው" (2007 ዓ/ም) እንደ ላይኞቹ ችግር ተረት ኾኗል ባይልም ግድቡ ድኽነትን መንግሎ እንደሚያጠፋውና አዲስ ትውልድ እንደሚፈጥር ይተነብያል፡-

በነዲድ በረሃ…ከሥሩ ተነቅሎ የሚመነገለው፣
ቋጥኝ ብቻ አይደለም… ድህነት አብሮት ነው።
በጉባ በረሃ… አንዴ ለዘለዓለም የምገድበው፣
ውሃን ብቻ አይደለም…ትውልድን ጭምር ነው። (ገጽ 33)

የፈለቀ ካሣ "ፍም ነው መክሊታችን" (2007 ዓ/ም) ባድዋ፣ በማይጨው(?!) የተላለፈውን ረመጥ የሕዳሴው ዘመን ትውልድም ለሚቀጥለው ለማስተላለፍ መሥዋዕት ይኹን በማለት ቀጥተኛ የድጋፍ ጥሪ ያደርጋል። የአንዱዓለም አባተም "የአባትዬው ጦማር!" ከአባት ለልጅ የትውልድ አደራን ያስተጋባል። የአባትዬው ጦማር ያለፈውን የችጋር፣ የስደትና የቀቢጸ ተስፋ ጊዜ እንዳይረሳ፣ ሕብረቱን እንዳያላላ፣ እስከ ሞት መሥዋዕትነት ቢጠየቅ ለዐባይ እንዲሰጥና በምንም ምክንያት

ከግንባታው እንዳይዘናጋ ያሳስባል። አደራውን በመቀበልም የመንደሩ ሕዝብ ሁሉ ቦንድ ለመግዛት በናፍቆት እየጠበቀ ነው በሚል የዋህ መደለያ ሌላውም ሰልፉን እንዲቀላቀል ይቀሰቅሳል። “ገፋ ገፋ አድርጉ” (2007 ዓ/ም) በሚለው ሌላው ግጥሙም እንዲሁ የድጋፍ ጥሪውን ያስተላልፋል፡-

በጠየቀን ዋጋ...በደምና በላብ፣
ይገደባል ዐባይ ...በድፍን ጦቢያ ሕዝብ። (ገጽ 32)

አንዱዓለም “አለ ክፉ መንፈስ” (2007 ዓ/ም) በሚለው ግጥሙ ከወዲያ ማዶ ኾነው በዐባይ ወንዝ ላይ የጀመሩት ግንባታ አይሳካላቸውም፣ ድኾች ናቸውና ዐቅም የላቸውም፣ ፈሪዎች ናቸውና ታሪክ አይጨርሱም፣ ዕውቀት የላቸውምና በራሳቸው የጀመሩትን ችለው አይጨርሱም በማለት የሚያሚርቱትን (እነ ግብፅን?) አሳፍሮ በተባበረ ክንድ ታሪኩን ለማደስ ትውልዱ ቆርጦ ተነስቷል የሚል ሙገሳ በመቸር በተዘዋዋሪ የተጀመረውን ለመጨረስ ሁሉም እንዲነሣ ይቀስቅሳል። “ከዚህ ታሪክ መኻል” የሚለው ግጥሙ ደግሞ ትውልዱ በጉባ በረሓ የታሪክ ገድል ሲሠራ በዚህ ውስጥ የኔ አሻራ የታለ በሚል ራሱን ጠይቆ፣ ያለው በገንዘቡ፣ የሌለው በዕውቀቱ ወይም በጉልበቱ አስተዋጽዖ እንዲያደርግ ይቀሰቅሳል። “እኛ እኮ ነን ታሪክ” (2007 ዓ/ም) የሚለው ግጥሙ ትኩረት በግድቡ ግንባታ ላይ በተሰማሩ ሠራተኞች ላይ ሲኾን ታሪክ ሠሪ ጀግኖች በማለት ያወድሳቸዋል። በተመሳሳይም “በወርቃማው ትውልድ!!” በሚለው ግጥሙ ኢትዮጵያ ለአፍሪካ አንድነት ፋና ወጊ እንደነበረችው ኹሉ አሁንም ትንሣኤዋ በዐባይ ግድብ ግንባታ በዘመኑ ትውልድ እውን ይኾናል በሚል ትውልዱን ያሞካሻል፤ ይቀሰቅሳልም፡-

አይሆንም ለሚሉ...ይኸው ሆኗል ታሪክ...ያውልህ ምስክር
የዘመኑ ትውልድ...
በወርቃማው ትውልድ...
ድህነት ድል ሊሆን...ዐባይ በቤቱ ሲያድር። (ገጽ 50)

“ለጦቢያ ምስራች” (2007 ዓ/ም) ግጥሙም እንደ ሌሎቹ ተስፋን ከማስተጋባት ባሻገር ዐባይ ተገድቦ አገሪቱን በመስኖ ከዳር እስከ ዳር እንዲያጠጣ የማድረግ ሕልሙንም ይገልጻል፡-

ቢሻን እንደወደድን!!
ለመስኖ ቀይሰን... ከአንዱ ጎጥ ወዳንዱ... እየተቀባበልን
ዐባይ ሙት እመነን...
አንተን ቱሪስት አርገን...
ስንት የማታውቀውን ...ጋራና ጉድባውን እናዞርሃለን። (ገጽ 43)

ነገር ግን ከሌሎች ሕልመኛ ግጥሞች ለየት ባለ ኹኔታም ዐባይን በማልማት ድኽነትን የማጥፋት ግብ እንዲህ በቀላሉ የሚሳካ እንዳልኾነና ብዙ ትግልና ኅብረት የሚጠይቅ መኾኑንም ያስገነዝባል፡-

እናም ትግል አለ... ጽናት የሚጠይቅ፣
መታከት የማይወድ...ኅብረት የሚጠይቅ።
ገና ትግል አለ
ድህነትን ያህል...ተራራ ለማፍረስ፣
ወኔን የሚፈትን...ልብን የሚያፈስስ። ገና ሩቅ ጉዞ አለ...
ለጦቢያ ምሥራች...ማልዶ ለመናገር፣
ዐባይን ላንደኛው...ጸንቶ ለማስገበር። (ገጽ 45)

በዚህ ከወትሮው በሰከነ ኹኔታ የሚተላለፈው ያለኅብረትና መሥዋዕት ስኬት አለመኖሩን የሚያስገነዝብ መልእክት በባንቿአየሁ ዓለሙም "ዐባይ ነፍሳችን ነው!!!" (2007 ዓ/ም) ይደጋማል፡-

ኀበዝ እንነሳ፣ ለጋራ ጥቅማችን
በጋራ ኃይላችን
እህት ወንድሞቼ ለሥራ እናብር
ይቀየር ስማችን! (ገጽ 17)

በብዙዎቹ በድኅረ-ሕዳሴ ግድብ ጅማሮ ግጥሞች ውስጥ የአንድነትና የሕዝባዊ ድጋፍ ጥሪ ተደጋግሞ የሚስተጋባበት ምክንያት ለግድቡ ግንባታ በግብፅ ተቃውሞ ምክንያት ከውጭ አገሮችና ዓለም ዐቀፍ የገንዘብ ተቋሞች ቀጥተኛ ድጋፍም ኾነ የገንዘብ ብድር ማግኘት ስላልተቻለ[12] እና ግድቡ በኢትዮጵያ መንግሥትና በኅብረተሰቡ የገንዘብ ድጋፍ የሚሠራ በመኾኑ ነው። ሌላው ፋይዳው በቋንቋ ማንነት በተዋቀረ ፌዴራሊዝምና በዋልታ-ረገጥ አቀንቃኞቹ በሚራገበው የልዩነት ፖለቲካ ለክፍፍል የተጋለጠውን ሕዝብ አንድ የጋራ አገራዊ ርእይ በመስጠት አንድነቱን ማጠናከር ነው። ስለኾነም ለግድቡ ድጋፍ ሕዝቡን የሚቀሰቅስ ግጥም ኹሉ የሚያጠነጥነው በኢትዮጵያዊ ማንነት ላይ ነው።

ከዚህ አንጻር የታደለ ገድሌም "እንኩዋንም አየሁህ!" (2007 ዓ/ም) የዐባይ ኃያልነት በገባሮቹ ኅብረት ምክንያት እንደኾነው ኹሉ ሕዝቡም ኅብረቱን እንዲያጠናክር ጥሪ ያስተላልፋል፡-

የአንተ ግዙፍነት የጥልቀትህ ምሥጢር፣
የአብሮነት ሕላዌ የወንዞች ትብብር።
እያንዳንዱ ዜጋም እንዲህ ነው ሐሳቡ፣
የኅብረት ማማ ነው መንፈሱና ልቡ፣
ለቃለ ሕዳሴም አንድ ነው ማተቡ። (ገጽ 20)

[12] በዚህ የግብፅ ሤራ ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊ በወቅቱ ቅሬታውን በገሀድ ገልጾ ነበር። (ኃይሉ 2001 ዓ/ም፣ ገጽ 167)

"ዓባይን ያላዬ" (2007 ዓ/ም) የሚለው የታደለ ገድሌ ግጥምም አትዮጵያ በሕዳሴ ግድብ ትታደሳለች፤ ታንጸባርቃለች፤ ትለማች፤ ለዜጎቿ መኩሪያ ትኾናለች፤ ግድቡን ኼዶ ማየትም ገነት መግባት ነው በማለት ቢያሞከሻሽም ለስኬቱ የጋራ ትጋትና ድጋፍን አስፈላጊነት ያሠምርበታል፡-

ሀገሩን ከረዳ ላቡን እየሰጠ፣
የታል መልካም ሥራ ከዚህ የበለጠ። (ገጽ 26)

"እርስዋስ ሥራ ላይ ናት!" (2007 ዓ/ም) በሚለው ግጥሙ አገሩ በሕዳሴ ግድቡ ከሚፈጠረው አዲሱ ሐይቅ ዓሣ አስግራ ልጆቿን ለመመገብ፣ ታላላቅ የቱሪስት መዳረሻ ከተማ ለመገንባት፣ በ"ብርሃን ፍጥነት" እየተንቀሳቀሰች እንደኾነና ለወሬ ጊዜ እንደሌላት ይሰብካል። ኾኖም ለዚህ ስኬትም የሰው ጥረት ብቻውን ስለማይበቃ የመለኮታዊ ድጋፍም እንዲታከልበት ተማፅኖውን ያቀርባል፡-

የሕዳሴው ግድብ ጸንቶ መሠረቱ፣
ለሚመጣው ትውልድ እንዲቆም ሐውልቱ፣
የድኽነት መዝገብ እንዲፋቅ መርገምቱ፣
እያንዳንዱ ዜጋ ያንሣው በጸሎቱ፣
እግዜር እንዲራዳ አዝኖ ለፍጥረቱ። (ገጽ 23)

"የትኛው ነህ እሳት!" (2007 ዓ/ም) የሚለው ግጥሙ በጉባ አካባቢ ያየውን የሰንበሌጥና የቁጥቋጦ ቃጠሎ በቁጭት በመጥቀስ ግድቡ ሲሠራ በሚፈጠረው ሐይቅ ምክንያት የአካባቢው ተፈጥሯዊ ሚዛን አንስራርቶ ዛፎችም ስለሚጠበቁ ውድመቱ እንደሚቆም ተስፋውን ያበሥራል፡-

አወይ ድንግል መሬት አወይ ተደንግሎ፣
ያለውበት መቅረት ነድዶና ተቃጥሎ፣
እመኚኝ ምድሪቱ ውብ ቀን ይወለዳል፣
ለአንቺ ቀምበጥ ጽጌ ብዙ ሰው ያረግዳል።
ነቢይ ሆኜ አይደለም ይህን መናገሬ፣
ስለነገረኝ ነው ጉባ ላይ ያየሁት ዓባይ ምስክሬ። (ገጽ 24)

**ማጠቃለያ**

ዐባይ ዕድሜ ጠገብነቱ፣ ርዝመቱ፣ የሥልጣኔ፣ የታሪክና የሕይወት መሠረትነቱ፣ ተፈጥሯዊ ውበቱና ኃያልነቱ ተደጋግሞ በተለይ በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ዘመን በተደረሱትና አልፎ አልፎም ከዚያ በኋላ በተደረሱ ጥቂት ግጥሞች ተዘክሮለታል፤ ተወድሷልም። ዐባይ በአድናቆት የተሣለው ከኹለት ማማተሪያ ዐውዶች አንጻር ነው፤ አንደኛው ከግብፅና ሱዳን አኳያ፤ ኹለተኛው ደግሞ ከኢትዮጵያ አንጻር። ከኹለቱ ጎረቤቶች (በተለይም ከግብፅ) አንጻር የሕይወት ዋልታ፣ የእምነት ምኅዋር፣ የሥልጣኔ እምብርትና የታሪክ ምንጭ ኾኖ የተሣለበት ነው። ከኢትዮጵያ አንጻር ደግሞ ውበቱ (በተለይ በዐባይ ፏፏቴ ተወክሎ)፣ የመነጨበት አካባቢ ወጉ (ትውፊቱ፣ ሙዚቃው፣ ጥበቡ)፣

ታላቅነቱ (ባለብዙ ገባሮች መኾኑ)፣ የበርካታ አሳሾች የትኩረት መስሕብ መኾኑ፣ የውሃው ፈዋሽነቱ (ምንጩ ጠበል መኾኑ)፣ በመጽሐፍ ቅዱስ የተሠጠው ሚና ለአድናቆት አብቅተውታል።

ዐባይን እንደ ስደተኛ ወይም እንደ ኮብላይ የሚያቀርቡ ግጥሞች ዐባይን የኢትዮጵያ ብቻ ሀብት አድርጎ የማየት አዝማሚያ ይንጸባረቅባቸዋል። ከዚህ ዕይታ ጀርባ ዐባይ ድንበሩን አልፎ በሰው አገር በረሓ መፍሰስ አልነበረበትም የሚል ቁጭትም ታዝሏል። በሰይፉ ግጥሞች እንደታየውም "ዐባይ ዐባዩ"፣ "ዐባይ ውኀዬ" የሚሉት አጠራሮችም ዐባይ የኛ ነው የሚል እሳቤን ነው የሚያራምዱት። ይህን እሳቤ ሌሎች በርካታ ግጥሞችም በተለያየ መልክ ይጋሩታል፤ ዐባይ የኢትዮጵያዊ ብሔረተኝነት መገለጫ ኾኗልና!

በጸጋዬና ሌሎች ግጥሞች በውዳሴ የተንበሸበሸው ዐባይ በጥቂት ግጥሞችና ልቦለዶች ደግሞ የሰው መቅሠፍት እና የግጭት መሾሪያ ኾኖ ተሥሏል። የአገሪቱ ኋላቀርነት ለፈጠረው ሥነ ልቦናዊም ኾነ ማኀበረ-ኢኮኖሚያዊ ችግር ዐባይ ሰበብ ኾኖ ቢቀርብም ወቀሳው ዞሮ ዞሮ የሚመለከተው ጉዳቱን መከላከል ወይም መቅረፍ የተሳነውን ራሱን ኀብረተሰቡንና በየዘመኑ የነበሩትን መሪዎቹን ነው።

ዐባይ ለሱዳንና ለግብፅ ማኀበረ-ኢኮኖሚያዊ ደኅንነት ከፍተኛ አስተዋጽዖ ያለው መኾኑ በተወሰኑ ግጥሞች ግንዛቤ ያገኘ ነው። በአንጻሩ ግን ይህን በመመርኮዝ የነዚህ ጎረቤት መንግሥታት በአገራቸው የሚፈሰውን ዐባይ አብዛኛውን ውሃ እና እርሻቸውን የሚያደልበውን ለም ዐፈር የምታበረክተው ኢትዮጵያ በወንዙ የመጠቀም ተፈጥሮአዊ መብቷን ዕውቅና ባለመስጠት ህልውናዋን እስካሁን ሲፈታተኑ መቆየታቸውንም የተወሰኑ የአማርኛ ግጥሞችና ልቦለዶች በምሬት ያወሳሉ። ይህ በደመኛ ባላንጣነት የተወሳላቸው ሚናቸው በተለይ ኢሕአዴግ የሥልጣን ኮርቻ ላይ ከወጣበት ጊዜ ጀምሮ በተደረሱ በዛ ያሉ ግጥሞችና ስለነዚህ ጎረቤቶቻችን በሚያወሱ ልቦለዶች ውስጥ አንዱ ዐቢይ ጭብጥ ኾኖ ቀርቧል። በነዚህ ድርሰቶች ውስጥ ዐባይ ለኢትዮጵያ ጦሰኛ ኾኖ ተሥሏል። ከሱዳን ይበልጥ ግብፅ በቀጥታም ኾነ በተዘዋዋሪ በተለይ ለኤርትራ መገንጠል ከፍተኛ ድጋፍ ከማድረጓ አንጻር ኢትዮጵያን ለማፈራረስና ለማዳከም የምታሤር የምንጊዜም ጠላት ኾና በአብዛኞቹ ልቦለዶች ውስጥ ተሥላለች። ስለኾነም ዐባይን እንደ የጋራ ሀብት በመቁጠር በድርድርና በትብብር የማልማትና በኹለቱ አገሮች መካከል ጤናማ የሕዝብ ለሕዝብ ግንኙነትን የማጎልበት ርእይ በሥነ ጽሑፉ ውስጥ ተገቢ ቦታ ተነፍጎታል። በሕዳሴው ግድብ ምክንያት ግብፅ በቀጣናው፣ በአህጉራችንና በዓለም ዐቀፍ ደረጃ የምታራምደው ፀረ ኢትዮጵያ እንቅስቃሴ ከቀጠለ በሕዝቡ ሥነ ልቦናና ሥነ ጽሑፍ ውስጥ ስለ ግብፅ ያለው አሉታዊ አመለካከት እንዳይሻሻል ትልቅ ጋሬጣ ይደቅናል።

በደርግ ዘመንና በኢሕአዴግ ዘመን በታተሙት አብዛኛዎቹ ቅድመ-ሕዳሴ ግድብ ግጥሞች ውስጥ ዐባይ የኢትዮጵያን ለም ዐፈር ጠራርጎ በመውሰድ የመነጨበትን አገር ሲያራቁትና የራሱን ሕዝብም ለድርቅ፣ ለረሃብና ለድኽነት ሲዳርግ በአንጻሩ የሱዳንንና የግብፅን በረሓ በማልማት የሰው አገር ሲታደግ ኖሯል በሚል በከሃዲነትና በበደለኛነት ይወቀሳል። ቀደም ሲል ዐባይን ሲክቡ የነበሩትን ትውፊቶች፣ ውዳሴያዊ ትርክቶችና ወሸነኔያዊ ምስል ኹሉ ይደረማምሷቸዋል። እንደ ከንቱ ሽንገላ በመቁጠርም እነዚህ ግጥሞች ይሳለቁባቸዋል፤ በርግማንና በውግዘትም ይተኳቸዋል። በነዚህ ግጥሞች ዐባይን በበረሓ ቀልጦ እንደ ቀረ የማሳየቱ ፋይዳም የአገሪቱ ሀብት ያለአግባብ ባክኖ

እንዳይቀር ከልካይ ጠፉ የሚል መልእክት ማስተላለፍ ነው። ስለዚህ በግጥሞቹ ውስጥ የሚስተጋቡት የእሮሮና የቁጭት ድምፆች ላይ ላዩን በዐባይ ላይ ያነጣጠሩ ቢመስሉም ዞሮ ዞሮ የትችቱ ዒላማ ዐባይን በማልማት የኅብረተሰቡን ሕይወት የማሻሻል ግምባር ቀደም ኃላፊነት ያለባቸው የአገሪቱ ዜጎችና መሪዎች ናቸው። ብሶቱ በነዚህ ላይ የቀረበ መኾኑን ደግሞ ዐባይ በሰውኛ ስልት በተሣለባቸው ግጥሞች ውስጥ በወንዙ ሲሳይ ላለመጠቀማቸው ተጠያቂው ራሳቸው ወቃሾቹ መኾናቸውን ከሚያቀርበው ሙግት መረዳት ይቻላል። በነዚህ የዐባይ ሙግት ግጥሞች ውስጥ በተዘዋዋሪና በተደጋጋሚ የሚቀርበው ጥሪ ዐባይን ደፍረን እናልማ፤ ዝምታ ከጥቅሙ ጉዳቱ ያመዝናል የሚል ነው። ስለዚህ ምንም እንኳን ሊከተል የሚችለውን መዘዝ ቢገነዘቡም፣ የሚሌንየም ግድብ ፕሮጀክት ከመጠንሰሱ በፊት እንኳን፣ ዐባይን የመገደብና የማልማት ጥያቄን ቅቡልነት በኅብረተሰቡ ዘንድ በመፍጠር ረገድ የኢትዮጵያ ደራስያን የማይናቅ አስተዋጽዖ ማድረጋቸውን ግጥሞቹ ራሳቸው ይመሰክራሉ። የዘውግ ፖለቲካው ኅብረተሰቡን በቋንቋና በአካባቢያዊ ማንነት ለያይቶ አንድነቱን ለማፈራረቅ በሚንቀሳቀስበት ዐውድ ውስጥ ሥነ ጽሑፉ በተቃራኒው ዐባይን የአንድነትና የኢትዮጵያዊነት ድርና ማግ፣ የአገራዊ ርእይ ማጠንጠኛ አድርጎ አቅርቦታል።

የሕዳሴ ግድብ ግንባታ መጀመር በኦፊሴል ከታወጀ በኋላ የተደረሱት አብዛኛዎቹ የቅስቀሳ ግጥሞች የሚመግቡት የተጋነነ ተስፋና የሚያበሥሩት ሀገራዊ ትንሣኤ ከእንዲህ ዓይነት የፕሮፓጋንዳ ሥራዎች እንደሚጠበቀው ኹሉ መሬት ላይ ካለው እውነታና ተግዳሮት ጋራ አይጣጣምም። የዐባይ ግድብን የኢትዮጵያን ትንሣኤ ብቸኛ ማስገኛና ከድኅነት እስከናካቴው መገላገያ በማስመሰል፤ ሕዝባዊ ድጋፍን ለማሰባሰብ ያልተረጋገጠ መጻኢ ብሩሕ ሕይወትን በማማለያነት የሚያቀርበው ሥነ ጽሑፋዊ ፕሮፓጋንዳ እስከ ግድቡ መጀመር ድረስ በየዘመናቱ የነበሩትን እና በግድቡ ጅማሬ ወቅት በየዘርፉ በመካኼድ ላይ ያሉትን የልማትና የዝመና እንቅስቃሴዎች በጎ አበርክቶቶች ዕውቅና የመንፈግና ከአንድ ፕሮጀክት ተአምራዊ ውጤት የመጠበቅ አንድምታ አለው።

ነገር ግን ግድቡ የሚሠራው በሕዝብ ድጋፍና በመንግሥት በጀት ከመኾኑና ፕሮጀክቱን በስኬት ለማጠናቀቅ ከሚጠይቀው የሕዝብ ርብርብ አንጻር፣ እንዲሁም የግድቡ ተቃዋሚ ወገኖች በአገሪቱ ላይ ከሚደቅኑት ውስብስብ ተግዳሮት አንጻር፣ የነዚህ ዓይነት ቀስቃሽ ግጥሞችም የአገር ፍቅር ስሜትን በማነቃቃትና የሕዝቡን ኅብረትና ተሳትፎ በማበረታታት ረገድ የተወሰነ በጎ አስተዋጽዖ ይኖራቸዋል።

## ማጣቀሻዎች

### ሀ/ ምርምራዊና ታሪክ-ነክ ጽሑፎች


Asnaketch Demissie. 2015. Analyzing Amharic lyrics discourses on Abay and their roles: Sociocultural perspectives. PhD Dissertation, Foreign Languages and Literature Dept., Addis Ababa University. Unpublished.

Assefa Alemu. June 2017. Images of the Nile as reflected in selected Amharic and Arabic poetry. PhD Dissertation, Foreign Languages and Literature Dept., Addis Ababa University. Unpublished.

Bairu Tafla. 2000. "The father of rivers: The Nile in Ethiopian literature", in The Nile: Histories, cultures, myths, edited by Haggai Erlich and Israel Gorshoni. Boulder/London: Lynne Rienner Publishers.

Bayleyegn Tassew. 1997. "Myth and reality: Minds of Ethiopian poets on the Blue Nile'', in Proceedings of the 5th Nile 2002 Conference, Addis Ababa. Unpublished.

Carles, Alexis. 2006. Power asymmetry and conflict over water resources in the Nile River Basin: The Egyptian hydro-hegemony. MA Thesis, King's College London.

ፍስሐ ደስታ (ሌ/ኮሎኔል)፤ 2008 ዓ/ም፤ አብዮቱና ትዝታዬ፤ አዲስ አበባ፤ ፀሐይ አሳታሚ ድርጅት።

Gilkes, P.S. 1994. "Revolution and military strategy: The Ethiopian army in the Ogaden and in Eritrea, 1974-84", in Proceedings of the Eleventh International Conference of Ethiopian Studies, Vol. II, edited by Bahru Zewde, Richard Pankhurst, and Taddese Beyene. Addis Ababa፡ IES.

Girma Gelaye. June 2016. Abay through written literature of Ethiopia: A focus on Ethiopic ecclesiastical sources. MA Thesis, Philology Dept., Addis Ababa University. Unpublished.

መርሻ አለኸኝ፤ 2021 እጎአ፤ ዐባይ በግእዝ ድርሳናት፤ አዲስ አበባ፤ አዲስ አባባ ዩኒቨርሲቲ ፕሬስ።

Neguss Yilma Woldesenbet. March 2018. Thematic analysis of selected Amharic song lyrics: A sociological approach. PhD Dissertation, Foreign Languages and Literature Dept, Addis Ababa University. Unpublished.

Phillipson, David W. 2012. Foundations of an African civlisation: Aksum and the Northern Horn, 1000 BC — AD 1300. Addis Ababa & New York: Addis Ababa University Press and James Currey.

Rubenson, Sven. 1976. The survivial of Ethiopian independence. London: Heinemann Educational Books.

ተክለ ጻድቅ መኩሪያ፤ 1950 ዓ/ም፤ ጥንታዊት ኢትዮጵያና ግብፅ፤ ቱትሞሲስና ራምሴስ፣ ፒያንኪና ሻባካ፤ አዲስ አበባ።

Taddese Tamrat. 1972. Church and State in Ethiopia, 1270-1527. London: Oxford University Press.

Teferi Mekonnen. 2004. The Blue Nile issue: A history of hydropolitics, 1884-1974. MA Thesis, AAU, Addis Ababa.

Tesfaye Tafesse. 2002. "The hydropolitical perspective of the Nile question", in Proceedings of the XIVth International Conference of Ethiopian Studies, Vol. 3, edited by Baye Yimam, Richard Pankhurst, David Chapple, Yonas Admassu, Alula Pankhurst, and Birhanu Teferra. Addis Ababa: Institute of Ethiopian Studies.

Trimingham, J. Spencer. 1952. Islam in Ethiopia. London: Oxford University Press.

Tsegaye Gebre-Medhin. August 1997. "Nile". https://allaboutethio.com/20-must-read-poems-of-ethiopia-best-ethiopian-poetry.html."ኩሽ ነው ምድሩ ይለናል ሎሬት ፀጋዬ"፤ https://www.youtube.com/watch?v=Ny2TMcn9msY (accessed on 14th Sept 2021).

Yaqob Arsano. 2007. Ethiopia and the Nile: Dilemmas of national and regional hydropolitics. PhD thesis, Center of Security Studies, Swiss Federal Institute of Technology, Zurich.

Yewulsew Shitie. 2012. Literature as a hydo-political discourse: A comparative analysis of Egyptian and Ethiopian poetry. MA Thesis, Foreign Languages and Literature Dept, Addis Ababa University. Unpublished.

የወያኔው ታላቁ ሤራ በቀድሞው አባላቱ ሲጋለጥ፤ ...የአቶ አብርሃም ያየህና የአቶ ገብረ መድኅን አርአያ ቃለ ምልልስ፤ ግንቦት 1982 ዓ/ም፤ አዲስ አበባ።

ኃይሉ ወልደ ጊዮርጊስ፤ 2001፤ ለዓባይ ውሃ ሙግት፤ አዲስ አበባ፤ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ፕሬስ።


## ለ/ <u>ሥነ ጽሑፋዊ ድርሰቶች</u>


ሀዲስ አለማየሁ፤ 1958 ዓ/ም፤ ፍቅር እስከ መቃብር፤ (6ኛ እትም 1977 ዓ/ም)፣ አዲስ አበባ፤ ኩራዝ አሳታሚ ድርጅት።

ልብሴ በላይ፤ 1991 ዓ/ም፤ "እንደ ስሞታ ለጣና"፤ መቅረዝ፤ ልዩ እትም፣ ቁ. 2፣ አ.ብ.ክ/ባቱማ ቢሮ፣ ባሕር ዳር።

መስፍን ወልደ ማርያም፤ 2005 ዓ/ም፤ "የበረሃው ጌታ"፤ ዛሬም እንጉርጉሮ፤ አዲስ አበባ።

መንግስቱ ዘገዬ፤ 2005 ዓ/ም፤ "አለው መላ መላ!"፤ ቀብድ የበላች ሀገር፤ አዲስ አበባ።

ምንዋጋው ተመስገን፤ 2008 ዓ/ም፤ "ትእምርተ ሚጠት"፤ አካልና ጥላ፤ ደብረ ማርቆስ።

በላይ ማናዬ፤ 2005 ዓ/ም፤ አዙሪት ዘአልፋ፤ አዲስ አበባ።

ሰይፉ መታፈሪያ ፍሬው፤ 2000 ዓ/ም፤ ዐባይ - ፈንጂ የቀበረ ውኀ፤ ደረኮ አሳታሚ። (ይህ በPDF ቅጂ የተገኘ መድበል በዚህ የጥናት ጽሑፍ ውስጥ የተዳሰሱትን የደራሲውን 10 ግጥሞች ያካተተ ነው።)

ታደለ ገድሌ፤1999 ዓ/ም፤ "ዐባይ ሰይጣን አለ!"፤ የዘመን ቀለማት፤ ቅጽ 1፤ አዲስ አበባ።

ታደሰ ሥዩም ንጉሤ፤ 2006 ዓ/ም፤ "የዓባይ ልጆች"፤ የዓባይ ልጆች፤ አዲስ አበባ።

ታደሰ አለነ፤ 1957 ዓ/ም፤ "የዓባይ ጉዞ"፤ ፍልስፍና ያዋቂዎች መከታ ናት፤ አዲስ አበባ።

ትእግስት ጌታቸው፤ 2000 ዓ/ም፤ "የአባይ ሸኝት"፤ አንፀባራቂ ቀለሞች፤ አዲስ አበባ።

ቴዎድሮስ ፀጋዬ፤ 1999 ዓ/ም፤ ነፍሰጡር ስንኞች፤ ("እዬዬ" እና "ወዮላት" የተባሉት ግጥሞች በዚህ መድበል ውስጥ ይገኛሉ።)

ነቢይ መኮንን፤ 1999 ዓ/ም፤ "ይልቅ ዐባይ ጨዋታ አምጣ"፤ ስውር-ስፌት፤ አዲስ አበባ።

አበባው መላኩ፤ 1999 ዓ/ም፤ "አባይ"፤ ከራድዮን፤ 3ኛ እትም፤ አዲስ አበባ።

አበባየሁ ለገሠ፤ 2004 ዓ/ም፤ ቅርጫት ያጡ ፍሬዎች፤ አዲስ አበባ። (መድበሉ "አባይ - ነዳጅ"፣ "የአባይ ከተራ" እና "አባይ ሐዋርያ" የተባሉትን የደራሲው ግጥሞችም ይዟል።)

አበራ ለማ፤ 1994 ዓ/ም፤ "አብዬ አባይ"፣ አውጫጭኝ።

አቤ ጉበኛ፤ 1965 ዓ/ም፤ "ጢስ ዐባይ"፤ እሬትና ማር፤ አዲስ አበባ።

Assefa Gebre Mariam. "The Nile", in The voice፡ Selected poems. Addis Ababa: Chamber Printing House.

አሰፋ ጉያ፤ 1984 ዓ/ም፤ "አባይና ቴቬረ"፤ የከንፈር ወዳጅ፤ አዲስ አበባ።

አየለ ዲ. ሚደቅሳ፤ 2003 ዓ/ም፤ የዓባይ ቋያ፤ አዲስ አበባ፤ ማንኩሳ አሳታሚ።

አያልነህ ሙላቱ፤ 1992 ዓ/ም፤ "ሾተላይ"፤ አዲስ አበባ።

____፤ 2004 ዓ/ም፤ ከድጡ ወደ ማጡ፡- የግዛተ ደርግ ግጥሞች፤ አዲስ አበባ። (ይህ መድበል "አባይ በጉልበቱ" እና "አባይ ንጉሡ" የተባሉትን የደራሲውን ግጥሞች የያዘ ነው።)

አደም ሁሴን፤ 2007 ዓ/ም፤ "ብቻዬን አይደለሁም"፤ እሳት ያልገባው ሐረግ፤ አዲስ አበባ።

ኢደማ፤ 2007 ዓ/ም፤ አዲስ መዝሙርና ሌሎች የግጥም ስብስቦች፤ አዲስ አበባ። (መድበሉ በዚህ ጥናት ውስጥ የተዳሰሱትን የኢደማ አባላት 22 ግጥሞች የያዘ ነው።)

እርቅይሁን በላይነህ፤ 2005 ዓ/ም፤ ታዳኤል፤ አዲስ አበባ።

ኤፍሬም ሥዩም፤ 2008 ዓ/ም፤ ኑ ግድግዳ እናፍርስ፤ አዲስ አበባ። ("አባይ ፩" እና "አባይ ፪" በዚሁ መድበል ውስጥ ይገኛሉ።)

ካሣ አያሌው ካሣ፤ 2004 ዓ/ም፤ተልዕኮ ምፅዓት፤ አዲስ አበባ።

ግርማ ተስፋው፤ 2005 ዓ/ም፤ "ዐባይ ውኃ አይደለም"፤ የጠፋችውን ከተማ ኃሠሣ፤ አዲስ አበባ።

ጌትነት እንየው፤ 2004 ዓ/ም፤ "ዐባይ"፤ እውቀትን ፍለጋ፤ 3ኛ እትም፤ አዲስ አበባ።

የደስደስ ተስፋ፤ 2007 ዓ/ም፤ "የዓባይ ዘመን"፤ እንጀራ ከመከራ፤ አዲስ አበባ።

ይስማዕከ ወርቁ፤ 2001 ዓ/ም፤ ዴርቶጋዳ፤ አዲስ አበባ።

ፀሐይ መልአኩ፤ 2002 ዓ/ም፤ "ምን እንበለው ለዐባይ"፤ የስሜት ትኩሳት፤ አዲስ አበባ።

ጸጋዬ ገብረ መድኅን፤ 1966 ዓ/ም፤ "አባይ"፤ እሳት ወይ አበባ፤ አዲስ አበባ።

Tsegaye Gebre Medhin. 1964 E.C. "Ilma Madhaa Abbaa Gadaa". https://www.youtube.com/watch?v=8b0VWiEyN7I (accessed on 14th Sept 2021).